https://www.path-2-happiness.com/am

الطريق إلى السعادة
The Path to Happiness

https://www.path-2-happiness.com/am



# መልክተኞችና ነቢያት

## ማውጫ

### መልክተኞችና ነቢያት


- መልክተኞች ለሰዎች አስፈላጊ ናቸውን?
- የነቢይነትና የመልክተኝነት እውነታ
- የነቢይነት አስረጅ ምልክቶች
- የመልክተኞች ጥሪ መሰረታዊ መርሕ
- የጽናትና የቁርጠኝነት ባለቤቶች ከሆኑ መልክተኞች ታሪክ በጨረፍታ

https://www.path-2-happiness.com/am



# መልክተኞችና ነቢያት

## መልክተኞች ለሰዎች አስፈላጊ ናቸውን?

አላህ (ሱ.ወ.) የሰው ልጆችን የፈጠራቸው በትክክለኛው ሚዛናዊ ተፈጥሮ ሲሆን፣እውነትን ከሐሰት መለየት ይችሉ ዘንድም አእምሮ ሰጥቷቸዋል። የሰው ልጅ አእምሮ ጉድለት፣እጥረት፣ስሜታዊ ዝንባሌና የጥቅም ተገዥነት የሚጠናወተው ከመሆኑም በላይ ለልዩነትና ለቅራኔም የተጋለጠ በመሆኑ ከፊሉ ሰው በጎ አድርጎ የሚመለከተውን ነገር ሌሎች መጥፎ አድርገው ይወስዳሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን የአንድ ሰው ሀሳብ ራሱ በጊዜና በቦታ መለወጥ ሊለዋወጥ ይችላል። ይህ ሰብአዊ አእምሮ ከግንዛቤው ውጭ የሆኑ ክስተቶችን፣ያልተማራቸው እውቀቶችንና በግለሰቦች አእምሮ ውስጥ የሚመላለሱ ሀሳቦችን ማወቅ የማይችል እስከሆነ ድረስ፣ስለ ፈጣሪ ዓለማዎች፣ትእዛዛትና እገዳዎች ማወቅ በእጅጉ ይሳነዋል። በመሆነም የአላህ መልክት ለሰዎች በቀጥታ ሊተላለፍላቸው አይችልም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَا كَانَ لِبَشَرٍ أَن يُكَلِّمَهُ ٱللَّهُ إِلَّا وَحْيًا أَوْ مِن وَرَآيِٕ حِجَابٍ أَوْ يُرْسِلَ رَسُولًا فَيُوحِيَ بِإِذْنِهِۦ مَا يَشَآءُ إِنَّهُۥ عَلِيٌّ حَكِيمٌ ﴿٥١﴾} [الشورى: ٥١]؛

‹‹ለሰውም አላህ በራእይ ወይም ከግርዶ ወዲያ፣ወይም መልክተኛን (መልአክን) የሚልክና በፈቃዱ የሚሻውን ነገር የሚያወርድለት ቢኾን እንጅ፣(በገሃድ) ሊያናግረው ተገቢው አይደለም። እርሱ በላይ ጥበበኛ ነውና።››[አል ሹራ:51]

በአላህና በአገልጋይ ባሮቹ መካከል ምርጥ አምባሳደሮች ይሆኑ ዘንድ፣አላህ (ሱ.ወ.) መልክተኞችንና ነቢያትን ከሰው ልጆች መካከል ምርጦች አድርጎ የመረጣቸውም ለዚህ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱللَّهُ يَصْطَفِي مِنَ ٱلْمَلَٰٓئِكَةِ رُسُلًا وَمِنَ ٱلنَّاسِۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌۢ بَصِيرٌ ﴿٧٥﴾}[الحج: ٧٥]،

### ገርነትና ቅለት ይኑርህ

‹‹ቁንጮ በደረሰ የድል አድራጊነቱ ጊዜ እንኳ ሙሐመድ ገርነትና ቀለል ባይነቱን እንደጠበቀ ነበር። ሰዎች ወደተሰባሰቡበት ክፍል ሲገባ ለርሱ ክብር ተነስቶ መቆምንና ከልክ ያለፈ የአክብሮት አቀባበል ማድረግንም ይጠላ ነበር።››

**ዋሽንግተን ኤርቨንጅ**

**አሜሪካዊ ዲፕሎማትና የስነጽሑፍ ሰው**



‹‹አላህ ከመላእክት ውስጥ መልክተኞችን ይመርጣል፤ከሰዎችም፣(እንደዚሁ)፤አላህ ሰሚ ተመልካች ነው።››[አል ሐጅ:75]

ሰዎችን ወደ ጌታቸው መንገድ እንዲመሩና ከጨለማ ወደ ብርሃን እንዲያወጧቸው፣መልክቱ ከደረሳቸው በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር አላህ (ሱ.ወ.) መልክተኞችን ልኳል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{رُّسُلًا مُّبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَى ٱللَّهِ حُجَّةٌۢ بَعْدَ ٱلرُّسُلِۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَزِيزًا حَكِيمًا ﴿١٦٥﴾}[النساء: ١٦٥].

‹‹ከመልክተኞቹ በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር፣አብሳሪዎችንና አስጠንቃቂዎች የኾኑን መልክተኞች (ላክን)፤አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው።››[አል ኒሳእ:165]

ለሰብአዊ ፍጡራን የሚበጀውን ለማስተማርና ስነምግራቸውን ለማረቅ፣ነቢያትና መልክተኞች ከሰው ልጆች መካከል የተመረጡ መሆናቸው አላህ ለአገልጋዮቹ ከዋለላቸው ታላላቅ ችሮታዎች አንዱ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَقَدْ مَنَّ ٱللَّهُ عَلَى ٱلْمُؤْمِنِينَ إِذْ بَعَثَ فِيهِمْ رَسُولًا مِّنْ أَنفُسِهِمْ يَتْلُواْ عَلَيْهِمْ ءَايَٰتِهِۦ وَيُزَكِّيهِمْ وَيُعَلِّمُهُمُ ٱلْكِتَٰبَ وَٱلْحِكْمَةَ وَإِن كَانُواْ مِن قَبْلُ لَفِي ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ﴿١٦٤﴾} [آل عمران: 164].

‹‹አላህ በምእመናን ላይ ከጎሳቸው የኾነን፤በነርሱ ላይ አንቀጾቹን የሚያነብ የሚያጠራቸውም፣መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸውም የኾነን መልክተኛ በውስጣቸው በላከ ጊዜ፤በእርግጥ ለገሰላቸው፤እነርሱም ከዚያ በፊት በግልጽ ስሕተት ውስጥ ነበሩ።››[ኣሊ ኢምራን :164]

አላህ (ሱ.ወ.) መልክተኛን መላኩና መልክተኛውም፦

{مِّنْ أَنفُسِهِمْ}

‹‹ከጎሳቸው የኾነ››

መሆኑ በእርግጥም ታላቅ ጸጋ ነው።

ይህ ጸጋ ከራሱ ዘንድ ክቡር ቃሉን ለሰው ልጅ እንዲያደርስ፣ስለ አላህ

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ሕልውና ስለ ባሕርያቱ እንዲያሳውቅ፣ስለ አምላክነት አውነታና ልዩ መለያዎች እንዲያስተምረው፤ከዚያም ስለራሱ ስለ ሰው ልጅ ስለ ደካማው አገልጋይ፣ስለ አነዋነዋሩ፣ስለ እንቅስቃሴውና ስለ እርጋታው፣ ሕያው ወደሚያደርገው ነገር ሊጠራው፣ቁሳዊና ሕሊናዊ ሁኔታውን ወደሚያሻሽለው ሊመራው፣የሰማያትና የምድር ያህል ስፋት ወዳለው ገነት ሊጠራው . . መልክተኛ በመላክ የሚንጸባረቅ ነው:: ይህ ሁሉ ገደብ የለሽ ጸጋ፣ይህ ታላቅ ችሮታ፣ይህ ታላቅ ስጦታ በቃላት የማይገለጽ ወሰን የለሽ ቸርነቱ ከመሆን ውጭ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?! ይህም ብቻ ሳይሆን ያነጻቸዋል፤ከፍ ያደርጋቸዋል፤ያጠራቸዋልም:: ልቦናቸውን አስተሳሰባቸውንና መንፈሳቸውንም፤ቤቶቻቸውን፣ክብራቸውንና ግንኙነቶቻቸውንም፤አነዋነዋራቸውን፣ሕብረተሳቦቻቸውንና ስርዓቶቻቸውንም ከማጋራት፣ከጣዖታዊነት፣ከተረትና ከቅዠቶች ቆሻሻ ያጠራል:: እነዚህ ሁሉ በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ከሚረጩትና የሰውን ሰብእና እና ክቡርነት ከሚጻረሩ ወራዳ አምልኮዎችና ልማዶች ያነጻል:: ግንዛቤን፣አምልኮተ አላህን፣በጎ ልማዶችንና እሴቶችን ከሚበክለው የዘመነ ጃህሊያ ብክለቶችም ያነጻል:: ማይምነት ወይም ጃህሊያ ዛሬም ጃህሊያ ነውና:: የሁሉም ዘመንና ስፍራ ጃህሊያ የየራሱ ብክለትና ርክሰት አለውና:: የሰው ልጆች አመለካከታቸውን ከሚገዛ መለኮታዊ እምነትና ከዚህ እምነት ከሚመነጨው የሕይወት መመሪያ ሕግ የሚራቆቱበት ሁኔታ ካለ ብዛት ካላቸው የጃህሊያ ገጽታዎች አንዱ እንጂ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም:: በመሆኑም የሰውን ዘር ከዚህ ጥንታዊም ይሁን ዘመናዊ ጃህሊያ ማዳን ወሳኝ ይሆናል:: ዘመናዊው ጃህሊያም በስነምግባራዊና ማሕበራዊ ገጽታው፣ስለሰው ልጅ የሕይወት ግቦችና ዓላማዎች ባለው ግንዛቤም ጭምር፣ዛሬ በተደረሰበት የላቀ የሥልጣኔና የዕድገት ዘመንም ያው የጥንቱን የማይማዊነት ባሕርያት የሚወክል ነው::

{وَإِن كَانُواْ مِن قَبْلُ لَفِي ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ۝٢}[الجمعة: ٢]،

‹‹እነርሱም ከርሱ በፊት በግልጽ ስሕተት ውስጥ ነበሩ::››[አል ጁሙዓ:2]





ቀደም ሲል በአመለካከትና በእምነት ግልጽ ስሕተት፣በሕይወት ዓለማ ግንዛቤና አካሄድ ግልጽ ስሕተት፣በወግና ልማድ ግልጽ ስሕተት፣የሥርዓትና የስነምግባር ግልጽ ስሕተት፣በማህበረሰብና በሞራላዊ ጉዳዮችም ግልጽ ስሕተት . . በሁሉም መስክ ግልጽ ስሕተትና ጥመት ውስጥ ነበሩ::

### ሃይማኖት ካልገራቸው የሰው አውሬዎች ናቸው!

‹‹አሜሪካ ትጸልያለች ወይስ አትጸልይም?›› በተሰኘ የዴቪድ ባርቶን መጽሐፍ ውስጥ በሰፈረውና በአንድ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ በተደረገ አኃዛዊ ጥናት መሰረት፦

- ከአሜሪካ ሴቶች መካከል 80% የሚሆኑት በሕይወታቸው ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ ለአስገድዶ መደፈር ጥቃት ተጋልጠዋል!!
- በየዕለቱ ተገደው የሚደፈሩ ሴቶች ቁጥር ከ1900 በላይ ሲሆን፣በዚህም ምክንያት 30% ያህል የሚሆኑ አሜርካውያት ልጃገረዶች በአስራ አራት ዓመታቸው ለእርግዝና ለውርጃ ወይም ለወሊድ ይጋለጣሉ::
- 61% የሚሆነው የአስገድዶ መድፈር ጥቃት የተፈጸመው ዕድሜያቸው ከአስራ ስምንት ዓመት በታች በሆኑት ሴቶች ላይ ነው::
- 29% የሚሆነው የአስገድዶ መድፈር ጥቃት የተፈጸመው ከአስራ አራት ዓመት በታች በሆኑ ሕጻናት ላይ ነው::

**ዴቪድ ባርቶን**
**አሜሪካዊ ጸሐፊ**



## የነቢይነትና የመልክተኛነት እውነታ

የአላህ (ሱ.ወ.) ጥበብ ሆኖ እያንዳንዱ መልክተኛ ከሚላክባቸው ወገን እንዲሆን ተደርጓል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ إِلَّا رِجَالٗا نُّوحِيٓ إِلَيۡهِمۡ}[النحل: ٤٣]،

‹‹ከአንተም በፊት ወደነሱ ወሕይን (ራእይን) የምናወርድላቸውን፣ሰዎችን እንጂ ሌላን አልላክንም፤››[አል ነሕል:43]

መልእክቱን እንዲያውቁትና እንዲረዱትም የሚላከው መልክተኛ የሚላክበት ሕዝብ ቋንቋ ተናጋሪ እንዲሆንም ተደርጓል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن رَّسُولٍ إِلَّا بِلِسَانِ قَوۡمِهِۦ لِيُبَيِّنَ لَهُمۡۖ فَيُضِلُّ ٱللَّهُ مَن يَشَآءُ وَيَهۡدِي مَن يَشَآءُۚ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ۝٤}[إبراهيم: ٤].

‹‹ከመልክተኛ ማንኛውንም፣ለነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ በወገኖቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አልላክንም፤አላህም የሚሻውን ያጠማል፤የሚሻውንም ያቀናል፤እርሱም

አሸናፊው፣ጥበበኛው ነው።››[ኢብራሂም:4]

ነቢዮችና መልክተኞች የምሉእ አእምሮና የጤነኛ ተፈጥሮ ባለቤቶች ሲሆኑ በእውነተኛነትና በታማኝነት የሚገለጹ፣ሰብአዊ ፍጡራንን ከሚጠናወቱ እንከኖችና ጉድለቶች ሁሉም የተጠበቁ ናቸው። እይታን ከሚስብና አመዛኝ ግምት ያላቸውን ሰዎች ሊያርቅ ከሚችል አካላዊ እንከንም የተጠበቁ ናቸው። ከሰዎች ሁሉ የላቀና የተሟላ የመልካም ስነምግባር ባለቤቶችም ናቸው። በሰብእናቸውና በባህርያቸው አላህ (ሱ.ወ.) ያጠራቸው ሲሆን፣ከሰው ሁሉ ቸሮችና ለጋሾች አድርጓቸዋል። በትእግስት፣በዕውቀት፣በገርነት፣በደግነት፣በጀግንነትና በፍትሐዊነት ባህርያት የተካኑ አድርጓቸዋል። በነዚህ ውብ ባሕርያት ከሕዝቦቻቸው ውስጥ አቻ የሌላቸው ሲሆኑ ተለይተው የሚታወቁባቸው መለያቸው ናቸው። መልክተኞች መልእክቱን ለመሸከምና አደራውን ለማድረስ አላህ (ሱ.ወ.) ከፍጥረታቱ ውስጥ ያላቃቸውና የመረጣቸው የርሱ ምርጦች ናቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱللَّهُ أَعۡلَمُ حَيۡثُ يَجۡعَلُ رِسَالَتَهُۥ}[الأنعام: ١٢٤

‹‹አላህ መልክቱን የሚያደርግበትን ስፍራ ዐዋቂ ነው፤››[አል አንዓም:124]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱللَّهَ ٱصۡطَفَىٰٓ ءَادَمَ وَنُوحٗا وَءَالَ إِبۡرَٰهِيمَ وَءَالَ عِمۡرَٰنَ عَلَى ٱلۡعَٰلَمِينَ ٣٣}[آل عمران: 33].

‹‹አላህ ኣደምን፣ኑሕንም፣የኢብራሂምንም ቤተሰብ፣የዒምራንንም ቤተሰብ፣በዓለማት ላይ መረጠ።››[ኣሊ ዒምራን:33]

ስለ ነቢዩ ዒሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِذۡ قَالَتِ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ يَٰمَرۡيَمُ إِنَّ ٱللَّهَ يُبَشِّرُكِ بِكَلِمَةٖ مِّنۡهُ ٱسۡمُهُ ٱلۡمَسِيحُ عِيسَى ٱبۡنُ مَرۡيَمَ وَجِيهٗا فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِ وَمِنَ ٱلۡمُقَرَّبِينَ ٤٥ وَيُكَلِّمُ ٱلنَّاسَ فِي ٱلۡمَهۡدِ وَكَهۡلٗا وَمِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ٤٦}[آل عمران: ٤٥-٤٦]

‹‹መላእክት ያሉትን (አስታውስ)፦ መርየም ሆይ! አላህ ከርሱ በኾነው ቃል፣ስሙ አልመሲሕ ዒሳ የመርየም ልጅ፣በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም የተከበረ፣ከባለሟሎችም በኾነ (ልጅ) ያበስርሻል፤በሕጻንነቱና በከፈኒሳነቱ (የበሰለ ሰው ዕድሜው ከ30-40 የኾነ) ሰዎቹን ያነጋግራል፤ከመልካሞቹም ነው (አላት)።››[ኣሊ ዒምራን:45-46]

ሙሐመድ [የአላህ ሰላምና እዝነቱ በርሳቸው ላይ ይሁን] በነቢይነት ከመላካቸው በፊት በማሕበረሰባቸው ውስጥ ‹‹እውነተኛው፣ታማኙ›› በመባል ይጠሩ የነበረ ሲሆን፣አላህም ታላቅ ስነምግባራቸውን ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፦

{وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٖ ٤}[القلم: 4].

‹‹አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ።››[አልቀለም:4]

እነዚህን መልክተኞችና ነቢያት አላህ (ሱ.ወ.) በታላቅ ባሕርያትና በምጡቅ ስነምግባራት የገለጻቸውም ቢሆንም፣ሰብአዊ ፍጡራን በመሆናቸው እንደማናቸውም ሰው ይርባቸዋል፣ይታመማሉ፣ይተኛሉ፣ይበላሉ፣ይጠጣሉ፣ያገባሉ፣ይሞታሉ . . አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا رُسُلٗا مِّن قَبۡلِكَ وَجَعَلۡنَا لَهُمۡ أَزۡوَٰجٗا وَذُرِّيَّةٗ}[الرعد: ٣٨] ،

‹‹ከአንተ በፊትም መልክተኞችን በእርግጥ ልከናል፤ለነርሱም ሚስቶችንና ልጆችን አድርገናል፤››[አልረዕድ:38]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّكَ مَيِّتٞ وَإِنَّهُم مَّيِّتُونَ ٣٠}[الزمر: ٣٠]،

‹‹አንተ ሟች ነህ፤እነርሱም ሟቾች ናቸው።››[አል ዙመር:30]

ለነቢዩና ለመልክተኛው ለሙሐመድ [የአላህ ሰላምና እዝነቱ በርሳቸው ላይ ይሁን] አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَتُخۡفِي فِي نَفۡسِكَ مَا ٱللَّهُ مُبۡدِيهِ}[الأحزاب: ٣٧]،

‹‹ . . አላህ ገላጩ የኾነን ነገር በነፍስህ ውስጥ የምትደብቅና . . ››[አል አሕዛብ:37]

በመሆኑም ነቢያት ጭቆና ሊደርስባቸው፣ሊገደሉ ወይም ከአገራቸው ሊሰደዱ ይችላሉ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذۡ يَمۡكُرُ بِكَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لِيُثۡبِتُوكَ أَوۡ يَقۡتُلُوكَ أَوۡ يُخۡرِجُوكَۚ وَيَمۡكُرُونَ وَيَمۡكُرُ ٱللَّهُۖ وَٱللَّهُ خَيۡرُ ٱلۡمَٰكِرِينَ ٣٠}[الأنفال: ٣٠]،

‹‹እነዚያም የካዱት ሊያስሩህ፣ወይም ሊገድሉህ፣ወይም (ከመካ) ሊያስወጡህ ባንተ ላይ በመከሩብህ ጊዜ፣(አስታውስ)፤ይመክራሉም፣አላህም ተንኮላቸውን ይመልስባቸዋል፤አላህም ከመካሪዎቹ ሁሉ በላይ ነው።››[አል አንፋል:30]

ይሁን እንጅ መልካሙ ፍጻሜ፣ድልና መመቻቸት በዛሬውም ሆነ በመጪው ሕይወት የነርሱ ይሆናል።



## የነቢይነት አስረጅ ምልክቶች

አላህ (ሱ.ወ.) ወደ ባሮቹ የላካቸው ነቢያትና መልክተኞች፣ጥሪያቸውና ትምሕርታቸው እውነተኛ ስለመሆኑ፣በእርግጥ ከር ሱ የተላኩ

ስለመሆናቸው አስረጅና ማረጋገጫዎችን አላህ ሰጥቷቸዋል። ይህም በነርሱ ላለማመንና እነርሱን ላለመታዘዝ በሰዎች ዘንድ ምንም ማመካኛ እንዳይኖር ለማድረግ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَقَدْ أَرْسَلْنَا رُسُلَنَا بِٱلْبَيِّنَٰتِ} [الحديد: ٢٥]،

‹‹መልክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን፤››[አል ሐዲድ:25]



የመልክተኞቹን እውነተኛነት የሚያረጋግጡ እነዚያ ማስረጃዎች ብዛት ያላቸው ሲሆኑ፣ከዋነኞቹ ውስጥ የሚከተሉትን እናገኛለን፦

1. አላህ (ሱ.ወ.) መልክተኞችንና ነቢያትን በምልክቶችና በተአምራት ያግዛቸዋል። እነዚህም ሰዎች ሊያደርጓቸው የማይችሉ ከተለመዱ የተፈጥሮ ሕግጋት ውጭ የሆኑና በመልክተኞቹና በነቢያቱ እጅ የሚፈጸሙ ትንግርታዊ ነገሮችና ክስተቶች ናቸው። ከነዚህ መካከል ወደ እባብነት የሚለወጠው የሙሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] በትር አንዱ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

وَمَا تِلْكَ بِيَمِينِكَ يَٰمُوسَىٰ ﴿١٧﴾ قَالَ هِىَ عَصَاىَ أَتَوَكَّؤُا۟ عَلَيْهَا وَأَهُشُّ بِهَا عَلَىٰ غَنَمِى وَلِىَ فِيهَا مَـَٔارِبُ أُخْرَىٰ ﴿١٨﴾ قَالَ أَلْقِهَا يَٰمُوسَىٰ ﴿١٩﴾ فَأَلْقَىٰهَا فَإِذَا هِىَ حَيَّةٌ تَسْعَىٰ ﴿٢٠﴾ قَالَ خُذْهَا وَلَا تَخَفْ سَنُعِيدُهَا سِيرَتَهَا ٱلْأُولَىٰ ﴿٢١﴾ وَٱضْمُمْ يَدَكَ إِلَىٰ جَنَاحِكَ تَخْرُجْ بَيْضَآءَ مِنْ غَيْرِ سُوٓءٍ ءَايَةً أُخْرَىٰ ﴿٢٢﴾ لِنُرِيَكَ مِنْ ءَايَٰتِنَا ٱلْكُبْرَى ﴿٢٣﴾} [طه: ١٧ - ٢٣].

‹‹ሙሳ ሆይ! ይህችም በቀኝ እጅህ ያለችው ምንድን ናት? (ተባለ)። ፦ እርሷ በትሬ ናት፤በርሷ ላይ እደገፍባታለሁ፤በርሷም ለፍየሎቼ ቅጠልን አራግፍባታለሁ፤ለኔም በርሷ ሌሎች ጉዳዮች አሉኝ፤አለ። (አላህም) ሙሳ ሆይ! ጣላት አለው። ጣላትም፤ወዲያውኑ እርሷ የምትሮጥ እባብ ኾነች። ፦ ያዛት፤አትፍራም፤ወደ መጀመሪያ ጠባይዋ እንመልሳታለን አለው። እጅህንም ወደ ብብትህ አግባ፤ሌላ ታምር ስትኾን ያለ ነውር ነጭ ኾና ትወጣለችና። ከታምራቶቻችን ታላቋን እናሳይህ ዘንድ፣(ይህን ሠራን)።››[ጣሃ:17-23]

የነብዩ ዒሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] ተአምር ደግሞ በአላህ ፈቃድ ዲዳ ሆኖ የተወለደን ሰውና ለምጻምን መፈወስ ነበር። ድንግል ማርያም በዒሳ ልደት [የአላህ ሰላም በሁለቱም ላይ ይሁን] በተበሰረች ጊዜ በርሷ አንደበት



አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قَالَتْ رَبِّ أَنَّىٰ يَكُونُ لِى وَلَدٌ وَلَمْ يَمْسَسْنِى بَشَرٌ قَالَ كَذَٰلِكِ ٱللَّهُ يَخْلُقُ مَا يَشَآءُ إِذَا قَضَىٰٓ أَمْرًا فَإِنَّمَا يَقُولُ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ﴿٤٧﴾ وَيُعَلِّمُهُ ٱلْكِتَٰبَ وَٱلْحِكْمَةَ وَٱلتَّوْرَىٰةَ وَٱلْإِنجِيلَ ﴿٤٨﴾ وَرَسُولًا إِلَىٰ بَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ أَنِّى قَدْ جِئْتُكُم بِـَٔايَةٍ مِّن رَّبِّكُمْ أَنِّىٓ أَخْلُقُ لَكُم مِّنَ ٱلطِّينِ كَهَيْـَٔةِ ٱلطَّيْرِ فَأَنفُخُ فِيهِ فَيَكُونُ طَيْرًۢا بِإِذْنِ ٱللَّهِ وَأُبْرِئُ ٱلْأَكْمَهَ وَٱلْأَبْرَصَ وَأُحْىِ ٱلْمَوْتَىٰ بِإِذْنِ ٱللَّهِ وَأُنَبِّئُكُم بِمَا تَأْكُلُونَ وَمَا تَدَّخِرُونَ فِى بُيُوتِكُمْ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَةً لَّكُمْ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴿٤٩﴾ وَمُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَىَّ مِنَ ٱلتَّوْرَىٰةِ وَلِأُحِلَّ لَكُم بَعْضَ ٱلَّذِى حُرِّمَ عَلَيْكُمْ وَجِئْتُكُم بِـَٔايَةٍ مِّن رَّبِّكُمْ فَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ وَأَطِيعُونِ ﴿٥٠﴾ إِنَّ ٱللَّهَ رَبِّى وَرَبُّكُمْ فَٱعْبُدُوهُ هَٰذَا صِرَٰطٌ مُّسْتَقِيمٌ ﴿٥١﴾} [آل عمران: ٤٧ - ٥١].

‹‹፦ ጌታዬ ሆይ! ሰው ያልነካኝ ስኾን፣ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል? አለች፤ነገሩ እንደዚህሽ ነው፤አላህ የሚሻውን ይፈጥራል፤አንዳችን በሻ ጊዜ፣ለርሱ ኹን ይለዋል፤ወዲያውኑም ይኾናል፤አላት። ጽሕፈትንና ጥበብንም፣ተውራትንና ኢንጂልንም ያስተምረዋል። ወደ እሥራኤልም ልጆች መልክተኛ ያደርገዋል፤(ይላልም)፦ እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣኋችሁ። እኔ ለናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ፤በርሱም እተነፍስበታለሁ፤በአላህም ፈቃድ ወፍ ይኾናል። በአላህም ፈቃድ ዕውር ኾኖ የተወለደን፣ለምጸኛንም፣ አድናለሁ፤ሙታንንም አስነሳለሁ። የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ፤የምታምኑ እንደኾናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ታምር አለበት። ከተውራትም ከኔ በፊት ያለውን ያረጋገጥሁ ስኾን፣የዚያንም በናንተ ላይ እርም የተደረገውን ከፊል ለናንተ እፈቅድ ዘንድ፣(መጣኋችሁ) ከጌታችሁም በኾነ ታምር መጣኋችሁ። አላህንም ፍሩ፤ታዘዙኝም። አላህ ጌታዬና ጌታችሁ ነው፤ስለዚህ ተገዙት፤ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው (አላቸው)።››[አል ዒምራን:47-51]

የነብዩ ሙሐመድ [የአላህ ሰላምና እዝነቱ በርሳቸው ላይ ይሁን]፣ታላቁ ተአምር የማያነቡና የማይጽፉ ነቢይ ከመሆናቸውም ጋር ታላቁ ቁርኣን ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُل لَّئِنِ ٱجْتَمَعَتِ ٱلْإِنسُ وَٱلْجِنُّ عَلَىٰٓ أَن يَأْتُوا۟ بِمِثْلِ هَٰذَا ٱلْقُرْءَانِ لَا يَأْتُونَ بِمِثْلِهِۦ وَلَوْ كَانَ بَعْضُهُمْ لِبَعْضٍ ظَهِيرًا ﴿٨٨﴾ وَلَقَدْ صَرَّفْنَا لِلنَّاسِ فِى هَٰذَا ٱلْقُرْءَانِ مِن كُلِّ مَثَلٍ فَأَبَىٰٓ أَكْثَرُ ٱلنَّاسِ إِلَّا كُفُورًا ﴿٨٩﴾} [الإسراء: ٨٨ - ٨٩]،

‹‹፦ ሰዎችም ጋኔኖችም የዚህን ቁርኣን ብጤ በማምጣት ላይ ቢሰባሰቡ፣ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢኾንም እንኳ፣ብጤውን አያመጡም፤በላቸው። በዚህም ቁርኣን ውስጥ ከምሳሌው ሁሉ ለሰዎች በእርግጥ መላለስን፤አብዛኞቹም ሰዎች፣ክሕደትን



https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am




እንጂ ሌላን እምቢ አሉ።››[አል እስራእ፡88-89]

የመልክተኞችና የነቢያት ታምራት እነዚህና ሌሎችም ነበሩ።

አላህ (ሱ.ወ.) ለመልክተኞችና ለነብዮች የሰጣቸውን ምልክቶችና ታምራት ስናስተነትን በሦስት ጉዳዮች ስር የሚካተቱ ሆነው እናገኛቸዋለን። እነሱም፦ ዕውቀት፣ችሎታና መብቃቃት ናቸው። ከሕዋሳዊ ግንዛቤ ውጭ የሆኑ ያለፉና የሚመጡ ጉዳዮችን በተመለከተ፣ነቢዩ ዒሳ ለሕዝባቸው የሚበሉትንና በየቤቶቻቸው የሚያስቀምጡትን መንገራቸው፣ነብያችን ሙሐመድም ስላለፉት ሕዝቦች፣ወደፊት ስለሚከሰቱ ተፈ‌ታታኝ ሁኔታዎችና ለትንሣኤ ቀን መምጫ መቃረብ ምልክት ስለሆኑ ምልክቶች የተናገሯቸው ትንቢቶች፣ . . እነዚህ ሁሉ በዕውቀት ስር የሚካተቱ ናቸው። የበትር ወደ እባብነት መለወጥ፣ዲዳንና ለምጻምን መፈወስ፣ሙታንን ማስነሳት፣አላህ መልክተኛው ሙሐመድን □ ከሰዎች ጥቃት መጠበቁ፣እነዚህ ደግሞ በችሎታ ስር የሚካተቱ ታምራት ናቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَـٰٓأَيُّهَا ٱلرَّسُولُ بَلِّغْ مَآ أُنزِلَ إِلَيْكَ مِن رَّبِّكَ ۖ وَإِن لَّمْ تَفْعَلْ فَمَا بَلَّغْتَ رِسَالَتَهُۥ ۚ وَٱللَّهُ يَعْصِمُكَ مِنَ ٱلنَّاسِ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْكَـٰفِرِينَ ﴿٦٧﴾}[المائدة: ٦٧]،

‹‹አንተ መልክተኛ ሆይ! ከጌታህ ወደ አንተ የተወረደውን አድርስ፤ባትሠራም (ጥቂትንም ብታስቀር) መልክቱን አላደረስክም፤(አድርስ) አላህም ከሰዎች ይጠብቅሃል፤አላህ ከሓዲዎችን ሕዝቦች አያቀናምና።››[አል ማእዳህ፡67]

እነዚህ ታምራቶች የሚሞረኮዙባቸው ሦስቱ ነገሮች ማለትም ዕውቀት ችሎታና መብቃቃት፣በተሟላና ፍጹማዊ በሆነ መልካቸው ለአላህ ብቻ የተገቡ ናቸው።



2. ቀዳሚዎቹ ነብያት በቀጣይ ስለሚመጡ ነቢያት ማብሰራቸው፦

ከነብይነት ማረጋገጫዎች አንዱ፣የቀደሙ ነቢያት ከነሱ በኋላ ስለሚመጡ ነቢያት ለሕዝቦቻቸው ብስራት መንገራቸው ነው። እያንዳንዱ ነብዩ ሙሐመድ ﷺ በርሱ የሕይወት ዘመን ከአላህ ከተላኩ አምኖ ሊከተላቸው አላህ (ሱ.ወ.) ቃል ኪዳን አስገብቶታል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذْ أَخَـذَ ٱللَّهُ مِيثَـٰقَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ لَمَآ ءَاتَيْتُكُم مِّن كِتَـٰبٍ وَحِكْمَةٍ ثُمَّ جَآءَكُمْ رَسُـولٌ مُّصَدِّقٌ لِّمَا مَعَكُـمْ لَتُؤْمِنُنَّ بِهِۦ وَلَتَنصُرُنَّهُۥ ۚ قَالَ ءَأَقْرَرْتُمْ وَأَخَذْتُمْ عَلَىٰ ذَٰلِكُمْ إِصْرِى ۖ قَالُوٓا۟ أَقْرَرْنَا ۚ قَالَ فَٱشْـهَدُوا۟ وَأَنَا۠ مَعَكُم مِّنَ ٱلشَّـٰهِدِينَ ﴿٨١﴾}[آل عمران: ٨١].

‹‹አላህ የነቢያትን ቃል ኪዳን፣ከመጽሐፍና ከጥበብ ሰጥቻችሁ ከዚያም ከእናንተ ጋር ላላው (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ መልክተኛ ቢመጣላችሁ፣በርሱ በእርግጥ እንደምታምኑበት በእርግጥም እንድትረዱት ሲል በያዘ ጊዜ (አስታውስ)፤አረጋገጣችሁን? በይሃችሁ ላይ ኪዳኔን ያዛችሁም? አላቸው፤አረጋገጥን አሉ፤እንግዲያስ መስክሩ፤እኔም ከእናንተ ጋር ከመስካሪዎቹ ነኝ አላቸው።››[ኣሊ. ዒምራን፡81]



3. የነቢያትን ሁኔታ መመልከት፦

ነብዮችና መልክተኞች ከሕዝቦቻቸው ጋር ተቀላቅለው በአብሮነት ይኖሩ ነበር። ከዚህም ሰዎች ስለ ማንነታቸውና ስለ ስነምግባራቸው በቀላሉ ይረዳሉ፤በሚያስተምሩት ነገርም እውነተኞች መሆናቸውን ይገነዘባሉ። አይሁድ ንጹይቱን መርየምና የአላህን ነብይ ዒሳን [የአላህ ሰላም በሁለቱም ላይ ይሁን] በወነጀሉ ጊዜ፣አላህ (ሱ.ወ.) የሁለቱን እውነተኛነት ግልጽ አድርጓል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَأَتَـتْ بِهِۦ قَوْمَهَا تَحْمِلُهُۥ ۖ قَالُوا۟ يَـٰمَرْيَمُ لَقَدْ جِئْتِ

## ዘላለማዊው ታምር

‹‹ከሙሐመድ በፊት የነበሩ ነቢያት ተአምራት በእርግጥ ጊዜያዊ ነበሩ። ቁርኣንን ግን ተጽእኖ ፈጣሪነቱ ቋሚና ቀጣይ በመሆኑ ‹‹ዘላለማዊው ተአምር›› ብለን ልንሰይመው እንችላለን። አንድ አማኝ በየትኛውም ጊዜና ስፍራ የአላህን መጽሐፍ በማንበብ ብቻ ይህን ተአምር በቀላሉ ማየት ይችላል። በዚህ ተአምር ውስጥም እስላም ላስመዘገበው ሰፊና ፈጣን የስርጭት ሽፋን አሳማኝ ምክንያትና ትንተና እናገኛለን። አውሮፓውያን ቁርኣንን ስለማያውቁት ወይም ተአማኒነት የሚጎድላቸው ብቻ ሳይሆኑ ሕይወት አልባ በሆኑ ትርጉሞች አማካይነት ብቻ የሚያውቁት በመሆኑ የዚህን ፈጣንና ሰፊ ስርጭት መንስኤ ምን እንደሆነ አይረዱም።››

ኤይተን ዴይነህ

ፈረንሳዊ ሰዓሊና አሳቢ



https://www.path-2-happiness.com/am

شَيْـًٔا فَرِيًّا (٢٧) يَـٰٓأُخْتَ هَـٰرُونَ مَا كَانَ أَبُوكِ ٱمْرَأَ سَوْءٍ وَمَا كَانَتْ أُمُّكِ بَغِيًّا (٢٨) فَأَشَارَتْ إِلَيْهِ ۖ قَالُوا۟ كَيْفَ نُكَلِّمُ مَن كَانَ فِى ٱلْمَهْدِ صَبِيًّا (٢٩) قَالَ إِنِّى عَبْدُ ٱللَّهِ ءَاتَىٰنِىَ ٱلْكِتَـٰبَ وَجَعَلَنِى نَبِيًّا (٣٠) وَجَعَلَنِى مُبَارَكًا أَيْنَ مَا كُنتُ وَأَوْصَـٰنِى بِٱلصَّلَوٰةِ وَٱلزَّكَوٰةِ مَا دُمْتُ حَيًّا (٣١) وَبَرًّۢا بِوَٰلِدَتِى وَلَمْ يَجْعَلْنِى جَبَّارًا شَقِيًّا (٣٢) وَٱلسَّلَـٰمُ عَلَىَّ يَوْمَ وُلِدتُّ وَيَوْمَ أَمُوتُ وَيَوْمَ أُبْعَثُ حَيًّا (٣٣)}[مريم: ٢٧- ٣٣]،

‹‹በርሱም የተሸከመችው ኾና ወደ ዘመዶቿ መጣች፤- መርየም ሆይ! ከባድን ነገር በእርግጥ ሠራሽ አሏት:: የሃሩን እኅት ሆይ! አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም፤እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም፤አሉዋት:: ወደርሱም ጠቀሰች፤በአንቀልባ ያለን ሕፃን እንዴት እናናግራለን! አሉ:: (ሕፃኑም) አለ፦ እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፤መጽሐፍን ሰጥቶኛል፣ነቢይም አድርጎኛል:: በየትም ስፍራ ብኾን ብሩክ አድርጎኛል፤በሕይወትም እስከ አለሁ ሶላትን በመስገድ፣ዘካንም በመስጠት አዞኛል:: ለእናቴም ታዛዥ (አድርጎኛል)፤ትዕቢተኛ እምቢተኛም አላደረገኝም:: ሰላምም በኔ ላይ ነው፣በተወለድሁ ቀን በምሞትበትም ቀን፣ሕያው ሆኘ በምቀሰቀስበትም ቀን፤››[መርየም:27-33]

ነቢዩ ዒሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] በዚህ ሁኔታ ጨቅላ ሕጻን ኾነው ተናግረዋል:: ቁረይሾችም መልክተኛው ሙሐመድን ﷺ በነብይነት ከመላካቸው በፊት ‹‹እውነተኛው ታማኝ›› ብለው ይጠሯቸው ነበር:: ይህም በእውነተኛነታቸውና ከማንም ይበልጥ በማሕበረሰቡ ውስጥ ታማኝ የነበሩ በመሆናቸው ነው:: የነብዩ ﷺ ሰብእና እና የሕይወት ታሪካቸው ትልቁ ማስረጃ በመሆኑ፣ቁርኣንም ይህን አቋማቸውን ለነብዩ እውነተኛነት አስረጅ አድርጓል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُل لَّوْ شَآءَ ٱللَّهُ مَا تَلَوْتُهُۥ عَلَيْكُمْ وَلَآ أَدْرَىٰكُم بِهِۦ ۖ فَقَدْ لَبِثْتُ فِيكُمْ عُمُرًا مِّن قَبْلِهِۦٓ ۚ أَفَلَا تَعْقِلُونَ (١٦)}[يونس:١٦].

‹‹አላህ በሻ ኖሮ፣በናንተ ላይ ባላነበብኩትም፣(አላህ) እርሱን ባላሳወቃችሁም ነበር፤በናንተም ውስጥ ከርሱ በፊት (ምንም ሳልል) ብዙን እድሜ (አርባ ኣመት) በእርግጥ ኖሬአለሁ፤አታውቁምን?››[ዩኑስ:16]

4. የመልክተኞችን ጥሪ መመልከት፦

ከነብይነት ጠቋሚ ማስረጃዎች መካከል መልክተኛው በጥሪው መሰረታዊ መርሆዎች ላይ ከሁሉም መልክተኞችና ነብዮች መሰረታዊ መርሆዎች ጋር አንድ መሆን አንዱ ነው:: በዚህ መሰረት መልክተኛው ለአላህ (ሱ.ወ.) ተውሒድ (ለአንድነቱ) ጥሪ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል:: ይህም፣አንድነቱን ማረጋገጥና እርሱን ብቻ ማምለክ ሰዎች የተፈጠሩበትና መልክተኞችም የተላኩበት ዐብይ ዓላማ በመሆኑ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِىٓ إِلَيْهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَـٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعْبُدُونِ (٢٥)}[الأنبياء: ٢٥]،

‹‹ከአንተ በፊትም፣እነሆ ከኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጂ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም::››[አል አንቢያእ:25]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَسْـَٔلْ مَنْ أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رُّسُلِنَآ أَجَعَلْنَا مِن دُونِ ٱلرَّحْمَـٰنِ ءَالِهَةً يُعْبَدُونَ (٤٥)}[الزخرف: ٤٥]،

‹‹ከመልክተኞቻችንም ካንተ በፊት የላክናቸውን (ተከታዮቻቸው)፣ ከአልረሕማን ሌላ የሚገዙዋቸው የኾኑን አማልክት አድርገን እንደ ኾነ ጠይቃቸው፤››[አል ዙኽሩፍ:45]

በተጨማሪም እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِى كُلِّ أُمَّةٍ رَّسُولًا أَنِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ وَٱجْتَنِبُوا۟ ٱلطَّـٰغُوتَ ۖ فَمِنْهُم مَّنْ هَدَى ٱللَّهُ وَمِنْهُم مَّنْ حَقَّتْ عَلَيْهِ ٱلضَّلَـٰلَةُ ۚ فَسِيرُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ فَٱنظُرُوا۟ كَيْفَ كَانَ عَـٰقِبَةُ ٱلْمُكَذِّبِينَ (٣٦)}[النحل: ٣٦]،

‹‹በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ፣አላህን ተገዙ፣ጣዖትንም ራቁ፤በማለት መልክተኛን ልከናል፤ከነሱም ውስጥ አላህ ያቀናው ሰው አለ፤ከነሱም ውስጥ በርሱ ላይ ጥመት የተረጋገጠበት ሰው አለ፤በምድርም ላይ ኺዱ፤የአስተባባዮችም መጨረሻ እንዴት እንደ ነበረ ተመልከቱ::››[አል ነሕል:36]

ሙሐመድም ﷺ ለዚህ ነው ጥሪ ያደረጉት:: የአላህ መልክተኛ በወሕይ





## እውነተኛው ክርስትና

‹‹አልመሲሕ በባሰረው መሰረት ወደ ጠራ መሰረቱ ሙሐመድ መመለስ የፈለገው የክርስትና እምነት፣ጳውሎስ ከነዛው ምስጢራዊ ትምሕርቶችና የተለያዩ የክርስትና ጎራዎች በእምነቱ ላይ ካስገቧቸው አስበርጋጊ ስሕተቶች የተለየ ነው:: የሙሐመድ ምኞትና ፍላጎት የአብርሃም ሃይማኖት በረከት በሕዝቦቹ ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የሰውን ዘር በመላ ያቀፈ እንዲሆን ማድረግ ነበር:: ሃይማኖቱ [የሙሐመድ ሃይማኖት] በብዙ ሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሰዎች መመሪያና የስልጣኔ መሰረት መሆን ችሏል:: ይህ ሃይማኖት ባይኖር ኖሮ እነዚህ ሕዝቦች በጭካኔና በአረማዊነት ተውጠው በቀሩ ነበር:: በእስላም ሃይማኖት ውስጥ የሚሰራበት እንዲህ ያለ ወንድማማችነትም ባልኖራቸው ነበር:: ››

ላይትዝ

እንግለዛዊ ኦሪየንታሊስት

(መለኮታዊ ራእይ) ብልጫ አግኝቶ የተከበረ ቢሆንም፣እንደተቀሩት ሰዎች ሁሉ ሰብአዊ ፍጡር ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُوحَىٰٓ إِلَىَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَٰحِدٌ ۖ فَمَن كَانَ يَرْجُوا۟ لِقَآءَ رَبِّهِۦ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَٰلِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِۦٓ أَحَدًۢا ﴿١١٠﴾}[الكهف: ١١٠]،(٥)

‹‹፦ እኔ፣አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው በማለት፣ወደኔ የሚወረድልኝ ቢጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ፤የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፣መልካምን ሥራ ይሥራ፤በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ፣በላቸው::››[አል ከህፍ፡110]

ነቢይ ለግዛትና ለሥልጣን ጥሪ አያደርግም:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُل لَّآ أَقُولُ لَكُمْ عِندِى خَزَآئِنُ ٱللَّهِ وَلَآ أَعْلَمُ ٱلْغَيْبَ وَلَآ أَقُولُ لَكُمْ إِنِّى مَلَكٌ ۖ إِنْ أَتَّبِعُ إِلَّا مَا يُوحَىٰٓ إِلَىَّ ۚ قُلْ هَلْ يَسْتَوِى ٱلْأَعْمَىٰ وَٱلْبَصِيرُ ۚ أَفَلَا تَتَفَكَّرُونَ ﴿٥٠﴾}[الأنعام: 50].

‹‹፦ ለናንተ የአላህ ግምጃ ቤቶች እኔ ዘንድ ናቸው አልልም፤ሩቅንም አላውቅም፤ለናንተም እኔ መልአክ ነኝ አልልም፤ወደኔ የሚወርድልኝን እንጅ ሌላን አልከተልም በላቸው፤ዕውርና የሚያይ ይተካከላሉን? አታስተነትኑምን? በላቸው::››[አል አንዓም፡50]

ለሕዝቡ ለሚያቀርበው ጥሪና ለትምሕርቱም ዋጋ እንዲከፈለው አይጠይቅም:: አላህ (ሱ.ወ.) ነቢዮቹ ኑሕ፣ሁድ፣ሳሊሕ፣ሉጥና ሹዐይብ የተናገሩትን እንዲህ ሲል ገልጾልናል፦

{وَمَآ أَسْـَٔلُكُمْ عَلَيْهِ مِنْ أَجْرٍ ۖ إِنْ أَجْرِىَ إِلَّا عَلَىٰ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿١٠٩﴾}[الشعراء: الآيات: ١٠٩، ١٢٧، ١٤٥، ١٦٤، ١٨٠]

‹‹በርሱም ላይ ምንም ዋጋ አልጠይቃችሁም፤ዋጋዬ በዓለማት ጌታ ላይ እንጅ በሌላ ላይ አይደለም::››[አልሹዐራ፡ 109፣127፣145፣164 እና 180]

ሙሐመድም ﷺ ለሕዝባቸው እንዲህ ብለዋል፦

{قُلْ مَآ أَسْـَٔلُكُمْ عَلَيْهِ مِنْ أَجْرٍ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلْمُتَكَلِّفِينَ ﴿٨٦﴾} [ص: ٨٦]

‹‹በላቸው፦ በርሱ ላይ ምንም ዋጋ አልጠይቃችሁም፤እኔም ከተግደርዳሪዎቹ አይደለሁም::››[ሷድ፡86]

## የእውነት ምስክርነት

‹‹ሙሐመድ አንድም ቀን መለኮታዊ ባህርይን ወይም ተአምራዊ ኃይልን ለራሱ አድርጎ አያውቅም፤በተቃራኒው እግዚአብሔር መልእክቱን ለሰው ልጆች ለማድረስ የላከው መልክተኛ መሆኑን ብቻ በአጽንኦት ይገልጽ ነበር::››



ሮም ላንዶ

እንግለዛዊ ቀራጺና ሐያሲ

5. የአላህ ረድኤትና እገዛ የተሰጣቸው መሆኑ፦

ለነቢያትና መልክተኞች እውነተኛነት ማረጋገጫ ከሆኑት አስረጅዎች አንዱ የአላህ ረድኤትና እገዛ የተቸራቸው መሆኑ ነው:: ይህም አንድ ግለሰብ በውሸት የአላህ ነብይና መልክተኛው ነኝ ብሎ ጥሪው በማሰራጨት ላይ ከአላህ ረድኤት እገዛና ድል ይሰጠዋል ብሎ ማሰብ የማይቻል በመሆኑ ነው:: ይልቅዬ ቁጣና ቅጣት ይወርድበታል ተብሎ ነው የሚጠበቀው!! አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا تَقُولُوا۟ لِمَا تَصِفُ أَلْسِنَتُكُمُ ٱلْكَذِبَ هَٰذَا حَلَٰلٌ وَهَٰذَا حَرَامٌ لِّتَفْتَرُوا۟ عَلَى ٱللَّهِ ٱلْكَذِبَ ۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَفْتَرُونَ عَلَى ٱللَّهِ ٱلْكَذِبَ لَا يُفْلِحُونَ ﴿١١٦﴾}[النحل: ١١٦]،

‹‹በአላህም ላይ ውሸትን ልትቀጣጥፉ፣ምላሶቻችሁ በሚመጥኑት ውሸት፦ ይህ የተፈቀደ ነው፤ይህም እርም ነው፣አትበሉ፤እነዚያ በአላህ ላይ ውሸትን የሚቀጣጥፉ፣አይድኑም::››[አል ነህል፡116]

## ለእግዚአብሔር ፍጹም ሆኖ መተናነስ

‹‹ሙሐመድ የዐረቢያ ባሕረገብ መሪ ቢሆንም ስለግሉ ክብርና ዝና አስቦ አያውቅም:: መሪነቱን ለዝናና ለእውቅና ተጠቅሞም አያውቅም:: የእግዚአብሔር መልክተኛና የሙስሊሞች አገልጋይ በመሆኑ ሁኔታ ብቻ ተወስኖ ነው የቀጠለው:: መኖሪያ ቤቱን ለራሱ ያጸዳ ነበር:: ጫማውንም ለራሱ ያድስ ነበር:: እንደ ተጓዥ ነፋስም ደግና በጣም ቸር ነበር:: ማንም ደሃ ወይም ችግረረኛ ሰው ጠይቆት ያለውን ከመለገስ ቸል ብሎ አያውቅም፤አብዛኛውን ጊዜ ያለው ነገር ለራሱም በቂ ያልሆነ ጥቂት ብቻ ነበር::››

ኤቭሊን ኮቦልድ

እንግሊዛዊት ዘረመሳፍንት

https://www.path-2-happiness.com/am

በተጨማሪም እንዲህ ብሏል፦

{وَلَـوۡ تَقَوَّلَ عَلَيۡنَا بَعۡضَ ٱلۡأَقَاوِيلِ ۝٤٤ لَأَخَذۡنَا مِنۡهُ بِٱلۡيَمِـينِ ۝٤٥ ثُمَّ لَقَطَعۡنَا مِنۡهُ ٱلۡوَتِينَ ۝٤٦}[الحاقة: ٤٤- ٤٦].

‹‹በኛ ላይም ከፊልን ቃላት (ያላልነውን) በቀጠፈ ኖሮ፤በኀይል በያዝነው ነበር:: ከዚያም ከርሱ የልቡን ስር (የተንጠለጠለበትን ጅማት) በቆረጥን ነበር::››[አልሓቃህ:44-46]

## እኔ እንደ እናንተው ሰው እንጂ ሌላ አይደለሁም

‹‹ሙሐመድ በእውነትም የምር ታሪካዊ ግለሰብ ነው:: እርሱ ባይኖር ኖሮ እስላም ሊሰራጭና ሊጨምር ባልቻለ ነበር:: እንደ ተቀሩት ሰዎች ሁሉ ሟች ሰው እንጂ ሌላ አለመሆኑንና ከእግዚአብሔር ይቅርታና ምሕረት የሚለምን መሆኑን በተደጋጋሚ ከመናገር ቦዝኖ አያውቅም:: ከመሞቱ በፊት ሕሊናውን ከማንኛውም ግድፈት ለማጽዳት ፈልጎ ወደ መናገሪያ በመውጣት እንዲህ ነበር ያለው፦ እናንተ ሙስሊሞች ሆይ! ከመካከላችሁ የመታሁት ሰው ካለ ይበቀለኝ ዘንድ ይኸውና ጀርባዬ፤ገንዘብ የነጠቅሁት ሰው ካለም ንብረቴ ንብረቱ ነው::››

ሄንሪ ሲሮያ

ፈረንሳዊ ኦሪየንታሊስት







## የመልክተኞች ጥሪ መሰረታዊ መርሕ

የሁሉም ነቢያትና መልክተኞች ጥሪ በአንድ መሰረታዊ መርሕ ላይ የተመሰረተና የተስማማ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{شَرَعَ لَكُـم مِّنَ ٱلدِّينِ مَا وَصَّىٰ بِـهِۦ نُوحًا وَٱلَّذِيٓ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ وَمَا وَصَّيۡنَـا بِهِۦٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ وَعِيسَىٰٓۖ أَنۡ أَقِيمُواْ ٱلدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُواْ فِيهِ}[الشورى: ١٣]؛

‹‹ለናንተ ከሃይማኖት ያንን ኑሕን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ፤ያንንም ወደ አንተ ያወረድነውን፣ያንንም በርሱ ኢብራሂምን፣ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን፣ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ፤በርሱም አትለያዩ፣ማለትን (ደነገግን)፤በአጋሪዎቹ ላይ ያ ወደርሱ የምትጠራቸው ነገር ከበዳቸው፤አላህ የሚሻውን ሰው ወደርሱ (እምነት) ይመርጣል፤የሚመለስንም ሰው ወደርሱ ይመራል::››[አል ሹራ፡13]

ለዚህም ነው የሁሉም ነቢያት ሃይማኖት አንድ የሆነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَـٰٓأَيُّهَا ٱلرُّسُـلُ كُلُواْ مِنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَٱعۡمَلُواْ صَٰلِحًاۖ إِنِّي بِمَا تَعۡمَلُونَ عَلِيمٞ ۝٥١ وَإِنَّ هَٰذِهِۦٓ أُمَّتُكُمۡ أُمَّةٗ وَٰحِدَةٗ وَأَنَا۠ رَبُّكُمۡ فَٱتَّقُونِ ۝٥٢}[المؤمنون:٥١- ٥٢]،

‹‹እላንተ መልክተኞች ሆይ! ከተፈቀዱት ምግቦች ብሉ፤በጎ ሥራንም ሥሩ፤እኔ የምትሠሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነኝ:: ይህችም፣(በአንድ አምላክ የማመን ሕግጋት)፣አንድ መንገድ ስትኾን፣ሃይማኖታችሁ ናት፤እኔም ጌታችሁ ነኝና ፍሩኝ፤››[አል ሙእሚኑን:51-52]

በዝርዝር ንዑሳን ሕግጋት ግን ሊለያዩ ይችላሉ:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لِكُلّٖ جَعَلۡنَا مِنكُمۡ شِرۡعَةٗ وَمِنۡهَاجٗا}[المائدة: ٤٨]،

‹‹ከናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግን፤›› [አል ማእዳህ:48]

ዝርዝር ሕግጋቱ ከዚያ የጋራ መሰረታዊ መርሕ ጋር የሚጻረር ቢሆን ኖሮ ከጥበብ ከጠቀሜታና ከርህራሄ የራቀ በሆነ ነበር:: ይህ ግን ፈጽሞ ሊሆን የማይችል ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَوِ ٱتَّبَعَ ٱلۡحَقُّ أَهۡوَآءَهُمۡ لَفَسَدَتِ ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلۡأَرۡضُ وَمَن فِيهِنَّ}[المؤمنون: 71].

‹‹አላህም ዝንባሌዎቻቸውን በተከተለ ኖሮ፣ሰማያትና





https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ምድር፣በውስጣቸውም ያለው ሁሉ፣በእርግጥ በተበላሸ ነበር፡፡››[አል ሙእሚኑን፡71]

በመልክተኞችና በትምሕርቶቻቸው ላይ የጋራ ስምምነት ከተደረገባቸው ጉዳዮች መካከል፦

በአላህ፣በመላእክቱ፣በመጽሐፎቹ፣በመልክተኞቹ፣በመጨረሻው ቀንና፣ደጉና ክፉውም በአላህ ዕውቀትና በርሱ ቅድመ ውሳኔ የሚከሰት መሆኑን ማመን ይገኙባቸዋል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ءَامَنَ ٱلرَّسُولُ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيۡهِ مِن رَّبِّهِۦ وَٱلۡمُؤۡمِنُونَۚ كُلٌّ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ لَا نُفَرِّقُ بَيۡنَ أَحَدٖ مِّن رُّسُلِهِۦۚ وَقَالُواْ سَمِعۡنَا وَأَطَعۡنَاۖ غُفۡرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيۡكَ ٱلۡمَصِيرُ ٢٨٥} [البقرة: ٢٨٥].

‹‹መልክተኛው፣ከጌታው ወደርሱ በተወረደው አመነ፤ምእመኖችም (እንደዚሁ)፤ሁሉም በአላህ፣በመላእክቱም፣በመጻሕፍቱም፣በመልክተኞቹም፣ከመልክተኞቹ በአንድም መካከል አንለይም፣(የሚሉ ሲኾኑ) አመኑ፤ሰማን፤ታዘዝንም፤ጌታችን ሆይ! ምሕረትህን (እንሻለን)፤መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው አሉም፡፡››[አል በቀራህ:285]

ሌላው ያለ ምንም ማጋራት አንድ አላህን ብቻ እንዲገዙ ሰዎችን ማዘዝ፣ወዳጅም ሆነ ልጅ ከመያዝ፣ከባላንጣ፣ከአምሳያና ከተጋሪ ሸሪክ እርሱን ማጥራት፤ከጣዖታትና ቅርጻ ቅርጽ አምልኮ መራቅ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِيٓ إِلَيۡهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعۡبُدُونِ ٢٥} [الأنبياء: ٢٥]،

‹‹ካንተ በፊትም፣እነሆ ከኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም፡፡››[አል አንቢያ:25]

እንደዚሁም የአላህን መንገድ ብቻ መከተል፣ከርሱ የሚጻረሩ መንገዶችን አለመከተል፣ቃል ኪዳንን ማክበር፣መስፈሪያና ሚዛንን አለማጉደል፣ለወላጆች ደግ መሆን፣ለሰዎች ሁሉ ፍትሐዊ መሆን፣በቃልና በተግባርም እውነተኛ መሆን፣ግልጹንም ሆነ ስውሩን ዝሙት እርም ማድረግ፣ሕጻናትን መግደልና ነፍስን ያለ ሕግ አግባብ ማጥፋትን እርም ማድረግ፣አራጣና የየቲሞችን (ወላጅ አልባዎች) ገንዘብ መብላትን መከልከል፣ማባከንን፣መኩራትንና የሰውን ገንዘብ በሐሰት መብላትን መከልከል ይገኙበታል።

በመጨረሻው ቀን ማመን፤እያንዳንዱ ሰው ከዕለታት አንድ ቀን እንደሚሞት በእርግጠኝነት ያውቃል። ይሁንና ከሞት በኋላ መጨረሻው ምን ይሆናል? ጽድቅ ወይስ ኩነኔ? ከሞት ተቀስቅሰው የየሥራቸውን ዋጋ በጎ ከሆነ በጎ፣ክፉ ከሆነ ክፉ ዋጋ እንደሚቀበሉ፣ሁሉም መልክተኞችና ነቢያት ለሕዝቦቻቸው አስተምረዋል። ይህን ጉዳይ - ከሞት በኋላ መቀስቀስና በሠሩት ሥራ መጠየቅን - አመዛዛኝ አእምሮ የሚያረጋግጠውና መለኮታዊ ሃይማኖቶች ያጸኑት እውነታ ነው። ኃያሉ ጥበበኛው ዐዋቂው ፈጣሪ ይህን ፍጥረት እንዳው ለከንቱ ፈጥሮ ከመተው የላቀና የጠራ አምላክ ነውና። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَا خَلَقۡنَا ٱلسَّمَآءَ وَٱلۡأَرۡضَ وَمَا بَيۡنَهُمَا بَٰطِلٗاۚ ذَٰلِكَ ظَنُّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْۚ فَوَيۡلٞ لِّلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنَ



ٱلنَّارِ ٢٧} [ص: ٢٧]،

‹‹ሰማይንና ምድርን፣በመካከላቸውም ያለውን ሁሉ፣ለከንቱ አልፈጠርንም፤ይህ የነዚያ የካዱት ሰዎች ጥርጣሬ ነው፤ለነዚያም ለካዱት ሰዎች ከእሳት ወየውላቸው፡፡››[ሷድ:27]

ይልቁዬ ይህን ድንቅ ፍጥረት የፈጠረው ለታላቅ ጥበብና ለክቡር ዓላማ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَا خَلَقۡتُ ٱلۡجِنَّ وَٱلۡإِنسَ إِلَّا لِيَعۡبُدُونِ ٥٦} [الذاريات: ٥٦]،

‹‹ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡››[አል ዛርያት:56]

ታዛዡንና አመጸኛውን እኩል ማስተናገድም ለዚህ ጥበበኛ ኃያል አምላክ የተገባ አይደለም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَمۡ نَجۡعَلُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ كَٱلۡمُفۡسِدِينَ فِي ٱلۡأَرۡضِ أَمۡ نَجۡعَلُ ٱلۡمُتَّقِينَ كَٱلۡفُجَّارِ ٢٨} [ص: ٢٨]؛

‹‹በውነቱ እነዚያን ያመኑትንና መልካሞችን የሠሩትን፣በምድር ውስጥ እንደሚያጠፉት እናደርጋለን?! ወይስ አላህን ፈሪዎቹን እንደ ከሓዲዎቹ እናደርጋለን?››[ሷድ:28]

ስለዚህም ፍጥረታትን በትንሣኤ ቀን ከሞት ቀስቅሶ ለያንዳንን ሰው እንደሥራው በመስጠት በጎ ሠሪውን መሸለምና ክፉ ሠሪውን መቅጣት፤የጥበቡ ምሉእነትና የችሎታው ኃያልነት መገለጫ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لِيَجۡزِيَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ بِٱلۡقِسۡطِۚ وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَهُمۡ شَرَابٞ مِّنۡ حَمِيمٖ وَعَذَابٌ أَلِيمُۢ بِمَا كَانُواْ يَكۡفُرُونَ ٤} [يونس: ٤]؛

‹‹ከዚያም እነዚያን ያመኑትንና መልካም የሠሩትን በትክክል ይመነዳ ዘንድ ይመልሰዋል፤እነዚያ የካዱትም፣ይክዱት በነበሩት ነገር ለነርሱ ከፈላ ውሃ የኾነ መጠጥና አሳማሚ ቅጣት አላቸው፡፡›› [ዩኑስ:4]

## የጠራ ስረ መሰረት

‹‹እስላም ከሙሐመድ ዘንድ የሆነ አዲስ ሃይማኖት አይደለም። አልመሲሕ [የአላህ ሰላም በርሱ ላይ ይሁን] ወደ ሰማይ ካረገ ከስድስት መቶ ዓመት በኋላ ምድር ላይ በተሰራጨ ጊዜ ቀደም ሲል በነበሩት መለኮታዊ ሃይማኖቶች ውስጥ የሰፈረውን መለኮታዊ ራእይ ዳግም አሰራጨ፤ወደ ጠራ ጥንታዊ ስረ መሰረቱም መለሰው። እግዚአብሔር የላካቸው ነቢያት ሁሉ መስሊሞች ነበሩ፤መልክቶቻቸውም ሁሌም አንድ ነበሩ፡፡››

ዲቦራ ቦተር
በአሜሪካ የሚታተም ጋዜጣ





https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

እናም ከሞቱ በኋላ ሰዎችን ዳግም መቀስቀስ ለርሱ እጅግ ቀላል ነው:: ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ እርሱ አይደለምን? ዩኒቨርሱን በመላ ያለ ምንም ቅድመ አምሳያ ከምንም ከፈጠረ፣ይህንኑ መልሶ እንደገና ማምጣት ከዚያ የቀለለ መሆኑ አያጠያይቅም! አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَوَ لَمۡ يَرَوۡاْ أَنَّ ٱللَّهَ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَلَمۡ يَعۡيَ بِخَلۡقِهِنَّ بِقَٰدِرٍ عَلَىٰٓ أَن يُحۡـِۧيَ ٱلۡمَوۡتَىٰۚ بَلَىٰٓۚ إِنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ﴿٣٣﴾}[الأحقاف: ٣٣]

‹‹ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ፣እነርሱንም በመፍጠሩ ያልደከመው አላህ፣ሙታንን ሕያው በማድረግ ላይ ቻይ መኾኑን አላስተዋሉምን? (በማስነሳት) ቻይ ነው:: እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና::››[አል አሕቃፍ:33]

በተጨማሪም እንዲህ ብሏል፦

{أَوَ لَيۡسَ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ بِقَٰدِرٍ عَلَىٰٓ أَن يَخۡلُقَ مِثۡلَهُمۚ بَلَىٰ وَهُوَ ٱلۡخَلَّٰقُ ٱلۡعَلِيمُ ﴿٨١﴾}[يس: ٨١]؛

‹‹ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ፣ብጤያቸውን በመፍጠር ላይ ቻይ አይደለምን? ነው እንጅ፣እርሱም በብዙ ፈጣሪው፣ዐዋቂው ነው::››[ያሲን:81]

ያልነበረውን ማስገኘት የሚችል የነበረውን መልሶ ማስገኘቱ ለርሱ በጣም ቀላል ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَهُوَ ٱلَّذِي يَبۡدَؤُاْ ٱلۡخَلۡقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ وَهُوَ أَهۡوَنُ عَلَيۡهِۚ وَلَهُ ٱلۡمَثَلُ ٱلۡأَعۡلَىٰ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ﴿٢٧﴾}[الروم: ٢٧]؛

‹‹እርሱም ያ መፍጠርንየሚጀምር፣ከዚያም የሚመልሰው ነው፣(መመለሱ)(7)በርሱ ላይ በጣም ገር ነው፣ለርሱም በሰማያትም በምድርም ከፍተኛ ባሕርይ (አንደነትና ለርሱ ብጤ የሌለው መኾን) አልለው፣እርሱም አሸናፊ ጥበበኛ ነው::››[አል ሩም:27]

ይልቅዬም በዚችው ዓለማዊ ሕይወት በነቢዩ ኢብራሂም [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] ፊት በአላህ ፈቃድ ሙታንን ከሞት ማስነሳት ተፈጽሟል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذۡ قَالَ إِبۡرَٰهِـۧمُ رَبِّ أَرِنِي كَيۡفَ تُحۡيِ ٱلۡمَوۡتَىٰۖ قَالَ أَوَ لَمۡ تُؤۡمِنۖ قَالَ بَلَىٰ وَلَٰكِن لِّيَطۡمَئِنَّ قَلۡبِيۖ قَالَ فَخُذۡ أَرۡبَعَةٗ مِّنَ ٱلطَّيۡرِ فَصُرۡهُنَّ إِلَيۡكَ ثُمَّ ٱجۡعَلۡ عَلَىٰ كُلِّ جَبَلٖ مِّنۡهُنَّ جُزۡءٗا ثُمَّ ٱدۡعُهُنَّ يَأۡتِينَكَ سَعۡيٗاۚ وَٱعۡلَمۡ أَنَّ ٱللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٞ ﴿٢٦٠﴾}[البقرة: ٢٦٠]،

‹‹ኢብራሂምም ጌታዬ ሆይ! ሙታንን እንዴት ሕያው እንደምታደርግ አሳየኝ ባለ ጊዜ፣(አስታውስ፣አላህ)፦ አላመንክምን? አለው፣አይደለም (አምኛለሁ)፣ግን ልቤ እንዲረጋ ነው አለ፣(አላህም)፦ ከበራሪዎች (ከወፎች) አራትን ያዝ፣ወደ አንተም ሰብስባቸው፣(ቆራርጣቸውም)፣ከዚያም በየኮረብታው ሁሉ ላይ ከነርሱ ቁራጭን አድርግ፣ከዚያም ጥራቸው፣ፈጥነው ይመጡሃልና፣አላህም አሸናፊ፣ጥበበኛ መኾኑን ዕወቅ አለው::››[አል በቀራህ:260]

በአልመሲሕ ዒሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] እጅም እንደዚሁ በአላህ ፈቃድ ተፈጽሟል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِذۡ قَالَ ٱللَّهُ يَٰعِيسَى ٱبۡنَ مَرۡيَمَ ٱذۡكُرۡ نِعۡمَتِي عَلَيۡكَ وَعَلَىٰ وَٰلِدَتِكَ إِذۡ أَيَّدتُّكَ بِرُوحِ ٱلۡقُدُسِ تُكَلِّمُ ٱلنَّاسَ فِي ٱلۡمَهۡدِ وَكَهۡلٗاۖ وَإِذۡ عَلَّمۡتُكَ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ وَٱلتَّوۡرَىٰةَ وَٱلۡإِنجِيلَۖ وَإِذۡ تَخۡلُقُ مِنَ ٱلطِّينِ كَهَيۡـَٔةِ ٱلطَّيۡرِ بِإِذۡنِي فَتَنفُخُ فِيهَا فَتَكُونُ طَيۡرَۢا بِإِذۡنِيۖ وَتُبۡرِئُ ٱلۡأَكۡمَهَ وَٱلۡأَبۡرَصَ بِإِذۡنِيۖ وَإِذۡ تُخۡرِجُ ٱلۡمَوۡتَىٰ بِإِذۡنِيۖ وَإِذۡ كَفَفۡتُ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ عَنكَ إِذۡ جِئۡتَهُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِ فَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنۡهُمۡ إِنۡ هَٰذَآ إِلَّا سِحۡرٞ مُّبِينٞ ﴿١١٠﴾}[المائدة: ١١٠].

‹‹አላህ በሚል ጊዜ (አስታውስ)፦ የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! በአንተና በእናትህ ላይ (የዋልኩላችሁን) ጸጋዬን አስታውስ፣በሕፃንነትና በከፈኒሳነት (የበሰለ ሰው ኾነህ) ሰዎችን የምትናገር ስትኾን፣በቅዱሱ መንፈስ (በገብርኤል) ባበረታሁህ ጊዜ፣ጽሕፈትንና ጥበብንም፣ተውራትንና ኢንጂልንም፣ባስተማርኩህ ጊዜ፣ከጭቃም የወፍ ቅርጽ ብጤ በፈቃዴ በምትሠራና በውስጧ በምትነፋ፣በፈቃዴም ወፍ በምትኾን ጊዜ፣ዕውርም ኾኖ የተወለደንና ለምጻምንም በፈቃዴ በምታሽር ጊዜ፣ሙታንንም በፈቃዴ (ከመቃብራቸው) በምታወጣ ጊዜ፣የእስራኤልንም ልጆች በተአምራት በመጣህባቸውና ከነሱ እነዚያ የካዱት ይህ ግልጽ ድግምት እንጅ ሌላ አይደለም ባሉ ጊዜ፣(ሊገድሉህ ሲያስቡህ) ከአንተ ላይ በከለከልኩልህም ጊዜ፣(ያደረግሁልህን ውለታ አስታውስ)::››[አልማእዳህ:110]

## እውነተኛው ተውሒድ

‹‹ዐረባዊው ነቢይ ሙሐመድ ከጌታው ጋር ባለው ጥልቅ ትስስር አንቂ በሆነ ድምጽ ነው ጥሪ ያደረገው:: ጣዖታት አምላኪዎችን፣የተዛነፉና የተበረዙ የክርስትና እና የአይሁድ እምነቶች ተከታዮችንም ወደ ጠራ እውነተኛው የተውሒድ (የአንድ አምላክ አምልኮ) እምነት ጠራ:: የሰውን ልጅ ከአንድ ፈጣሪ አምላክ ጋር ባዕድ አማልክትን እንዲያመልክ በሚያደርጉ ኋላ ቀር አዝማሚዎች ላይ ግልጽ ተጋድሎ ማድረግንም ምርጫው አደረገ::››



ሎራ ፊሽያ ቫግሌሪ

ጣሊያናዊት ኦሪየንታሊስት



## የጽናትና የቁርጠኝነት ባለቤቶች ከሆኑ መልክተኞች ታሪክ በጨረፍታ

ሰዎች መጀመሪያ ላይ በንጹሕ ተፈጥሯቸው በትክክለኛው መንገድ ላይ የነበሩ ሲሆን፣በኋላ ተለያዩና ያስተምሯቸውና ያሰጠነቅቋቸው ዘንድ አላህ መልክተኞቹን ላከላቸው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ ٱلَّذِى بَعَثَ فِى ٱلْأُمِّيِّـۧنَ رَسُولًا مِّنْهُمْ يَتْلُوا۟ عَلَيْهِمْ ءَايَـٰتِهِۦ وَيُزَكِّيهِمْ وَيُعَلِّمُهُمُ ٱلْكِتَـٰبَ وَٱلْحِكْمَةَ وَإِن كَانُوا۟ مِن قَبْلُ لَفِى ضَلَـٰلٍ مُّبِينٍ ﴿٢﴾}[الجمعة: ٢]،

‹‹እርሱ ያ በመሃይሞች ውስጥ አንቀጾቹን (ቁርአንን)፣በነርሱ ላይ የሚያነብላቸው፣(ከማጋራት) የሚያጠራቸውም፣መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸው የኾነን መልክተኛ (ሙሐመድን) ከነሱው ውስጥ የላከ ነው፤እነርሱም ከርሱ በፊት በግልጽ ስሕተት ውስጥ ነበሩ::››[አል ጁሙዓ:2]

ሰዎች ግን የመልክተኞቹን ጥሪና ትምህርት በተመለከተ በሁለት ጎራ ተከፋፈሉ:: አንደኛው ጎራ መልክተኞቹን አምኖ ሲቀበላቸው፣ሌላኛው ጎራ ደግሞ መልክተኞቹን አስተባብሎ በነርሱና ይዘውት በመጡት ጥሪም ካደ:: አላህ (ሱ.ወ.) ይህን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፦

{كَانَ ٱلنَّاسُ أُمَّةً وَٰحِدَةً فَبَعَثَ ٱللَّهُ ٱلنَّبِيِّـۧنَ مُبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ وَأَنزَلَ مَعَهُمُ ٱلْكِتَـٰبَ بِٱلْحَقِّ لِيَحْكُمَ بَيْنَ ٱلنَّاسِ فِيمَا ٱخْتَلَفُوا۟ فِيهِ ۚ وَمَا ٱخْتَلَفَ فِيهِ إِلَّا ٱلَّذِينَ أُوتُوهُ مِنۢ بَعْدِ مَا جَآءَتْهُمُ ٱلْبَيِّنَـٰتُ بَغْيًۢا بَيْنَهُمْ ۖ فَهَدَى ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لِمَا ٱخْتَلَفُوا۟ فِيهِ مِنَ ٱلْحَقِّ بِإِذْنِهِۦ ۗ وَٱللَّهُ يَهْدِى مَن يَشَآءُ إِلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ ﴿٢١٣﴾}[البقرة: ٢١٣]،

‹‹ሰዎች ሁሉ አንድ ሕዝብ ነበሩ፤(ተለያዩ)፤አላህም ነቢያትን አብሳሪዎችና አስጠንቃቂዎች አድርጎ ላከ፤ከነርሱም ጋር መጻሕፍትን በሰዎች መካከል በዚያ በተለያዩበት ነገር ይፈርድ ዘንድ በእውነት አወረደ፤በርሱም (በሃይማኖት) ግልጽ አስረጂዎች ከመጡላቸው በኋላ በመካከላቸው ለኾነው ምቀኝነት እነዚያው የተሰጡት እንጅ አልተለያዩበትም፤አላህም እነዚያን ያመኑትን ሰዎች፣ለዚያ ከውነት በርሱ ለተለያዩበት በፈቃዱ መራቸው፤አላህም የሚሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል::››[አል በቀራህ:213]

ያስተባበሏቸውና የካዱትም በትዕቢትና ዝንባሌዎቻቸውን በመከተል ነበር:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَفَكُلَّمَا جَآءَكُمْ رَسُولٌۢ بِمَا لَا تَهْوَىٰٓ أَنفُسُكُمُ ٱسْتَكْبَرْتُمْ فَفَرِيقًا كَذَّبْتُمْ وَفَرِيقًا تَقْتُلُونَ ﴿٨٧﴾}[البقرة: ٨٧].

‹‹ነፍሶቻችሁ በማትወደው ነገር መልክተኛ በመጣላችሁ ቁጥር (ከመከተል) ትኮራላችሁን? ከፊሉን አስተባበላችሁ፤ከፊሉንም ትገድላላችሁ::››[አል በቀራህ:87]

አንዱን ከሌላው ሳይለዩ በሁሉም አላህ መልክተኞችና ነቢያት ማመንን አላህ (ሱ.ወ.) ግዴታ አድርጎ አዟል፦

{قُولُوٓا۟ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَمَآ أُنزِلَ إِلَيْنَا وَمَآ أُنزِلَ إِلَىٰٓ إِبْرَٰهِـۧمَ وَإِسْمَـٰعِيلَ وَإِسْحَـٰقَ وَيَعْقُوبَ وَٱلْأَسْبَاطِ وَمَآ أُوتِىَ مُوسَىٰ وَعِيسَىٰ وَمَآ أُوتِىَ ٱلنَّبِيُّونَ مِن رَّبِّهِمْ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّنْهُمْ وَنَحْنُ لَهُۥ مُسْلِمُونَ ﴿١٣٦﴾}[البقرة: ١٣٦]،

‹‹በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን)፣ወደ ኢብራሂምም፣ወደ እስማዒልና ወደ ኢስሐቅም፣ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው፣በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት፣በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት፣ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን በሉ::››[አል በቀራህ: 136

በመልክተኞች ላመኑት በዛሬዋ ዓለማዊ ሕይወትና በወዲያኛው ዘላለማዊ ሕይወት ተድላና ድልን ሊያጎናጽፍ አላህ ቃል ገብቷል:: ስለ አመኑ ሰዎች ሲናገርም እንዲህ ብሏል፦

{وَمَن يَتَوَلَّ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ فَإِنَّ حِزْبَ ٱللَّهِ هُمُ ٱلْغَـٰلِبُونَ ﴿٥٦﴾}[المائدة: ٥٦]،

‹‹አላህንና መልክተኛውን፣እነዚያንም ያመኑትን የሚወዳጅ ሰው፣(ከአላህ ጭፍሮች ይኾናል)፤የአላህም ጭፍሮች እነርሱ አሸናፊዎች ናቸው::›› [አል ማእዳህ:56]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَتَطْمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكْرِ ٱللَّهِ ۗ أَلَا بِذِكْرِ ٱللَّهِ تَطْمَئِنُّ ٱلْقُلُوبُ ﴿٢٨﴾}[الرعد: ٢٨]

‹‹(እነሱም) እነዚያ ያመኑ፣ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው፤ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ:: እነዚያ ያመኑትና መልካም ሥራዎችን የሠሩት፣ለነሱ ደግ ኑሮ መልካም መመለሻም አላቸው::››[አል ረዕድ: 28]

በመልክተኞቹ የካዱትን አስመልክቶም እንዲህ ብሏል፦

{لَا تَحْسَبَنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ مُعْجِزِينَ فِى ٱلْأَرْضِ ۚ وَمَأْوَىٰهُمُ ٱلنَّارُ ۖ وَلَبِئْسَ ٱلْمَصِيرُ ﴿٥٧﴾}[النور: ٥٧].

‹‹እነዚያን የካዱትን በምድር ውስጥ የሚያቅቱ አድርገህ አታስብ፤መኖሪያቸውም እሳት ናት፤በእርግጥም የከፋች መመለሻ ናት::››[አል ኑር:57]

እያንዳንዱ ነቢይም ጠላቶች ነበሩት:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَكَذَٰلِكَ جَعَلْنَا لِكُلِّ نَبِىٍّ عَدُوًّا شَيَـٰطِينَ ٱلْإِنسِ وَٱلْجِنِّ يُوحِى بَعْضُهُمْ إِلَىٰ بَعْضٍ زُخْرُفَ ٱلْقَوْلِ غُرُورًا ۚ وَلَوْ شَآءَ رَبُّكَ مَا فَعَلُوهُ ۖ فَذَرْهُمْ وَمَا يَفْتَرُونَ ﴿١١٢﴾}[الأنعام: ١١٢]،

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am



‹‹እንደዚሁም ለነቢዩ ሁሉ ከሰውና ከጋኔን የኾኑን ሰይጣናት ጠላት አደረግን፤ከፊላቸው ወደ ከፊሉ ለማታለል ልብስብስን ቃል ይጥላሉ፤ጌታህም በሻ ኖሮ ባልሠሩት ነበር። ከቅጥፈታቸውም ጋር ተዋቸው።፡››[አል አንዓም፡ 112]

በተጨማሪም ከሓዲዎቹ አስተባባዮች በነቢዮቻቸው ላይ ድንበር አለፉ፤ጥቃት ሰነዘሩባቸው፤ተሳለቁባቸው፣መዘባበቻም አደረጓቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَا يَأْتِيهِم مِّن رَّسُولٍ إِلَّا كَانُوا بِهِۦ يَسْتَهْزِءُونَ ﴿١١﴾}[الحجر: ١١]،

‹‹ማንኛውም መልክተኛ በርሱ የሚያላግጡበት ኾነው እንጅ አይመጣቸውም ነበር።፡››[አል ሕጅር፡11]

በተጨማሪም አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَمَا يَأْتِيهِم مِّن نَّبِيٍّ إِلَّا كَانُوا بِهِۦ يَسْتَهْزِءُونَ ﴿٧﴾}[الزخرف: ٧]،

‹‹ከነቢይም አንድም የሚመጣላቸው አልነበረም፣በርሱ ይሳለቁበት የነበሩ ቢኾን እንጅ።፡››[አል ዙኽሩፍ፡7]

በተጨማሪም እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدِ اسْتُهْزِئَ بِرُسُلٍ مِّن قَبْلِكَ فَحَاقَ بِالَّذِينَ سَخِرُوا مِنْهُم مَّا كَانُوا بِهِۦ يَسْتَهْزِءُونَ ﴿١٠﴾}[الأنعام: ١٠]،

‹‹ካንተ በፊትም በመልክተኞች በእርግጥ ተላግጧል፤በነዚያም ከነሱ ባላገጡት ላይ በርሱ ያላግጡ የነበሩት ነገር (ቅጣት) ወረደባቸው።፡››[አል አንዓም፡10]

ሃማኖታቸውን እንዲተው ካልተው ግን ከአገር ለማስወጣትም ዛቱባቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَقَالَ الَّذِينَ كَفَرُوا لِرُسُلِهِمْ لَنُخْرِجَنَّكُم مِّنْ أَرْضِنَا أَوْ لَتَعُودُنَّ فِي مِلَّتِنَا فَأَوْحَىٰ إِلَيْهِمْ رَبُّهُمْ لَنُهْلِكَنَّ الظَّالِمِينَ ﴿١٣﴾}[إبراهيم: ١٣]،

‹‹እነዚም የካዱት፣ለመለክተኞቻቸው፦ ከምድራችን በእርግጥ እናወጣችኋለን፤ወይም ወደ ሃማኖታችን በእርግጥ ትመለሳላችሁ፣አሉ፤ወደነርሱም ጌታቸው እንዲህ ሲል ላከ፦ ከሓዲዎችን በእርግጥ እናጠፋለን። ››[ኢብራሂም፡13]

ማስጠንቀቂያው እስከ የመግደል ሙከራ ደርሷል፦

‹‹ሕዝቦችም ሁሉ መልክተኛቸውን ልይዙ አሰቡ››[አል ሙእሚ፡5]

ይህም መልክተኞቻቸውንና ነቢዮቻቸውን ለመግደል አሰቡ ማለት ሲሆን፣ነቢዮችን የገደሉ ሕዝቦችም ይገኛሉ፦



{أَفَكُلَّمَا جَاءَكُمْ رَسُولٌ بِمَا لَا تَهْوَىٰ أَنفُسُكُمُ اسْتَكْبَرْتُمْ فَفَرِيقًا كَذَّبْتُمْ وَفَرِيقًا تَقْتُلُونَ ﴿٨٧﴾}[البقرة: ٨٧]،

‹‹ነፍሶቻችሁ በማትወደው ነገር መልክተኛ በመጣላችሁ ቁጥር (ከመከተል) ትኮራላችሁን? ከፊሉን አስተባበላችሁ፤ከፊሉንም ትገድላላችሁ።፡››[አልበቀራህ፡87]

ከዚያ በኋላ ግን አላህ አስተባባዮቹን ከሓዲዎች አጠፉ። የመልክተኞቹን ጥሪም ይፋ አደረገ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{كَتَبَ اللَّهُ لَأَغْلِبَنَّ أَنَا وَرُسُلِي ۚ إِنَّ اللَّهَ قَوِيٌّ عَزِيزٌ ﴿٢١﴾}[المجادلة: ٢١]،

‹‹አላህ ፦ እኔ በእርግጥ አሸንፋለሁ፤መልክተኞቹም (ያሸንፋሉ ሲል) ጽፏል። አላህ ብርቱ፣አሸናፊ ነውና።፡››[አል ሙጃደላህ፡21]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدْ سَبَقَتْ كَلِمَتُنَا لِعِبَادِنَا الْمُرْسَلِينَ ﴿١٧١﴾ إِنَّهُمْ لَهُمُ الْمَنصُورُونَ ﴿١٧٢﴾}[الصافات: ١٧١- ١٧٢]،

‹‹(የርዳታ) ቃላችንም፣መልክተኞች ለኾኑት ባሮቻችን በውነት አልፋለች። እነርሱ ተረጂዎቹ እነርሱ ናቸው።፡››[አል ሷፋት፡171-172]

አላህም መልክተኞቹንና ነቢዮቹን [የአላህ ሰላም በሁሉም ላይ ይሁን] ከከሓዲዎች ተንኮል አዳናቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَأَنجَيْنَا الَّذِينَ آمَنُوا وَكَانُوا يَتَّقُونَ ﴿٥٣﴾}[النمل: ٥٣]،

‹‹እነዚያንም ያመኑትንና ከክሕደት ይጠነቀቁ የነበሩትን አዳን።፡››[አል ነምል፡53]

በተጨማሪም እንዲህ ብሏል፦

{وَنَجَّيْنَا الَّذِينَ آمَنُوا وَكَانُوا يَتَّقُونَ ﴿١٨﴾}[فصلت: ١٨]

‹‹እነዚያንም ያመኑትንና ይጠነቀቁ የነበሩትን አዳንናቸው።፡››[ሓ ሚም አልሰጅዳህ፡18]

እያንዳንዱ ነቢይ የተላከው ለራሱ ሕዝብና ለራሱ ዘመን፣ሕይወታቸውን ለመግራትና ባህርቸውን ለማረቅ ተስማሚ የሆነ መልክት ይዞ ነው። በአንድ መልክተኛ የካደ ሰው በሁሉም የአላህ መልክተኞች እንደ ካደና እንዳስተባበለ ይቆጠራል። በዒሳ [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] የካደ ሰው፣በእርግጥ በሙሳም [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] አላመነም።



ማርሴል ቦዋዛር
ፈረንሳዊ አሳቢ

### ከአንድ ምንጭ የተቀዱ

‹‹ቀደም ሲል የተላለፉትን ውድቅ ማድረግ በሙሐመድ መልክት ውስጥ አልተካተተም፤ይልቅዬ በመለኮታዊ መጽሐፎች ላይ የተፈጸመውን የማዛባትና የመከለስ አደጋ በመኮነን በትክክለኛ ስረመሰረታቸው ያረጋግጣቸዋል። የቀደምት መልክተኞችን ትምሕርቶች ለመላው የሰው ዘር በሁሉም ዘመንና ስፍራ የተመቹ ይሆኑ ዘንድ፣ከደረሰባቸው የማጣመምና የማዛባት ችግር የማጥራት፣የማስፋትና ምሉእ እንዲሆኑ የማድረግ ተልእኮንም ተወጥቷል።፡››

https://www.path-2-happiness.com/am

የሙሐመድ ﷺ መልክት የዒሳን عليه السلام መልክት ሽሯል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَأَنزَلْنَآ إِلَيْكَ ٱلْكِتَٰبَ بِٱلْحَقِّ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ ٱلْكِتَٰبِ وَمُهَيْمِنًا عَلَيْهِ ۖ فَٱحْكُم بَيْنَهُم بِمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ ۖ وَلَا تَتَّبِعْ أَهْوَآءَهُمْ عَمَّا جَآءَكَ مِنَ ٱلْحَقِّ}[المائدة: ٤٨]،

‹‹ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በውነት አወረድን፤በመካከላቸውም፣አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ፤እውነቱም ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል::››[አል ማእዳህ፡ 48]

በሙሐመድ ﷺ ያላመነ ሰውም በዒሳ عليه السلام መልክት በትክክል አላመነም::

የነቢያትና የመልክተኞች የመደምደሚያ መልክትና ጥሪ፣ለሁሉም ሕዝቦችና ለሁሉም ዘመን እንጅ ለተወሰነ ዘመን ወይም ለተለየ አንድ ሕዝብ አለመሆኑ ግድ ነው:: ያ ባይሆን ኖሮ የሰው ልጅ ከሰማያትና ምድር ፈጣሪ የሚተላለፍለትን የመለኮታዊ ራእይ ትሩፋት ባጣ ነበር:: ሙሐመድም ﷺ የነቢያትና የመልክተኞች መደምደሚያና የመቋጫ ጉልላት ናቸው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَآ أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ ٱللَّهِ وَخَاتَمَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمًا ﴿٤٠﴾}[الأحزاب: ٤٠]

‹‹ሙሐመድ፣ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፤ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፤አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው::››[አል አሕዛብ:40]







ለመሆኑ የሰው ልጆች ታሪክ አስኳል የሆነው የነቢዮችና የመልክተኞች ታሪክ ምንድነው?

**አንዱን ከሌላው ሳንለይ በሁሉም እናምናለን**

‹‹ቅዱስ ቁርኣን ለተቀሩት መለኮታዊ መጻሕት ሁሉ ዕውቅና የሚሰጥ ብቸኛው መጽሐፍ ነው:: ሌሎቹ ግን ሁሉም አንዱ ሌላውን ዕውቅና ሲነሳና ሲቃወም እናያለን::›



በሺር ሻድ ሕንዳዊ ሰባኪ.

አላህ (ሱ.ወ.) ሰውን መፍጠር ከፈለገበት ጊዜ ጀምሮ ኣደምን ከጀነት እስከ አወጣበትና ወደ መሬት እስከ አወረደበት ባለው እንጀምራለን:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَٰٓئِكَةِ إِنِّى جَاعِلٌ فِى ٱلْأَرْضِ خَلِيفَةً ۖ قَالُوٓا۟ أَتَجْعَلُ فِيهَا مَن يُفْسِدُ فِيهَا وَيَسْفِكُ ٱلدِّمَآءَ وَنَحْنُ نُسَبِّحُ بِحَمْدِكَ وَنُقَدِّسُ لَكَ ۖ قَالَ إِنِّىٓ أَعْلَمُ مَا لَا تَعْلَمُونَ ﴿٣٠﴾ وَعَلَّمَ ءَادَمَ ٱلْأَسْمَآءَ كُلَّهَا ثُمَّ عَرَضَهُمْ عَلَى ٱلْمَلَٰٓئِكَةِ فَقَالَ أَنۢبِـُٔونِى بِأَسْمَآءِ هَٰٓؤُلَآءِ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ﴿٣١﴾ قَالُوا۟ سُبْحَٰنَكَ لَا عِلْمَ لَنَآ إِلَّا مَا عَلَّمْتَنَآ ۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلْعَلِيمُ ٱلْحَكِيمُ ﴿٣٢﴾ قَالَ يَٰٓـَٔادَمُ أَنۢبِئْهُم بِأَسْمَآئِهِمْ ۖ فَلَمَّآ أَنۢبَأَهُم بِأَسْمَآئِهِمْ قَالَ أَلَمْ أَقُل لَّكُمْ إِنِّىٓ أَعْلَمُ غَيْبَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَأَعْلَمُ مَا تُبْدُونَ وَمَا كُنتُمْ تَكْتُمُونَ ﴿٣٣﴾ وَإِذْ قُلْنَا لِلْمَلَٰٓئِكَةِ ٱسْجُدُوا۟ لِـَٔادَمَ فَسَجَدُوٓا۟ إِلَّآ إِبْلِيسَ أَبَىٰ وَٱسْتَكْبَرَ وَكَانَ مِنَ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٣٤﴾ وَقُلْنَا يَٰٓـَٔادَمُ ٱسْكُنْ أَنتَ وَزَوْجُكَ ٱلْجَنَّةَ وَكُلَا مِنْهَا رَغَدًا حَيْثُ شِئْتُمَا وَلَا تَقْرَبَا هَٰذِهِ ٱلشَّجَرَةَ فَتَكُونَا مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٣٥﴾ فَأَزَلَّهُمَا ٱلشَّيْطَٰنُ عَنْهَا فَأَخْرَجَهُمَا مِمَّا كَانَا فِيهِ ۖ وَقُلْنَا ٱهْبِطُوا۟ بَعْضُكُمْ لِبَعْضٍ عَدُوٌّ ۖ وَلَكُمْ فِى ٱلْأَرْضِ مُسْتَقَرٌّ وَمَتَٰعٌ إِلَىٰ حِينٍ ﴿٣٦﴾ فَتَلَقَّىٰٓ ءَادَمُ مِن رَّبِّهِۦ كَلِمَٰتٍ فَتَابَ عَلَيْهِ ۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلتَّوَّابُ ٱلرَّحِيمُ ﴿٣٧﴾ قُلْنَا ٱهْبِطُوا۟ مِنْهَا جَمِيعًا ۖ فَإِمَّا يَأْتِيَنَّكُم مِّنِّى هُدًى فَمَن تَبِعَ هُدَاىَ فَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ ﴿٣٨﴾ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ وَكَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَآ أُو۟لَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ ٱلنَّارِ ۖ هُمْ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿٣٩﴾}[البقرة: ٣٠- ٣٩].

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ለመላእክት ፦ እኔ በምድር ላይ ምትክን አድራጊ ነኝ፤ ባለ ጊዜ፣(የኾነውን አስታውስ፤እነርሱም) እኛ ከማመስገን ጋር የምናጠራህ፣ላንተም የምንቀድስ ስንኾን በርሷ ውስጥ የሚያጠፉንና ደሞችንም የሚያፈስን ታደርጋለህን? አሉ፤(አላህ) እኔ የማታውቁትን ነገር ዐውቃለሁ አላቸው:: አደምንም ስሞችን ሁሏንም አስተማረው፤ከዚያም በመላእክት ላይ (ተጠሪዎቹን) አቀረባቸው፤እውነተኞችም እንደ ኾናችሁ



https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

የነዚህን (ተጠሪዎች) ስሞች ንገሩኝ፣ አላቸው፡፡ ጥራት ይገባህ፤ከአስተማርከን ነገር በስተቀር ለኛ ዕውቀት የለንም፤አንተ ዐዋቂው ጥበበኛው አንተ ብቻ ነህና (አሉ)፡፡ ፦ አደም ሆይ! ስሞቻቸውን ንገራቸው አለው፤ስሞቻቸውን በነገራቸውም ጊዜ፣እኔ የሰማያትንና የምድርን ሩቅ ምስጢር ዐውቃለሁ፤የምትገልጹትንና ያንንም ትደብቁት የነበራችሁትን ዐውቃለሁ አላልኳችሁምን? አላቸው፡፡ ለመላእክትም፣ለአደም ስገዱ፣ባልን ጊዜ (አስታውስ)፤ሁሉም ወዲያውኑ ሰገዱ፤ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር፣እምቢ አለ፤ኮራም፣ከከሓዲዎቹም ኾነ፡፡ አደም ሆይ! አንተ ከነሚስትህ በገነት ተቀመጥ፤ከርሷም በፈለጋችሁት ስፍራ በሰፊው ተመገቡ፤ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ፤ከበደለኞች ትኾናላችሁና አልንም፡፡ ከርሷም ሰይጣን እንዳለጣቸው፤በውስጡም ከነበሩበት (ድሎት) አወጣቸው፤ከፊላችሁም ለከፊሉ ጠላት ሲኾን ውረዱ፤ለናንተም በምድር ላይ እስከ ጊዜ (ሞታችሁ) ድረስ መርጊያና መጣቀሚያ አላችሁ፤አልናቸው፡፡ አደምም ከጌታው ቃላትን ተቀበለ፤ከርሱ ላይም (ጌታው ጸተትን በመቀበል) ተመለሰለት፤እነሆ እርሱ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡ ሁላችሁም ኾናችሁ ከርሷ ውረዱ፤ከኔም የኾነ መምሪያ ቢመጣላችሁ፣ወዲያውኑ መምሪያዬን የተከተለ ሰው፣በነሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤እነሱም አያዝኑም፣አልናቸው፡፡ እነዚያም (በመልክተኞቻችን) የካዱ፣በአንቀጾቻችንም ያስተባበሉ፣እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው፤እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው፡፡››[አል በቀራህ፡30-39]



ኋላ ላይ ሰዎች ሲለያዩና ከቀጥተኛው መንገድና ከእውነት ሲርቁ፣አላህ መልክተኞችን ላከ፡፡የየራሳቸውን ሕግጋት የያዙ መልክተኞችም በተከታታይ ወደ ሰው ልጆች ተላኩ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{شَرَعَ لَكُم مِّنَ ٱلدِّينِ مَا وَصَّىٰ بِهِۦ نُوحًا وَٱلَّذِىٓ أَوْحَيْنَآ إِلَيْكَ وَمَا وَصَّيْنَا بِهِۦٓ إِبْرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ وَعِيسَىٰٓ ۖ أَنْ أَقِيمُوا۟ ٱلدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُوا۟ فِيهِ}[الشورى: ١٣]،

‹‹ለናንተ ከሃይማኖት ያንን ኑሕን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ፤ያንንም ወደ አንተ ያወረድነውን፣ያንንም በርሱ ኢብራሂምን፣ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን፣ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ፣በርሱም አትለያዩ፣ማለትን (ደነገግን)፤››[አል ሹራ፡13]

የአላህ ነቢያትና መልክተኞች ከእድሪስ፣ከኑሕና ከኢብራሂም ጀምሮ እስከ እስማዒል፣ሙሳ፣ዒሳና ሙሐመድ [የአላህ ሰላም በሁሉም ላይ ይሁን] ድረስ ተከታትለው መጡ፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ስለነሱ ተርኮልን፣ዜናቸውንም ነግሮናል፡፡ እዚህ ላይ ስለ አንዳንዶቻቸው ታሪክ ጥቂቱን እንመለከታለን፡፡ ታሪካቸው ለሚያስተውሉ ሰዎች በትምህርትና በግሳጼ የተሞላ ነውና፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَقَدْ كَانَ فِى قَصَصِهِمْ عِبْرَةٌ لِّأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ۗ مَا كَانَ حَدِيثًا يُفْتَرَىٰ وَلَٰكِن تَصْدِيقَ ٱلَّذِى بَيْنَ يَدَيْهِ وَتَفْصِيلَ كُلِّ شَىْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً لِّقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ ﴿١١١﴾}[يوسف: 111]؛

‹‹በታሪካቸው ውስጥ፣ለአእምሮ ባለቤቶች በእርግጥ መገሠጫ ነበረ፤(ይህ ቁርኣን) የሚቀጣጠፍ ወሬ አይደለም፤ግን ያንን በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ፣ለነገርም ሁሉ ገላጭ፣ለሚያምኑ ሕዝቦችም መሪና ችሮታ ነው፡፡››[ዩሱፍ፡111]

ከዚህ ታሪክ ውስጥ የሚከተሉትን ነቢያት ታሪክ እናገኛለን፦

## 1. ኑሕ عليه السلام ፦

የኑሕ ሕዝቦች ቀደም ሲል አንድ አላህን ብቻ የሚያመልኩ፣ከሞት በኋላ ዳግም መቀስቀስና መጠየቅ መኖሩን የሚያምኑ፣መልካም ሥራዎችንም የሚሠሩ ሕዝቦች ነበሩ፡፡ እነዚያ ሰዎች በሞት ሲያልፉ ቀሪዎቹ ለነዚያ ደጋግ ጻድቃን ሰዎችና ለውብ ስነምግባራቸው በጣም ስላዘኑ የመታሰቢያ ቅርጻ ቅርጽና ሐውልቶች አቆሙላቸው፡፡ እነዚያን ነገሮችም ‹‹ወድ፣ሱዋዕ፣የጉሥ፣የዑቅ፣ነስር›› ብለው ሰየሟቸው፡፡ እነዚህን ምስሎችና ቅርጻቅርጾች መላመድና የነዚያ የሞቱባቸው ደጋግ ሰዎች መለያ ምልክትና ተምሳሌት አድርገው መውሰድ ጀመሩ፡፡ ለሙታኑ የነበራቸውን አክብሮት ለመግለጽም ቀስ በቀስ እነዚህን ምስሎችና ቅርጻቅርጾች ማክበር ያዙ፡፡ እንዲህ እያሉ ዘመን አልፎ ዘመን ተተካ፡፡ አባቶች ሞተው ልጆች ጎለመሱ፡፡ ተተኪው ትውልድ አባቶቹ የጀመሩትን የምስሎቹንና የቅርጻቅርጾቹን አክብሮት በይበልጥ በመጨመር ከፊታቸው ማጎንበስና መስገድ ጀመሩ፡፡ ቅርጻቅርጾቹ በሰዎቹ ልብ ውስጥ ጠልቀው እየገቡና ከፍተኛ ቦታ እየያዙ መጡ፡፡ ቀጣዩ ትውልድም በቅርጻቅርጾቹንና ምስሎቹን የሚሰገድላቸውና የሚሳልላቸው አማልክት አድርጎ በመያዙ ብዙ ሕዝብ ለጥመት ተጋለጠ፡፡

በዚህን ጊዜ ነው አላህ (ሱ.ወ.) ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዲመራቸው፣ከጣዖታት አምልኮ እንዲከለክላቸውና አላህን ብቻ እንዲገዙ ጥሪ እንዲያደርጉላቸው ነቢዩ ኑሕን عليه السلام ወደነዚህ ሕዝቦች የላከው፡፡ . .

{فَقَالَ يَٰقَوْمِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُۥٓ}[المؤمنون: ٢٣]؛

‹‹፦ ሕዝቦቼ ሆይ! አላህን ተገዙ፤ከርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም . . አላቸው፡፡››[አል ሙእሚኑን፡23]

አስተባበሉት እንጂ አልተቀበሉትም፡፡ ከአላህ ቅጣትና ከቁጣው በማስጠንቀቅም እንዲህ አላቸው፦

{إِنِّىٓ أَخَافُ عَلَيْكُمْ عَذَابَ يَوْمٍ عَظِيمٍ ﴿١٣٥﴾}[الشعراء: ١٣٥]،

https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹እኔ በናንተ ላይ የታላቅን ቀን ቅጣት እፈራለሁና፡፡››[አል ሹዐራ፡135]

እንዲህም መለሱለት፦

{قَالَ ٱلْمَلَأُ مِن قَوْمِهِۦٓ إِنَّا لَنَرَىٰكَ فِى ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ﴿٦٠﴾}[الأعراف: ٦٠]،

‹‹ከሕዝቦቹ (የካዱት) መሪዎቹ፦ እኛ በግልጽ መሳሳት ውስጥ ኾነህ በእርግጥ እናይሃለን አሉት፡፡››[አል አዕራፍ፡60]

ኑሕም ﷺ መለሱላቸው፦

{قَالَ يَٰقَوْمِ لَيْسَ بِى ضَلَٰلَةٌ وَلَٰكِنِّى رَسُولٌ مِّن رَّبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٦١﴾ أُبَلِّغُكُمْ رِسَٰلَٰتِ رَبِّى وَأَنصَحُ لَكُمْ وَأَعْلَمُ مِنَ ٱللَّهِ مَا لَا تَعْلَمُونَ ﴿٦٢﴾}[الأعراف: ٦١ـ ٦٢]؛

‹‹አላቸው፦ ወገኖቼ ሆይ! ምንም መሳሳት የለብኝም፤ግን እኔ ከዓለማት ጌታ መልክተኛ ነኝ፡፡ የጌታዬን መልክቶች አደርስላችኋለሁ፤ለናንተም እመክራችኋለሁ፤ከአላህም በኩል የማታውቁትን ዐቃለሁ፡፡››[አል አዕራፍ፡61-62]

ሕዝቡቦቹም በኑሕ አነጋገር ተገረሙ፡፡ አንተ እንደኛው ያለ ሰው ሆነህ እንዴት የአላህ መልክተኛ ትሆናለህ?! አንተን አምነው የተከተሉህም ግምት የማይሰጣቸው ተራ ሰዎች ናቸው፤ . . እናም በገንዘብም ሆነ በክብር ከኛ የተሻላችሁ አይደላችሁምና ውሸታሞች ናችሁ የሚል ጥርጣሬ አለን፣አሉ፡፡ እርስ በርሳቸውም እንዲህ ተባባሉ፦

{مَا هَٰذَآ إِلَّا بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُرِيدُ أَن يَتَفَضَّلَ عَلَيْكُمْ وَلَوْ شَآءَ ٱللَّهُ لَأَنزَلَ مَلَٰٓئِكَةً مَّا سَمِعْنَا بِهَٰذَا فِىٓ ءَابَآئِنَا ٱلْأَوَّلِينَ ﴿٢٤﴾ إِنْ هُوَ إِلَّا رَجُلٌۢ بِهِۦ جِنَّةٌ}[المؤمنون: ٢٤ـ ٢٥]،

‹‹፦ ይህ ብጤያችሁ ሰው እንጅ ሌላ አይደለም፤በናንተ ላይ መብለጥን ይፈልጋል፤አላህም በሻ ኖሮ መላእክትን ባወረደ ነበር፤ይህንንም (የሚለውን) በመጀመሪያዎቹ አባቶቻችን አልሰማንም፡፡ እርሱ፣በርሱ ዕብደት ያለበት ሰው እንጅ ሌላ አይደለም፤››[አል ሙእሚኑን፡24-25]

ከፊላቸው ከፊሉን በጣዖታቱ አምልኮ ላይ አበረታታ፦

{وَقَالُوا۟ لَا تَذَرُنَّ ءَالِهَتَكُمْ وَلَا تَذَرُنَّ وَدًّا وَلَا سُوَاعًا وَلَا يَغُوثَ وَيَعُوقَ وَنَسْرًا ﴿٢٣﴾}[نوح: ٢٣]،

‹‹አሉም፦ አምላኮቻችሁን አትተዉ፤ወድንም፣ሱዋዕንም፣የጉሥንም፣የዑቅን ም፣ነስርንም (እነዚህ የአማልክቶቻቸው ስሞች ናቸው) አትተዉ፡፡››[ኑሕ፡23]

ኑሕም ﷺ እንዲህ አሏቸው፦

{أَوَعَجِبْتُمْ أَن جَآءَكُمْ ذِكْرٌ مِّن رَّبِّكُمْ عَلَىٰ رَجُلٍ مِّنكُمْ لِيُنذِرَكُمْ}[الأعراف: ٦٣]،

‹‹አላህን ልትፈሩና ይታዘንላችሁም ዘንድ ከናንተው (ጎሳ) በኾነ ሰው ላይ እንዲያስጠነቅቃችሁ ከጌታችሁ ግሣጼ ቢመጣላችሁ ትደነቃላችሁን?(አላቸው)፡፡››[አል አዕራፍ፡63]

በጥሪው ኑሕ ﷺ ለስለስ ያለ አግባቢ አቀራረብ ቢከተሉም ሰዎቹ ግን እምቢታና ትእቢትን ብቻ ጨመሩ፡፡ ነቢዩ ሳይሰለቹ አዘውትረው ጥሪያቸውን ቀጠሉ፡፡ እንዲህ እስከማለት ደረጃ ድረስም ለፉ፦

{قَالَ رَبِّ إِنِّى دَعَوْتُ قَوْمِى لَيْلًا وَنَهَارًا ﴿٥﴾ فَلَمْ يَزِدْهُمْ دُعَآءِىٓ إِلَّا فِرَارًا ﴿٦﴾ وَإِنِّى كُلَّمَا دَعَوْتُهُمْ لِتَغْفِرَ لَهُمْ جَعَلُوٓا۟ أَصَٰبِعَهُمْ فِىٓ ءَاذَانِهِمْ وَٱسْتَغْشَوْا۟ ثِيَابَهُمْ وَأَصَرُّوا۟ وَٱسْتَكْبَرُوا۟ ٱسْتِكْبَارًا ﴿٧﴾}[نوح: ٥ـ ٧]،

‹‹(ስለተቃወሙትም) አለ፦ ሕዝቦቼ ሆይ! እኔ ለናንተ ገላጭ የኾንኩ አስጠንቃቂ ነኝ፡፡ አላህን ተገዙት፤ፍሩትም፤ታዘዙኝም በማለት (አስጠንቃቂ ነኝ)፡፡ ለናንተ ከኀጢአቶቻችሁ ይምራልና፤ወደ ተወሰነው ጊዜም ያቆያችኋል፤የአላህ (የወሰነው) ጊዜ፣በመጣ ወቅት አይቅቆይም፡፡ የምታውቁ ብትኾኑ ኖሮ (በታዘዛችሁ ነበር)፡፡ (ስለ ተቃወሙትም) አለ፦ ጌታዬ ሆየ! እኔ ሌሊትም ቀንም ሕዝቦቼን ጠራሁ፡፡ ጥሪየም መሸሽን እንጅ ሌላ አልጨመረላቸውም፡፡ እኔም ለነርሱ ትምር ዘንድ (ወደ እምነት) በጠራኋቸው ቁጥር፣ጣቶቻቸውን በጆሮቻቸው ውስጥ አደረጉ፤ልብሶቻቸውንም ተከናነቡ፤(በመጥፎ ሥራቸው ላይ) ዘወተሩም፡፡ (ያለ ልክ) መኩራትንም ኮሩ፡፡››[ኑሕ፡5-7]

ነቢዩ ﷺ አመቺ ሆኖ በተገኘ ስልት ሁሉ ጥሪ አደረጉ፦

{ثُمَّ إِنِّىٓ أَعْلَنتُ لَهُمْ وَأَسْرَرْتُ لَهُمْ إِسْرَارًا ﴿٩﴾ فَقُلْتُ ٱسْتَغْفِرُوا۟ رَبَّكُمْ إِنَّهُۥ كَانَ غَفَّارًا ﴿١٠﴾}[نوح: ٩ـ ١٠]،

‹‹ከዚያም እኔ ለነሱ ገለጽኩ፣ለነሱም መመስጠርን መሰጠርኩ (በግልጽም በምስጢርም ወደ እምነት ጠራኋቸው)፣አልኳቸውም፦ ጌታችሁን ምሕረትን ለምኑት፤እርሱ በጣም መሓሪ ነውና፡፡››[ኑሕ፡9-10]

አንዳንዶቻቸው ውሃ የማይቋጥር ምክንያት መደርደር ያዙ፡፡ እንዲህም አሉ፦

{قَالُوٓا۟ أَنُؤْمِنُ لَكَ وَٱتَّبَعَكَ ٱلْأَرْذَلُونَ ﴿١١١﴾}[الشعراء: ١١١]



### የማጠቃለያው መልክት

‹‹ሙሐመድ እስላምን ይዞ የመጣው መልክተኛ ነው፡፡ በዚህም ታላላቅ መልክቶችን ይዘው ከመጡ የመልክተኞች ሰንሰለት የመጨረሻው ዘለበት ይሆናል፡፡››

ዎልፍ ባሮን አሀር ነዚር

የኦስትሪያ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር



‹‹(እነርሱም)፣ወራዶቹ የተከተሉህ ኾነህ ለአንተ እናምናለን? አሉት፡፡››[አል ሹዐራ፡111]

የኑሕ ﷺ ምላሽ ግን ሙሉ በሙሉ በለሰለሰ ለዘብተኛ መካሪ አነጋገር ነበር፦

{قَالَ وَمَا عِلْمِي بِمَا كَانُوا يَعْمَلُونَ ﴿١١٢﴾}[الشعراء: ١١٢]

## ትእቢትና ታሪክን ማጣመም

‹‹በመካከለኞቹ ክፍለ ዘመናት ክርስቲያን ጸሐፍት በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ የተጠቀሱትን የሰው ዝርዮች ምደባን አምነው መቀበል ጀመሩ፡፡ አዳዲስ መደቦችንም ጨመሩበት፡፡ ሰፍኖ የቆየው እምነትም ካህናትና ቀሳውስት ከሴም ዝርያ፣ፈረሰኞችና ተዋጊዎች ከያፌት ዝርያ፣ድሆች ከካም ዝርያ የወጡ መሆናቸው ነበር፡፡ ይህ ምደባ ስር ሰዶ በ1964 ከምዕራብ ቨርጂኒያ የአሜሪካ ሴናተር የሆኑት ሮበርት በይርድ ይህን የኖሕ ልጆች ትረካ የዩ.ኤስ. አሜሪካን የዘር መድልዖ ጭቆና ለማቆየት እንደምክንያት እንዲገለገሉበት አድርጓቸዋል፡፡››



‹‹(እርሱም) አላቸው፦ ይሠሩት በነበሩት ነገር ምን ዕውቀት አለኝ፤››[አል ሹዐራ፡112]

እንዲህም አሏቸው፦

{إِنْ حِسَابُهُمْ إِلَّا عَلَىٰ رَبِّي ۖ لَوْ تَشْعُرُونَ ﴿١١٣﴾}[الشعراء: ١١٣]،

‹‹ምርመራቸው በጌታዬ ላይ እንጅ በሌላ ላይ አይደለም፤ብታውቁ ኖሮ፣(ይህንን ትረዱ ነበር)፤››[አል ሹዐራ፡113]

በተጨማሪም እንዲህ አሏቸው፦

{وَمَا أَنَا بِطَارِدِ الْمُؤْمِنِينَ ﴿١١٤﴾}[الشعراء: ١١٤]، {وَمَا أَنَا بِطَارِدِ الَّذِينَ آمَنُوا}[هود: ٢٩]،

‹‹እኔም አማኞችን አባራሪ አይደለሁም፤››[አል ሹዐራ፡114]

‹‹እኔም እነዚያን ያመኑትን አባራሪ አይደለሁም፤››[ሁድ፡29]

በኔ ያመኑ፣ከኔ ጋር የቆሙና ያገዙኝን ሰዎች እንዴት አባርራለሁ?! በማለት ጠየቁ፦

{وَيَا قَوْمِ مَن يَنصُرُنِي مِنَ اللَّهِ إِن طَرَدتُّهُمْ ۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ﴿٣٠﴾}[هود: ٣٠]، {إِنْ أَنَا إِلَّا نَذِيرٌ مُّبِينٌ ﴿١١٥﴾}[الشعراء: ١١٥]؛

‹‹ሕዝቦቼም ሆይ! ባባርራቸው፣ከአላህ (ቅጣት) የሚያድነኝ ማን ነው? አትገሠጹምን?››[ሁድ፡30]

‹‹እኔ ግልጽ አስፈራሪ እንጅ ሌላ አይደለሁም፡፡››[አል ሹዐራ፡115]

ጨዋና ተራ፣ሀብታምና ደሃ፣ትልቅና ትንሽ፣ነጭና ጥቁር ሳይሉ ሰዎችን ሁሉ በእኩል አስተማሩ፤ አስጠነቀቁ፡፡ . . ሰዎቹ ግን በኑሕ የቀረበላቸውን ማስረጃ መካድ ሲያቅተታቸውና መሞገት ሲሳናቸው፣ነቢዩን በድንጋይ ለመውገር



መዛት ጀመሩ፦

{قَالُوا لَئِن لَّمْ تَنتَهِ يَا نُوحُ لَتَكُونَنَّ مِنَ الْمَرْجُومِينَ ﴿١١٦﴾}[الشعراء: ١١٦].

‹‹፦ ኑሕ ሆይ! (ከምትለው) ባትከለከል፣በእርግጥ ከሚወገሩት ትኾናለህ አሉት፡፡››[አል ሹዐራ፡116]

ኑሕ ﷺ፣ሰዎቹ ምንም ዓይነት ምክንያታዊ አስተሳሰብ እንደማይቀበሉና እንደማይመሩ እርግጠኛ በሆኑ ጊዜ፣ከነዚህ ትእቢተኞች እንዲያድናቸው አላህን ለመኑ፦

{قَالَ رَبِّ إِنَّ قَوْمِي كَذَّبُونِ ﴿١١٧﴾}[الشعراء: ١١٧]، {فَافْتَحْ بَيْنِي وَبَيْنَهُمْ فَتْحًا وَنَجِّنِي وَمَن مَّعِيَ مِنَ الْمُؤْمِنِينَ ﴿١١٨﴾}[الشعراء: ١١٨].

‹‹(እርሱም) አለ፦ ጌታዬ ሆይ! ሕዝቦቼ አስተባበሉኝ፤››[አል ሹዐራ፡117] ‹‹በኔና በነርሱም መካከል (ተገቢን) ፍርድ ፍረድ፤አድነኝም፤ከኔ ጋር ያሉትንም ምእመናን፡፡››[አል ሹዐራ፡118]

ኑሕ ﷺ፣ሰዎቹ በክህደታቸው ከቀጠሉ የአላህ ቅጣት እንሚወርድባቸው በሚያስጠነቅቁበት ጊዜ፣አንዳንዶቹ በመሳለቅ እንዲህ አሏቸው፦

فَأْتِنَا بِمَا تَعِدُنَا إِن كُنتَ مِنَ الصَّادِقِينَ ﴿٣٢﴾}[هود: ٣٢]،

‹‹ከእውነተኞቹም አንደ ኾንክ የምታስፈራራብንን ቅጣት አምጣው አሉ፡፡››[ሁድ፡32]

ኑሕ ግን ውሳኔው በኔ እጅ አይደለም አሏቸው፦

{إِنَّمَا يَأْتِيكُم بِهِ اللَّهُ إِن شَاءَ}[هود: ٣٣]، {وَلَا يَنفَعُكُمْ نُصْحِي إِنْ أَرَدتُّ أَنْ أَنصَحَ لَكُمْ}[هود: ٣٤].

‹‹፦ እርሱን የሚያመጣባችሁ የሻ እንደኾነ አላህ ብቻ ነው፤››[ሁድ፡33] ‹‹ለናንተም ልመክራችሁ ብሻ አላህ ሊያጠማችሁ ሽቶ እንደኾነ ምክሬ አይጠቅማችሁም፤››[ሁድ፡34]

አላህም (ሱ.ወ.) እንዲህ ሲል ወደ ነቢዩ ላከ፦

{أَنَّهُ لَن يُؤْمِنَ مِن قَوْمِكَ إِلَّا مَن قَدْ آمَنَ فَلَا تَبْتَئِسْ بِمَا كَانُوا يَفْعَلُونَ ﴿٣٦﴾}[هود: ٣٦]،

‹‹ከሕዝቦችህ በእርግጥ ካመኑት በስተቀር (ወደፊት) አያምኑም፤ይሠሩትም በነበሩት (ክህደት) አትዘን . . ››[ሁድ፡36]

ማስረጃው ተጠናቆ ቀርቧል፤የማመካኛ ቀዳዳ ሁሉ ተዘግቷል፤ጥሪውም ለዐሥር ምእተ ዓመታት ያህል ተራዝሟል፡፡ ነቢዩ ኑሕም ﷺ ከዚህ ሁሉ ረዥምም ዘመናት ጥረት በኋላ ከሕዝባቸው ተስፋ ቆርጠዋል፡፡ በመሆኑም እንዲህ ሲሉ አላህን (ሱ.ወ.) ለመኑ፦

{وَقَالَ نُوحٌ رَّبِّ لَا تَذَرْ عَلَى الْأَرْضِ مِنَ الْكَافِرِينَ دَيَّارًا ﴿٢٦﴾ إِنَّكَ إِن تَذَرْهُمْ يُضِلُّوا عِبَادَكَ وَلَا يَلِدُوا إِلَّا فَاجِرًا كَفَّارًا ﴿٢٧﴾}[نوح: ٢٦-٢٧]

‹‹ኑሕም አለ፦ ጌታዬ ሆይ! ከከሃዲዎቹ በምድር ላይ አንድንም አትተው፡፡ አንተ ብትተዋቸው ባሮችህን ያሳስታሉና፤ኀጢአተኛና ከሓዲንም እንጅ ሌላን



https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am



አይወልዱም::››[ኑሕ:26-27]

መርከብ እንዲሰሩም አላህ ላከባቸው፦

{فَأَوْحَيْنَآ إِلَيْهِ أَنِ ٱصْنَعِ ٱلْفُلْكَ بِأَعْيُنِنَا وَوَحْيِنَا}[المؤمنون: ٢٧]،

‹‹ወደርሱም (እንዲህ ስንል) ላክን፦ በተመልካችነታችንና በትእዛዛችን፣ታንኳን ሥራ፤››[አል ሙእሚኑን:27]

መርከቡንም መስራት ጀመሩ፦

{وَيَصْنَعُ ٱلْفُلْكَ وَكُلَّمَا مَرَّ عَلَيْهِ مَلَأٌ مِّن قَوْمِهِۦ سَخِرُوا۟ مِنْهُ}[هود: ٣٨].

‹‹ከወገኖቹም መሪዎቹ በርሱ አጠገብ ባለፉ ቁጥር ከርሱ እየተሳለቁ መርከቢቱን ይሠራል::››[ሁድ:38]

ኑሕም عليه السلام በመልካም ስነምግባርና በተለሳለሰ አነጋገር መልስ ሰጧቸው፦

{إِن تَسْخَرُوا۟ مِنَّا فَإِنَّا نَسْخَرُ مِنكُمْ كَمَا تَسْخَرُونَ ﴿٣٨﴾}[هود: ٣٨]،

‹‹ከኛ ብትሳለቁ እኛም እንደ ተሳለቃችሁብን ከእናንተ እንሳለቅባችኋለን አላቸው::››[ሁድ:38]

ከዚያም ሕዝቡን አስጠነቀቁ፤በአላህም ቅጣት አስፈራሩ፦

{فَسَوْفَ تَعْلَمُونَ مَن يَأْتِيهِ عَذَابٌ يُخْزِيهِ وَيَحِلُّ عَلَيْهِ عَذَابٌ مُّقِيمٌ ﴿٣٩﴾}[هود: ٣٩]،

‹‹የሚያዋርደው ቅጣት የሚመጣበትን፣በርሱም ላይ ዘውታሪ ቅጣት የሚሰፍርበትን ሰው፣(ማን እንደ ኾነ) ወደፊት ታውቃላችሁ (አላቸው)::››[ሁድ:39]

መርከቡ ተሰርቶ እስኪያበቃ ድረስ ሥራውን በትጋት አከናወኑ:: ከዚያም ከርሳቸው ጋር ያመኑትን ሰዎችና ሕይወት ካላቸው ነገሮች ሁሉ ጥንድ ጥንድ በመርከቢቱ እንዲያሳፍሩ አላህ (ሱ.ወ.) ኑሕን አዘዛቸው፦

{حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءَ أَمْرُنَا وَفَارَ ٱلتَّنُّورُ قُلْنَا ٱحْمِلْ فِيهَا مِن كُلٍّ زَوْجَيْنِ ٱثْنَيْنِ وَأَهْلَكَ إِلَّا مَن سَبَقَ عَلَيْهِ ٱلْقَوْلُ وَمَنْ ءَامَنَ وَمَآ ءَامَنَ مَعَهُۥٓ إِلَّا قَلِيلٌ ﴿٤٠﴾}[هود: ٤٠]؛

‹‹ትእዛዛችን በመጣና እቶኑም በገነፈለ ጊዜ፣በርሷ ውስጥ ከየዓይነቱ ሁሉ ሁለት ሁለት፣(ወንድና ሴት)፤ቤተሰቦችህንም፣ቃል ያለፈበት ሲቀር፣ያመነንም ሰው ሁሉ ጫን አልነው፤ከርሱም ጋር ጥቂቶች እንጅ አላመኑም::››[ሁድ:40]

አምነው የተከተሏቸውን ሰዎችና ጥንድ ጥንዶቹንም እንስሳት አሳፈሩ፦

{وَقَالَ ٱرْكَبُوا۟ فِيهَا بِسْمِ ٱللَّهِ مَجْر۪ىٰهَا وَمُرْسَىٰهَآ ۚ إِنَّ رَبِّى لَغَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٤١﴾}[هود: ٤١]،

‹‹፦ መኼጃም መቆሚያም በአላህ ስም ነው፣እያላችሁም በውስጧ ተሳፈሩ፤ጌታዬ መሓሪ አዛኝ ነውና ?አላቸው::››[ሁድ:41]

ኑሕና ከርሳቸው ጋር ያመኑ ሰዎች፣ከጥንድ ጥንዶቹ እንስሳት ጋር በመርከቡ ተሳፍረው ቦታ ቦታቸውን ሲይዙ፣ሰማዩ ከባድና የማያቋርጥ ዝናም ማንቆርቆር ጀመረ:: ወንዞችና ምንጮች በውሃ ገነፈሉ፦

{فَفَتَحْنَآ أَبْوَٰبَ ٱلسَّمَآءِ بِمَآءٍ مُّنْهَمِرٍ ﴿١١﴾ وَفَجَّرْنَا ٱلْأَرْضَ عُيُونًا فَٱلْتَقَى ٱلْمَآءُ عَلَىٰٓ أَمْرٍ قَدْ قُدِرَ ﴿١٢﴾ وَحَمَلْنَٰهُ عَلَىٰ ذَاتِ أَلْوَٰحٍ وَدُسُرٍ ﴿١٣﴾ تَجْرِى بِأَعْيُنِنَا جَزَآءً لِّمَن كَانَ كُفِرَ ﴿١٤﴾}[القمر: ١١-١٤]،

‹‹ወዲያውም የሰማይን ደጃፎች በሚንቧቧ ውሃ ከፈትን:: የምድርንም ምንጮች አፈነዳን፤ውሃውም (የሰማዩና የምድሩ) በእርግጥ በተወሰነ ኹነታ ላይ ተገናኘ:: ባለ ሳንቃዎችና ባለ ሚስማሮች በኾነችም ታንኳ ላይ ጫነው:: በጥበቃችን ሥር ኾና ትንሻለላለች፤ተክዶ ለነበረው ሰው ምንዳ (ይህንን ሠራን)::››[አል ቀመር:11-14]

ኑሕ ﷺ ያላመነውን ልጃቸውን ከውሃ ማጥለቅለቁ ለመሸሽ ሲሞክር ያዩትና እንዲህ ሲሉ ይጠሩታል፦

{يَٰبُنَىَّ ٱرْكَب مَّعَنَا وَلَا تَكُن مَّعَ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٤٢﴾}[هود: ٤٢]،

‹‹ልጄ ሆይ! ከኛ ጋር ተሳፈር፣ከከሓዲዎቹም አትኹን ሲል ጠራው::››[ሁድ:42]

ልጁ ግና አላምን ይላል፤የአባቱን ምክር አሻፈረኝ ብሎ ለኑሕ እንዲህ ሲል ይመልሳል፦

{قَالَ سَـَٔاوِىٓ إِلَىٰ جَبَلٍ يَعْصِمُنِى مِنَ ٱلْمَآءِ}[هود: ٤٣]،

‹‹(ልጁም)፦ ከውሃው ወደሚጠብቀኝ ተራራ እጠጋለሁ አለ፤››[ሁድ:43]

ኑሕ ﷺ ልጃቸውን በእዝነትና በርህራሄ ተመለከቱና እንዲህ አሉት፦

{لَا عَاصِمَ ٱلْيَوْمَ مِنْ أَمْرِ ٱللَّهِ إِلَّا مَن رَّحِمَ}[هود: ٤٣]،

‹‹(አባቱም)፦ ዛሬ ከአላህ ትእዛዝ ምንም ጠባቂ የለም፤(እርሱ) ያዘነለት ካልኾነ በቀር አለው፤››[ሁድ:43]

{وَحَالَ بَيْنَهُمَا ٱلْمَوْجُ فَكَانَ مِنَ ٱلْمُغْرَقِينَ ﴿٤٣﴾}[هود: ٤٣]،

‹‹ማዕበሉም በመካከላቸው ጋረደ፤ከሰጣሚዎቹም ኾነ::››[ሁድ:43]

ቀደም ብሎ ቤተሰባቸው ለማዳን አላህ ቃል የገባላቸው ኑሕ ﷺ፣ሆዳቸው ለአብራካቸው ክፋይ ይራራና ያድነው ዘንድ ወደ አላህ (ሱ.ወ.) ይማጸናሉ:: እንዲህ ሲሉም ለመኑ፦

{رَبِّ إِنَّ ٱبْنِى مِنْ أَهْلِى وَإِنَّ وَعْدَكَ ٱلْحَقُّ وَأَنتَ أَحْكَمُ ٱلْحَٰكِمِينَ ﴿٤٥﴾}[هود: ٤٥]،

‹‹፦ ጌታዬ ሆይ! ልጄ ከቤተሰቤ ነው፤ኪዳንህም እውነት ነው፤አንተም ከፈራጆቹ ሁሉ ይበልጥ ዐዋቂ ነህ::››[ሁድ:45]

በጎ ሠሪ ምእመናን የሆኑ ቤተሰቦቻቸውን ለማዳን ቃል የገባላቸው አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ሲል መለሰላቸው፦

{قَالَ يَٰنُوحُ إِنَّهُۥ لَيْسَ مِنْ أَهْلِكَ ۖ إِنَّهُۥ عَمَلٌ غَيْرُ صَٰلِحٍ}[هود: ٤٦]،

‹‹(አላህም)፦ ኑሕ ሆይ! እርሱ ከቤተሰብህ አይደለም፤እርሱ መልካም ያልኾነ ሥራ ነው፤ . . . አለው::››[ሁድ:46]

https://www.path-2-happiness.com/am

በሃይማኖት ውስጥ አማላጅ ጉዳይ አስፈጻሚ የለም፤እርሱ ቤተሰብህ አይደለም:: በአላህ አንድነት ካላመነና እርሱን ብቻ ካልተገዛ ያንተ የነቢዩ ልጅ መሆኑ ምንም አይጠቅመውም::

ውሃው ምድሪቱን ሙሉ በሙሉ ካጥለቀለቀና ከሓዲዎቹን ሙሉ በሙሉ ካጠፋ በኋላም ለምድሪቱ እንዲህ ተባለ፦

{وَقِيلَ يَـٰٓأَرۡضُ ٱبۡلَعِي مَآءَكِ}[هود: ٤٤]،

‹‹ተባለም፦ ምድር ሆይ! ውሃሽን ዋጪ፤[ሁድ:44]

ከምድር የፈለቀው ውሃ ወደ ምድር ገባ፤ለሰማይም ጥሪ ተላለፈ፦

{وَيَـٰسَمَآءُ أَقۡلِعِي}[هود: ٤٤]،

‹‹ሰማይም ሆይ! (ዝናምሽን) ያዥ::››[ሁድ:44]

ከሰማይ የሚንቆረቆረው ውሃ ጋብ አለ፤ዝናሙም አቆመ፦

{وَٱسۡتَوَتۡ عَلَى ٱلۡجُودِيِّ}[هود: ٤٤]،

‹‹ጁዲይ በሚባልም ተራራ ላይ (መርከቢቱ) ተደላደለች፤››[ሁድ:44]

ጁዲይ መርከቢቱ የቆመችበት ተራራ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) ወደ ኑሕ ﷺ እንዲህ ሲል ላከ፦

{يَـٰنُوحُ ٱهۡبِطۡ بِسَلَٰمٖ مِّنَّا وَبَرَكَٰتٍ عَلَيۡكَ وَعَلَىٰٓ أُمَمٖ مِّمَّن مَّعَكَ}[هود: ٤٨]؛

‹‹፦ ኑሕ ሆይ! ከኛ በኾነ ሰላም፣ባንተ ላይና አንተም ጋር ባሉት ሕዝቦች (ትውልድ) ላይ በኾኑ በረከቶችም፣የተጎናጸፍክ ኾነህ ውረድ፤››[ሁድ:48]

ኑሕ ከመርከቧ ወረዱ:: ከርሳቸው ጋር የነበሩ ምእመናንም ወረዱ:: መንደርም መሰረቱ:: እጽዋት ተከሉ:: አብሯቸው የነበሩ የእንስሳት ዝርያዎችንም ጥይራቡ ዘንድ አውጥተው ለቀቁ:: በምድር ላይ ግንባታ ተጀመረ:: ሰዎችም መዋለድና መራባት ቀጠሉ::

## የነቢያትን ክብር ማዋረድ

‹‹ኖኅም ገበሬ መሆን ጀመረ፣ወይንም ተከለ:: ከወይን ጠጁም ጠጣና ሰከረ፤በድንኳኑም ውስጥ እራቁቱን ሆነ:: የከነዓን አባት ካምም አባቱን ዕራቁትነት አየ፣ወደ ውጭም ወጥቶ ለሁለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው:: ሴምና ያፌትም ሸማ ወስደው በጫንቃቸው ላይ አደረጉ፣ኋሊትም ሄደው አባታቸውን ዕራቁትነት አለበሱ፤ፊታቸውም ወደ ኋላ ነበረ፣የአባታቸውንም እራቁትነት አላዩም:: ኖኅም ከወይን ጠጁ ስካር ነቃ፣ታናሹ ልጁ ያደረገበትንም አወቀ:: እንዲህም አለ፦ ከነዓን ርጉም ይሁን፤ለወንድሞቹም ባሪያዎች ባሪያ ይሁን:: እንዲህም አለ፦ የሴም አምላክ እግዚአብሔር ይባርክ፣ከነዓንም ለእነርሱ ባሪያ ይሁን::›› ዘፍጥ. 9፣20-27

የባቢሎኑ ቴልሙድ ገጽ 70 ላይ ለዚህ ጥቅስ ማብራሪያ ሲሰጥ ከንዓን ወይም ካም ኖኅን ስልብ አድርገው ደፈሩት ይላል:: ክቡሩ የአላህ ነቢይ ኑሕ عليه السلام ግን ፈጽሞ ከዚህ የጠሩና የተጠበቁ ናቸው::





## 2. ኢብራሂም ﷺ ፦

ኢብራሂም ﷺ የነቢያት አባትና የተውሒድ ነቢይ ናቸው:: ይህም በሁሉም የሕይወት ታሪካቸው ውስጥ በግልጽ የተንጸባረቀ ነው:: ለዚህም ነው አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ሲል የገለጻቸው፦

{إِنَّ إِبۡرَٰهِيمَ كَانَ أُمَّةٗ قَانِتٗا لِّلَّهِ حَنِيفٗا وَلَمۡ يَكُ مِنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ ١٢٠}[النحل: ١٢٠]؛

‹‹ኢብራሂም ለአላህ ታዛዥ፣ወደ ቀጥተኛ ሃይማኖት ተዘንባይ፣ሕዝብ ነበር፤ከአጋሪዎቹም አልነበረም::››[አል ነሕል:120]

ነቢዩ ኢብራሂም عليه السلام ያደጉት በጣዖታውያን ሕዝቦች ውስጥ ነበር:: ይልቅዬም አባታቸው ከጣዖት አምላኪዎች አንዱ ብቻ ሳይሆን የጣዖታቱ አንዱ ጠራቢ አዘጋጅና አገልጋይም ነበር:: ኢብራሂም عليه السلام በዚህ ጉዳይ ላይ አባታቸውንና ሕዝባቸውን አወያዩ፦

{وَإِذۡ قَالَ إِبۡرَٰهِيمُ لِأَبِيهِ ءَازَرَ أَتَتَّخِذُ أَصۡنَامًا ءَالِهَةً إِنِّيٓ أَرَىٰكَ وَقَوۡمَكَ فِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٖ ٧٤}[الأنعام: ٧٤]،

‹‹ኢብራሂምም ለአባቱ ለአዘር ጣዖታትን አማልክት አድርገህ ትይዛለህን? እኔ፤አንተንም ሕዝቦችህንም በግልጽ መሳሳት ውስጥ ኾናችሁ አያችኋለሁ ባለ ጊዜ (አስታውስ)::››[አል አንዓም:74]

የሕዝባቸውን ጣዖት አምልኮ አሳማኝ ማስረጃዎችን በመደርደር ተቃወሙ:: የአላህን (ሱ.ወ.) አንድነት የሚያሳዩ ምልክቶችንም ተመልክተው ያስተነትኑ ነበር፦

{فَلَمَّا جَنَّ عَلَيۡهِ ٱلَّيۡلُ رَءَا كَوۡكَبٗاۖ قَالَ هَٰذَا رَبِّيۖ فَلَمَّآ أَفَلَ}[الأنعام: ٧٦]؛

‹‹ሌሊቱም በርሱ ላይ ባጨለመ ጊዜ ኮከብን አየ፤ይህ ጌታዬ ነው አለ፤በጠለቀም ጊዜ፦ ››[አል አንዓም:76]

ኮከቡ ከእይታ በተሰወረ ጊዜም ፦

{قَالَ لَآ أُحِبُّ ٱلۡأٓفِلِينَ ٧٦ فَلَمَّا رَءَا ٱلۡقَمَرَ بَازِغٗا}[الأنعام: ٧٦-٧٧]؛

‹‹ጠላቂዎችን አልወድም አለ:: ጨረቃንም ወጪ ኾኖ ባየ ጊዜ፦››[አል አንዓም: 76-77]





https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ጨረቃን ወጥታ አድማሱ ላይ ሲመለከቱ አንዳንድ ሰዎች ሲያመልኳት አስተዋሉና፦

{قَالَ هَٰذَا رَبِّي}[الأنعام: ٧٧]؛

‹‹ይህ ጌታዬ ነው አለ፤››[አል አንዓም:77]

ይህም አባባላቸው የሰዎቹን ሥራ በማብጠልጠልና በአምልኳቸውም በመገረም ድምጸት ነበር።

{فَلَمَّآ أَفَلَ}[الأنعام: ٧٧]؛

‹‹በገባም ጊዜ፡፡››[አል አንዓም:77]

ጨረቃዋ ጠልቃ ስታልፍም ለሕዝቡ እንዲህ አሉ፦

{قَالَ لَئِن لَّمْ يَهْدِنِي رَبِّي لَأَكُونَنَّ مِنَ ٱلْقَوْمِ ٱلضَّآلِّينَ ﴿٧٧﴾ فَلَمَّا رَءَا ٱلشَّمْسَ بَازِغَةً}[الأنعام: ٧٧ـ ٧٨]؛

‹‹፦ ጌታዬ (ቅኑን መንገድ) ባይመራኝ በእርግጥ ከተሳሳቱት ሕዝቦች እኾናለሁ አለ። ፀሐይንም ጮራዋን ዘርግታ ባየ ጊዜ፦ ››[አል አንዓም:77-78]

ሕዝቡን ለፀሐይቱ ሲሰግዱ ተመለከቱና፦

{قَالَ هَٰذَا رَبِّي هَٰذَآ أَكْبَرُ}[الأنعام: ٧٨]؛

‹‹ይህ ጌታዬ ነው፤ይህ በጣም ትልቅ ነው አለ፤››[አል አንዓም:78]

ይህም ድርጊታቸውን በማብጠልጠልና ወጥታ የምትጠልቅ ፀሐይ እንዴት አምላክ አድርጎ ይይዟሉ?! ብሎ በመሳለቅ መንፈስ ነበር።

{فَلَمَّآ أَفَلَتْ}[الأنعام: ٧٨]؛

‹‹በገባችም ጊዜ፦ ››[አል አንዓም:78]

ፀሐይዋ ጠልቃ ከዓይን ስትሰወርም ሲያመልኳት ወደነበሩ ሰዎች ፊታቸውን አዞሩና፦

{قَالَ يَٰقَوْمِ إِنِّي بَرِيٓءٌ مِّمَّا تُشْرِكُونَ ﴿٧٨﴾ إِنِّي وَجَّهْتُ وَجْهِيَ لِلَّذِي فَطَرَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ حَنِيفًا وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿٧٩﴾}[الأنعام: ٧٨ـ ٧٩].

‹‹ወገኖቼ ሆይ! እኔ ከምታጋሩ ሁሉ ንጹሕ ነኝ አለ። እኔ ለዚያ ሰማያትንና ምድርን ለፈጠረው (አምላክ) ቀጥተኛ ስኾን ፊቴን አዞርኩ፤እኔም ከአጋሪዎቹ አይደለሁም (አለ)፡፡››[አል አንዓም:78-79]

ነቢዩ ኢብራሂም አባታቸውን ለጠዖት አምልኮና ከሽርክ ለመከልከል በተለሳለሰና ምክንያታዊነትን በተላበሰ አቀራረብ ብዙ ይመክሩ ነበር፦

{يَٰٓأَبَتِ لِمَ تَعْبُدُ مَا لَا يَسْمَعُ وَلَا يُبْصِرُ وَلَا يُغْنِي عَنكَ شَيْـًٔا ﴿٤٢﴾ يَٰٓأَبَتِ إِنِّي قَدْ جَآءَنِي مِنَ ٱلْعِلْمِ مَا لَمْ يَأْتِكَ فَٱتَّبِعْنِيٓ أَهْدِكَ صِرَٰطًا سَوِيًّا ﴿٤٣﴾ يَٰٓأَبَتِ لَا تَعْبُدِ ٱلشَّيْطَٰنَ إِنَّ ٱلشَّيْطَٰنَ كَانَ لِلرَّحْمَٰنِ عَصِيًّا ﴿٤٤﴾ يَٰٓأَبَتِ إِنِّيٓ أَخَافُ أَن يَمَسَّكَ عَذَابٌ مِّنَ ٱلرَّحْمَٰنِ}[مريم: ٤٢ـ ٤٥]،

‹‹፦ አባቴ ሆይ! የማይሰማንና የማያይን፤ከአንተም ምንንም የማይጠቅምህን (ጣዖት) ለምን ትገዛለህ? አባቴ ሆይ! እኔ ከዕውቀት ያልመጣልህ ነገር በእርግጥ መጥቶልኛልና ተከተለኝ፤ቀጥተኛውን መንገድ እመራሃለሁና። አባቴ ሆይ! ሰይጣንን አትግገዛ፤ሰይጣን ለአልረሕማን አመጠኛ ነውና። አባቴ ሆይ! እኔ ከአልረሕማን ቅጣት ሊያገኝህ፤ለሰይጣንም ጓደኛ ልትኾን እፈራለሁ፡፡››[መርየም፡ 42-45]

የሚያሳዝነው ግን የአባታቸው ምላሽ ከእምቢታም ያለለፈ መሆኑ ነበር፦

{قَالَ أَرَاغِبٌ أَنتَ عَنْ ءَالِهَتِي يَٰٓإِبْرَٰهِيمُ لَئِن لَّمْ تَنتَهِ لَأَرْجُمَنَّكَ وَٱهْجُرْنِي مَلِيًّا ﴿٤٦﴾}[مريم: ٤٦]،

‹‹(አባቱም)፦ ኢብራሂም ሆይ! አንተ ከአምላኮቼ ትተህ የምትዞር ነህን? ባትከለከል፤በእርግጥ እወግረሃለሁ፤ረጅም ጊዜንም ተዎኝ አለ፡፡››[መርየም:42]

ለዚህ ማስፈራሪያ ኢብራሂም ﷺ የሰጡት መልስ በመልካም ስነምግባር በእዝነትና በርህራሄ የታጀበ ነበር፦

{قَالَ سَلَٰمٌ عَلَيْكَ سَأَسْتَغْفِرُ لَكَ رَبِّيٓ إِنَّهُۥ كَانَ بِي حَفِيًّا ﴿٤٧﴾ وَأَعْتَزِلُكُمْ وَمَا تَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ وَأَدْعُوا۟ رَبِّي عَسَىٰٓ أَلَّآ أَكُونَ بِدُعَآءِ رَبِّي شَقِيًّا ﴿٤٨﴾ }[مريم: ٤٧ـ ٤٨].

‹‹፦ ደህና ኹን፤ወደፊት ከጌታዬ ምሕረትን እለምንልሃለሁ፤እርሱ ለኔ በጣም ርኅሩኅ ነውና አለ፤እናንተንም፤ከአላህ ሌላ የምትግዙትንም ፤እርቃለሁ፤ጌታዬን በመገዛት የማፍር አለመኾኔን እከጀላለሁ፡፡››[መርየም:47-48]

ኢብራሂም ﷺ ለአባታቸውና ለሕዝባቸው ጣዖታትን ማምለክና በአላህ ማጋራትን ትተው አንድ አላህን (ሱ.ወ.) ብቻ እንዲያመልኩ ወደ ተውሒድ የሚያደርጉትን ጥሪ አለመታከት ቀጠሉበት። ሕዝቡ ግን ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ በሽርኩ ገፋበት፦

{وَحَآجَّهُۥ قَوْمُهُۥ قَالَ أَتُحَٰٓجُّوٓنِّي فِي ٱللَّهِ وَقَدْ هَدَىٰنِ وَلَآ أَخَافُ مَا تُشْرِكُونَ بِهِۦٓ إِلَّآ أَن يَشَآءَ رَبِّي شَيْـًٔا وَسِعَ رَبِّي كُلَّ شَيْءٍ عِلْمًا أَفَلَا تَتَذَكَّرُونَ ﴿٨٠﴾ وَكَيْفَ أَخَافُ مَآ أَشْرَكْتُمْ وَلَا تَخَافُونَ أَنَّكُمْ أَشْرَكْتُم بِٱللَّهِ}[الأنعام: ٨٠ـ ٨١]،

https://www.path-2-happiness.com/am



‹‹ወገኖቹም ተከራከሩት፤በአላህ (አንድነት) በእርግጥ የመራኝ ሲኾን፣ትከራከሩኛላችሁን? በርሱም የምታጋሩትን ነገር አልፈራም፤ግን ጌታዬ ነገርን ቢሻ (ያገኘኛል)፤ጌታዬም ነገሩን ሁሉ ዕውቀቱ ሰፋ፤አትገነዘቡምን? አላቸው:: በናንተ ላይ በርሱ ማስረጃን ያላወረደበትን፣እናንተ ማጋራታችሁን የማትፈሩ ስትኾኑ፣የምታጋሩትን (ጣዖታት) እንዴት እፈራለሁ! የምታውቁም ብትኾኑ ከሁለቱ ክፍሎች (በአንድ አምላክ ከሚያምኑና ከሚያጋሩ) በጸጥታ ይበልጥ ተገቢው ማንኛው ነው? (አለ)::››[አል አንዓም:80-81]

በድጋሜም ለአባታቸውና ለሕዝቡ እንዲህ አሏቸው፦

{إِذۡ قَالَ لِأَبِيهِ وَقَوۡمِهِۦ مَا تَعۡبُدُونَ (٧٠)} [الشعراء: ٧٠]،

‹‹ለአባቱና ለሕዝቦቹ ምንን ትገግገዛላችሁ ባለ ጊዜ፣››[አል ሹዐራ:70]

የተሰጣቸው መልስ ግን አሽፈረን ጣዖታቱን መግገዛት እንቀጥልበታለን የሚል ነበር፦

{قَالُواْ نَعۡبُدُ أَصۡنَامًا فَنَظَلُّ لَهَا عَٰكِفِينَ (٧١)}[الشعراء: ٧١]، {قَالَ هَلۡ يَسۡمَعُونَكُمۡ إِذۡ تَدۡعُونَ (٧٢) أَوۡ يَنفَعُونَكُمۡ أَوۡ يَضُرُّونَ (٧٣)}[الشعراء: ٧٢ـ ٧٣]،

‹‹ጣዖታትን እንግገዛለን፤እርሷንም በመግገዛት ላይ እንቆያለን፤አሉ::››[አል ሹዐራ:71] ‹‹(እርሱም) አለ፦ በጠራችኋቸው ጊዜ ይሰሟችኋልን? ወይስ ይጠቅሟችኋልን? ወይስ ይጎዷችኋልን?››[አል ሹዐራ:73]

ምላሹ በእርግጥ አዙሮ ማየትን የማያውቅ፣ሰብአዊ አእምሮን አውልቆ የሚያስቀምጥ፣አመንክዮን የሚጻረርና ሲሰሩ አይተን ተከተልን በሚል በጭፍን ተከታይነት ላይ የተመሰረተ ጅላጅል ምላሽ ነበር::

{قَالُواْ بَلۡ وَجَدۡنَآ ءَابَآءَنَا كَذَٰلِكَ يَفۡعَلُونَ (٧٤)}[الشعراء: ٧٤]،

‹‹የለም፣አባቶቻችን እንደዚሁ ሲሠሩ አገኘን አሉት::››[አል ሹዐራ:74]

ኢብራሂም በማስረጃዎችና በአመንክዮና በአስተዋይ አእምሮ በተደገፈ የጠራ ተውሒድ መልስ ሰጧቸው፦

{قَالَ أَفَرَءَيۡتُم مَّا كُنتُمۡ تَعۡبُدُونَ (٧٥) أَنتُمۡ وَءَابَآؤُكُمُ ٱلۡأَقۡدَمُونَ (٧٦) فَإِنَّهُمۡ عَدُوّٞ لِّيٓ إِلَّا رَبَّ ٱلۡعَٰلَمِينَ (٧٧) ٱلَّذِي خَلَقَنِي فَهُوَ يَهۡدِينِ (٧٨) وَٱلَّذِي هُوَ يُطۡعِمُنِي وَيَسۡقِينِ (٧٩) وَإِذَا مَرِضۡتُ فَهُوَ يَشۡفِينِ (٨٠) وَٱلَّذِي يُمِيتُنِي ثُمَّ يُحۡيِينِ (٨١) وَٱلَّذِيٓ أَطۡمَعُ أَن يَغۡفِرَ لِي خَطِيٓـَٔتِي يَوۡمَ ٱلدِّينِ (٨٢) رَبِّ هَبۡ لِي حُكۡمٗا وَأَلۡحِقۡنِي بِٱلصَّٰلِحِينَ (٨٣) وَٱجۡعَل لِّي لِسَانَ صِدۡقٖ فِي ٱلۡأٓخِرِينَ (٨٤) وَٱجۡعَلۡنِي مِن وَرَثَةِ جَنَّةِ ٱلنَّعِيمِ (٨٥) وَٱغۡفِرۡ لِأَبِيٓ إِنَّهُۥ كَانَ مِنَ ٱلضَّآلِّينَ (٨٦)}[الشعراء: ٧٥ـ ٨٦].

‹‹እናንተም የቀድሞዎቹ አባቶቻችሁም፣(የተገዛችሁትን)፤እነሱም (ጣዖቶቹ) ለኔ ጠላቶች ናቸው፤ግን የዓለማት ጌታ ሲቀር፣(እርሱ ወዳጄ ነው):: (እርሰሱ) ያ የፈጠረኝ ነው፤እርሱም ይመራኛል:: ያም እርሱ የሚያበላኝና፣የሚያጠጣኝ ነው:: በታመምኩም ጊዜ፣እርሱ ያሽረኛል:: ያም የሚገድለኝ፣ከዚያም ሕያው የሚያደርገኝ፣ነው:: ያም በፍርዱ ቀን ኀጢአቴን ለኔ ሊምር የምከጅለው ነው::ጌታዬ ሆይ! ዕውቀትን ስጠኝ፤በደጋጎቹም ሰዎች አስጠጋኝ:: በኋለኞቹም ሕዝቦች ውስጥ ለኔ መልካም ዝናን አድርግልኝ:: የጸጋይቱን ገነት ከሚወርሱትም አድርገኝ:: ለአባቴም ማር፤እርሱ ከተሳሳቱት ነበረና::››[አል ሹዐራ:75-86]

ሕዝቡና ንጉሣቸው በዓላቸውን ለማክበር ወደ በረሃ ሲወጡ ኢብራሂም አብሯቸው ሳይወጡ ቀሩ::

{فَتَوَلَّوۡاْ عَنۡهُ مُدۡبِرِينَ (٩٠) فَتَوَلَّوۡاْ عَنۡهُ مُدۡبِرِينَ (٩٠) فَرَاغَ إِلَىٰٓ ءَالِهَتِهِمۡ فَقَالَ أَلَا تَأۡكُلُونَ (٩١) مَا لَكُمۡ لَا تَنطِقُونَ (٩٢) فَرَاغَ عَلَيۡهِمۡ ضَرۡبَۢا بِٱلۡيَمِينِ (٩٣)}[الصافات: ٩٠ـ ٩٣]،

‹‹ከርሱም የሸሹ ኾነው ኼዱ:: ወደ አማልክቶቻቸውም ተዘነበለ፤አለም፦ አትበሉምን? የማትናገሩት ለናንተ ምን አላችሁ? በኀይል የሚመታቸውም ኾኖ በነርሱ ላይ በድብቅ ተዘነበለ::››[አል ሷፍፋት:90-93]

ከበዓሉ ስነ ሥርዓት ፍጻሜ በኋላ ሲመለሱ የሚያመልኩባቸው ጣዖቶቻቸውን ተሰባብረው አገኙ:: ራሳቸውን እንኳ ከጥቃት ለመከላከል አቅም የሌላቸው ጣዖታት እንዴት አማልክት መሆን ይችላሉ! እናም እየተጣደፉ መጡና፦

{قَالُواْ مَن فَعَلَ هَٰذَا بِـَٔالِهَتِنَآ إِنَّهُۥ لَمِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ (٥٩) قَالُواْ سَمِعۡنَا فَتٗى يَذۡكُرُهُمۡ يُقَالُ لَهُۥٓ إِبۡرَٰهِيمُ (٦٠) قَالُواْ فَأۡتُواْ بِهِۦ عَلَىٰٓ أَعۡيُنِ ٱلنَّاسِ لَعَلَّهُمۡ يَشۡهَدُونَ (٦١) قَالُوٓاْ ءَأَنتَ فَعَلۡتَ هَٰذَا بِـَٔالِهَتِنَا يَٰٓإِبۡرَٰهِيمُ (٦٢)}[الأنبياء: ٥٩ـ ٦٢]،

‹‹፦ በአማልክቶቻችን ይህንን የሠራ ማነው? እርሱ በእርግጥ ከበደለኞቹ ነው አሉ:: ኢብራሂም የሚባል ጎበዝ፣(በመጥፎ) ሲያነሳቸው ሰምተናል፣ተባባሉ::

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ይመሰክሩበት ዘንድ፣በሰዎቹ ዓይን (ፊት) ላይ አምጡት አሉ:: ኢብራሂም ሆይ! በአማልክቶቻችን ይህንን የሠራህ አንተ ነህን? አሉት:: ››[አል አንቢ.ያ:59-62]

ኢብራሂንምም عليه السلام ማፈናፈኛ የማይሰጥ መልስ ሰጧቸው፦

{قَالَ بَلۡ فَعَلَهُۥ كَبِيرُهُمۡ هَٰذَا فَسۡـَٔلُوهُمۡ إِن كَانُواْ يَنطِقُونَ ۝٦٣}[الأنبياء: ٦٣]؛

‹‹አይደለም፣ይህ ትልቃቸው ሠራው፣ይናገሩም እንደ ኾነ ጠይቋቸው፣አለ::››[አል አንቢ.ያ:63]

በምላሹ ምክንያታዊነትና በአስረጅነቱ፣በሙግቱም ጥንካሬ ፊት የተዋራጅነት ስሜት ተሰማቸው::

{فَرَجَعُوٓاْ إِلَىٰٓ أَنفُسِهِمۡ فَقَالُوٓاْ إِنَّكُمۡ أَنتُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ۝٦٤ ثُمَّ نُكِسُواْ عَلَىٰ رُءُوسِهِمۡ لَقَدۡ عَلِمۡتَ مَا هَٰٓؤُلَآءِ يَنطِقُونَ ۝٦٥}[الأنبياء: ٦٤-٦٥]؛

‹‹ወደ ነፍሶቻቸውም ተመለሱ:: እናንተ (በመጠየቃችሁ) በዳዮች ናችሁም ተባባሉ:: ከዚያም በራሶቻቸው ላይ ተገለበጡ (ወደ መጥፎ ሁኔታቸው ተመለሱ)፤እነዚህ የሚናገሩ አለመኾናቸውን በእርግጥ ዐውቀሃል፤(አሉ)::››[አል አንቢ.ያ:64-65]

ኢብራሂምም በማያፈናፍን ብርቱ አስረጅ ጠየቋቸው፦

{قَالَ أَفَتَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَنفَعُكُمۡ شَيۡـٔٗا وَلَا يَضُرُّكُمۡ ۝٦٦ أُفّٖ لَّكُمۡ وَلِمَا تَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ۝٦٧}[الأنبياء: ٦٦-٦٧]؛

‹‹ታዲያ ለናንተ ምንም የማይጠቅማችሁንና የማይጎዳችሁን ነገር፣ከአላህ ሌላ ትግገዛላችሁን? አላቸው::››[አል አንቢ.ያ:66]

አስተዋይ አእምሮ፣አሳማኝ ማስረጃና ምክንያታዊ መከራከሪያ እንደራቃቸው



ሲረዱ ኢብራሂምን ለመበቀል አሰቡ::

{قَالُواْ حَرِّقُوهُ وَٱنصُرُوٓاْ ءَالِهَتَكُمۡ إِن كُنتُمۡ فَٰعِلِينَ ۝٦٨}[الأنبياء: ٦٨]،

‹‹፦ ሠሪዎች እንደ ኾናችሁ አቃጥሉት፣አማልክቶቻችሁንም እርዱ አሉ:: (በእሳት ላይ ጣሉትም)::››[አል አንቢ.ያ:68]

አላህ (ሱ.ወ.) ግን ነቢዩን አዳናቸው፦

{قُلۡنَا يَٰنَارُ كُونِي بَرۡدٗا وَسَلَٰمًا عَلَىٰٓ إِبۡرَٰهِيمَ ۝٦٩ وَأَرَادُواْ بِهِۦ كَيۡدٗا فَجَعَلۡنَٰهُمُ ٱلۡأَخۡسَرِينَ ۝٧٠}[الأنبياء: ٦٩-٧٠].

‹‹፦ እሳት ሆይ! በኢብራሂም ላይ ቀዝቃዛ፤ሰላም ኹኚ፣አልን:: በርሱም ተንኮልን አሰቡ፤በጣም ከሳሪዎችም አደረግናቸው::››[አል አንቢ.ያ:69-70]

አላህ (ሱ.ወ.) ከጥቃቱ ካዳናቸው በኋላ ኢብራሂም ተመልሰው ከንጉሡ ጋር ተከራከሩ፦

{أَلَمۡ تَرَ إِلَى ٱلَّذِي حَآجَّ إِبۡرَٰهِـۧمَ فِي رَبِّهِۦٓ أَنۡ ءَاتَىٰهُ ٱللَّهُ ٱلۡمُلۡكَ إِذۡ قَالَ إِبۡرَٰهِـۧمُ رَبِّيَ ٱلَّذِي يُحۡيِۦ وَيُمِيتُ}[البقرة: ٢٥٨]،

‹‹ወደዚያ አላህ ንግሥናን ስለ ሰጠው ኢብራሂምን በጌታው ነገር ወደ ተከራከረው አላየህምን? ኢብራሂም፦ ጌታዬ ያ ሕያው የሚያደርግና የሚገድልነው ባለ ጊዜ፣››[አል በቀራህ:258]

ለዚህ ግልጽና አሳማኝ ማስረጃ ጅላጅል ምላሽ ተሰጠ፦

{قَالَ أَنَا۠ أُحۡيِۦ وَأُمِيتُ}[البقرة: ٢٥٨]؛

‹‹እኔ ሕያው አደርጋለሁ፣እገድላለሁም አለ፤››[አል በቀራህ:258]

የፈለገውን ሰው መግደልና የፈለገውንም መተው ለሚለው ለዚህ ጅል የሸሸት ክርክር ኢብራሂም መልስ አልሰጡም::

{قَالَ إِبۡرَٰهِـۧمُ فَإِنَّ ٱللَّهَ يَأۡتِي بِٱلشَّمۡسِ مِنَ ٱلۡمَشۡرِقِ فَأۡتِ بِهَا مِنَ ٱلۡمَغۡرِبِ فَبُهِتَ ٱلَّذِي كَفَرَۗ وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ۝٢٥٨}[البقرة: ٢٥٨]،

‹‹ኢብራሂም፦ አላህ ፀሐይን ከምሥራቅ በኩል ያመጣል፣(አንተ) ከምዕራብ በኩል አምጣት አለው፤ያም የካደው ሰው ዋለለ (መልስ አጣ)፤ አላህም በዳዮች ሕዝቦችን አይመራም::››[አል በቀራህ:258]

በዚህም የከሓዲዎቹ አስረጅና አመንክዮ ምን ያህል ደካማ እንደሆነ ተጋለጠ:: ከክርክሩ በኋላም አላህ (ሱ.ወ.) እንዴት እንደሚፈጥርና እንዴት ሕያው እንደሚያደርግ ኢብራሂም በገዛ ዓይናቸው ለማየት ፈለጉ::

{وَإِذۡ قَالَ إِبۡرَٰهِـۧمُ رَبِّ أَرِنِي كَيۡفَ تُحۡيِ ٱلۡمَوۡتَىٰۖ قَالَ أَوَلَمۡ تُؤۡمِنۖ قَالَ بَلَىٰ وَلَٰكِن لِّيَطۡمَئِنَّ قَلۡبِيۖ قَالَ فَخُذۡ أَرۡبَعَةٗ مِّنَ ٱلطَّيۡرِ فَصُرۡهُنَّ إِلَيۡكَ ثُمَّ ٱجۡعَلۡ عَلَىٰ كُلِّ جَبَلٖ مِّنۡهُنَّ جُزۡءٗا ثُمَّ ٱدۡعُهُنَّ يَأۡتِينَكَ سَعۡيٗاۚ وَٱعۡلَمۡ أَنَّ ٱللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٞ ۝٢٦٠}[البقرة: ٢٦٠].



‹‹ኢብራሂምም ጌታዬ ሆይ! ሙታንን እንዴት ሕያው እንደምታደርግ አሳየኝ ባለ ጊዜ፣(አስታውስ፤አላህ)፦ አላመንክምን? አለው፤አይደለም (አምኛለሁ)፤ግን ልቤ እንዲረጋ ነው አለ፤(አላህም)፦ ከበራሪዎች (ከወፎች) አራትን ያዝ፤ወደ አንተም ሰብስባቸው፤(ቆራርጣቸውም)፤ከዚያም በየኮረብታው ሁሉ ላይ ከነርሱ ቁራጭን አድርግ፤ከዚያም ጥራቸው፤ፈጥነው ይመጡሃልና፤አላህም አሸናፊ ጥበበኛ መኾኑን ዕወቅ አለው።››[አል በቀራህ፡260]

አላህ (ሱ.ወ.) ኢብራሂምንና ልጃቸው እስማዒልን መካ የሚገኘውን የአላህ ማምለኪያ ቤት ከባእድ አምልኮና ከጣዖታት ነጻ እንዲያደርጉ አዘዛቸው።

{وَعَهِدۡنَآ إِلَىٰٓ إِبۡرَٰهِـۧمَ وَإِسۡمَٰعِيلَ أَن طَهِّرَا بَيۡتِيَ لِلطَّآئِفِينَ وَٱلۡعَٰكِفِينَ وَٱلرُّكَّعِ ٱلسُّجُودِ ١٢٥ وَإِذۡ قَالَ إِبۡرَٰهِـۧمُ رَبِّ ٱجۡعَلۡ هَٰذَا بَلَدًا ءَامِنٗا وَٱرۡزُقۡ أَهۡلَهُۥ مِنَ ٱلثَّمَرَٰتِ مَنۡ ءَامَنَ مِنۡهُم بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِۚ قَالَ وَمَن كَفَرَ فَأُمَتِّعُهُۥ قَلِيلٗا ثُمَّ أَضۡطَرُّهُۥٓ إِلَىٰ عَذَابِ ٱلنَّارِۖ وَبِئۡسَ ٱلۡمَصِيرُ ١٢٦ وَإِذۡ يَرۡفَعُ إِبۡرَٰهِـۧمُ ٱلۡقَوَاعِدَ مِنَ ٱلۡبَيۡتِ وَإِسۡمَٰعِيلُ رَبَّنَا تَقَبَّلۡ مِنَّآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ١٢٧ رَبَّنَا وَٱجۡعَلۡنَا مُسۡلِمَيۡنِ لَكَ وَمِن ذُرِّيَّتِنَآ أُمَّةٗ مُّسۡلِمَةٗ لَّكَ وَأَرِنَا مَنَاسِكَنَا وَتُبۡ عَلَيۡنَآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلتَّوَّابُ ٱلرَّحِيمُ ١٢٨}[البقرة: ١٢٥-١٢٨].

‹‹ቤቱንም (የአላህን መገዣ ቤት ከዕባን) ለሰዎች መመለሻና ጸጥተኛ ባደረግን ጊዜ (አስታውስ)፤ከኢብራሂምም መቆሚያ መስገጃን አድርጉ፤ወደ ኢብራሂምና ወደ ኢስማዒልም ቤቴን ለዘዋሪዎቹና ለተቀማጮቹም፣ለአጎንባሽ ሰጋጆችም፣አጥሩ ስንል ቃል ኪዳን ያዝን። ኢብራሂም ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤ጌታዬ ሆይ! ይህንን ጸጥተኛ አገር አድርግ፤ቤተሰቦቹንም ከነሱ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነውን ሰው ከፍሬዎች ስጠው፤(አላህም) ፦ የካደውንም ሰው (እሰጠዋለሁ)፤ጥቂትም እጠቅመዋለሁ፤ከዚያም ወደ እሳት ቅጣት አስጠጋዋለሁ፤ምን ትከፋም መመለሻ! (አለ)። ኢብራሂምና ኢስማዒልም ጌታችን ሆይ! ከኛ ተቀበል፤አንተ ሰሚው፣ዐዋቂው አንተ ነህና የሚሉ ሲኾኑ፣ከቤቱ መሠረቶቹን ከፍ ባደረጉ ጊዜ፣(አስታውስ)። ጌታችን ሆይ! ላንተ ታዛዦችም አድርገን፤ከዘሮቻችንም ላንተ ታዛዦች ሕዝቦችን (አድርግ)፤ሕግጋታችንንም አሳየን (አሳውቀን)፤በኛም ላይ ተመለስልን፤አንተ ጸጸትን ተቀባዩ፣ርኅሩኅ አንተ ብቻ ነህና።››[አል በቀራህ፡125-128]




ፍልስጥኤም ውስጥ በአልኸሊል (ሄብሮን) ከተማ በኢብራሂም መስጊድ የሚገኘው የነብዩ ኢብራሂም عليه السلام መቃብር።





## 3. ነቢዩ ሙሳ عليه السلام ፦

እስራኤላውያን ከኢብራሂም عليه السلام ሲወርድ ሲዋረድ በውርስ የደረሳቸውንና ከዝርያቸው መካከል በሚወለድ ልጅ እጅ የግብጽ ንጉሥ ጥፋት እንደሚከሰት በሚገልታ ትንቢት ላይ ይነጋገሩ ነበር። ይህ የብስራት ትንቢትም በእስራኤላውያን ዘንድ በስፋት የተሰራጨ ስለ ነበር በሹማምንቱ በኩል ነገሩ ወደ ፈርዖን ጆሮ ደረሰ። በዚህን ጊዜ ፈርዖን ትንቢቱን ለማክሸፍ ለእስራኤላውያን የሚወለድ ወንድ ልጅ ሁሉ እንዲገደል ትእዛዝ አስተላለፈ። እስራኤላውያንም ግብጽ ውስጥ የግፍና የሰቆቃ ሕይወት ይገፉ ነበር፦

{إِنَّ فِرۡعَوۡنَ عَلَا فِي ٱلۡأَرۡضِ وَجَعَلَ أَهۡلَهَا شِيَعٗا يَسۡتَضۡعِفُ طَآئِفَةٗ مِّنۡهُمۡ يُذَبِّحُ أَبۡنَآءَهُمۡ وَيَسۡتَحۡيِۦ نِسَآءَهُمۡۚ إِنَّهُۥ كَانَ مِنَ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ٤}[القصص: ٤]،

‹‹ፈርዖን በምድር ላይ ተንበጣረረ፤ነዋሪዎችዋንም የተከፋፈሉ ጓዶች አደረጋቸው፤ከነሱ ጭፍሮችን ያዳክማል፤ወንዶች ልጆቻቸውን በብዛት ያርዳል፤ሴቶቻቸውንም ይተዋል፤እርሱ ከሚያበላሹ ሰዎች ነበርና። ››[አልቀሶስ፡4]

አላህ (ሱ.ወ.) ለግፉአኑ የእስራኤል ልጆች ጸጋውን መዘርጋት ፈለገ፦

{وَنُرِيدُ أَن نَّمُنَّ عَلَى ٱلَّذِينَ ٱسۡتُضۡعِفُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَنَجۡعَلَهُمۡ أَئِمَّةٗ وَنَجۡعَلَهُمُ ٱلۡوَٰرِثِينَ ٥ وَنُمَكِّنَ لَهُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَنُرِيَ فِرۡعَوۡنَ وَهَٰمَٰنَ وَجُنُودَهُمَا مِنۡهُم مَّا كَانُواْ يَحۡذَرُونَ ٦}[القصص: ٥-٦]،

‹‹በነዚያም በምድር ውስጥ በተጨቆኑት ላይ ልንለግስ፤መሪዎችም ልናደርጋቸው፣ወራሾችም ልናደርጋቸው፣እንሻለን። ለነርሱም በምድር ላይ ልናስመች፣ፈርዖንንና ሃማንንም፣ሰራዊቶቻቸውንም፣ከነሱ ይፈሩት የነበሩትን ነገር ልናሳያቸው፣(እንሻለን)።››[አልቀሶስ፡5-6]

እየዞሩ እርጉዝ ሴቶችን ሁሉ የሚከታተሉና መች እንደሚወልዱ የሚያጣሩ ሠራተኞችንና አዋላጆችን እስከማሰማራት ድረስ ፈርዖን ከሙሳ ለመዳን የተሟላ ጥብቅ ጥንቃቄ ቢያደርግም፣ተቆጣጣሪዎቹም ወንድ ሕጻናትን እንደተወለዱ ወዲያውኑ ሲያርዱ ቢቆዩም፣አላህ (ሱ.ወ.) ግን ለፈርዖን ለሹሙና ለሰራዊቶቻቸው የፈሩትን ማሳየት ፈቃዱ ሆነ።

የሙሳ እናት በወለደች ጊዜም፦

{وَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰٓ أُمِّ مُوسَىٰٓ أَنۡ أَرۡضِعِيهِۖ فَإِذَا خِفۡتِ عَلَيۡهِ فَأَلۡقِيهِ فِي ٱلۡيَمِّ وَلَا تَخَافِي وَلَا تَحۡزَنِيٓۖ إِنَّا رَآدُّوهُ



https://www.path-2-happiness.com/am

إِلَيْكِ وَجَاعِلُوهُ مِنَ ٱلْمُرْسَلِينَ ﴿٧﴾} [القصص: ٧]؛

‹‹ወደ ሙሳም እናት፦ አጥቢው፤በርሱም ላይ በፈራሽ ጊዜ በባሕሩ ውስጥ ጣይው፤አትፍሪም፤አትዘኚም፤እኛ ወዳንቺ መላሾቹና ከመልክተኞቹም አድራጊዎቹ ነንና ማለትን አመለከትን፡፡›[አልቀሶስ:7]

እንዳይገድሉት ስለፈራች ሕፃኑን ሳጥን ውስጥ አድርጋው ወደ ወንዝ ጣለችው፦

{فَٱلْتَقَطَهُۥٓ ءَالُ فِرْعَوْنَ لِيَكُونَ لَهُمْ عَدُوًّا وَحَزَنًا ۗ إِنَّ فِرْعَوْنَ وَهَٰمَٰنَ وَجُنُودَهُمَا كَانُوا۟ خَٰطِـِٔينَ ﴿٨﴾} [القصص: ٨]،



‹‹የፈርዖን ቤተሰቦችም (መጨረሻው) ለነርሱ ጠላት ፣ሐዘንም፣ይኾን ዘንድ አነሱት፤ፈርዖንና ሃማንም፣ሰራዊቶቻቸውም ኀጢአተኞች ነበሩ፡፡›[አልቀሶስ:8]

የፈርዖን ሚስት ልብም በሕጻኑ ሙሳ ፍቅር ተጠመደ፦

{وَقَالَتِ ٱمْرَأَتُ فِرْعَوْنَ قُرَّتُ عَيْنٍ لِّى وَلَكَ ۖ لَا تَقْتُلُوهُ عَسَىٰٓ أَن يَنفَعَنَآ أَوْ نَتَّخِذَهُۥ وَلَدًا وَهُمْ لَا يَشْعُرُونَ ﴿٩﴾} [القصص: ٩]،

‹‹የፈርዖንም ሚስት ለኔ የዓይኔ መርጊያ ነው፤ለአንተም፤አትግደሉት፤ሊጠቅመን ወይም ልጅ አድርገን ልንይዘው ይከጀላልና አለች፤እነርሱም (ፍጻሜውን) የማያውቁ ኾነው (አነሱት)፡፡›[አልቀሶስ:9]

የሙሳ እናት ግን፦

{وَأَصْبَحَ فُؤَادُ أُمِّ مُوسَىٰ فَٰرِغًا ۖ إِن كَادَتْ لَتُبْدِى بِهِۦ لَوْلَآ أَن رَّبَطْنَا عَلَىٰ قَلْبِهَا لِتَكُونَ مِنَ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿١٠﴾ وَقَالَتْ لِأُخْتِهِۦ قُصِّيهِ ۖ فَبَصُرَتْ بِهِۦ عَن جُنُبٍ وَهُمْ لَا يَشْعُرُونَ ﴿١١﴾} [القصص: ١٠-١١]، {وَحَرَّمْنَا عَلَيْهِ ٱلْمَرَاضِعَ مِن قَبْلُ فَقَالَتْ هَلْ أَدُلُّكُمْ عَلَىٰٓ أَهْلِ بَيْتٍ يَكْفُلُونَهُۥ لَكُمْ وَهُمْ لَهُۥ نَٰصِحُونَ ﴿١٢﴾ فَرَدَدْنَٰهُ إِلَىٰٓ أُمِّهِۦ كَىْ تَقَرَّ عَيْنُهَا وَلَا تَحْزَنَ وَلِتَعْلَمَ أَنَّ وَعْدَ ٱللَّهِ حَقٌّ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ﴿١٣﴾} [القصص: ١٢-١٣].

‹‹የሙሳም እናት ልብ፣ባዶ ኾነ፤ከምእመናን ትኾን ዘንድ በልቧ ላይ ባላጠነከርን ኖሮ ልትገልጸው ቀርባ ነበር፡፡ ለእኅቱም ተከታተይው አለቻት፤እርሱንም እነሱ የማያውቁ ሲኾኑ በሩቅ ኾና አየችው፡፡›[አልቀሶስ: 10-11] ‹‹(ወደናቱ ከመመለሱ) በፊትም አጥቢዎችን (መጥባትን) በርሱ ላይ እርም አደረግን፤(እኅቱ) ለናንተ የሚያሳድጉላችሁን፣እነርሱም ለርሱ ቅን አገልጋዮች የኾኑን ቤተሰቦች ላመልክታችሁን? አለችም፡፡ ወደናቱም፣ዓይንዋ እንድትረጋ፣እንዳታዝንም፣የአላህም የተስፋ ቃል እርግጥ መኾኑን እንድታውቅ፣መለስነው፤ግን አብዛኞቻቸው አያውቁም፡፡›[አልቀሶስ:12-13]

ሙሳም عليه السلام በግፈኛው ንጉሥ በፈርዖን ቤት አደገ፦

{وَلَمَّا بَلَغَ أَشُدَّهُۥ وَٱسْتَوَىٰٓ ءَاتَيْنَٰهُ حُكْمًا وَعِلْمًا ۚ وَكَذَٰلِكَ نَجْزِى ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿١٤﴾ وَدَخَلَ ٱلْمَدِينَةَ عَلَىٰ حِينِ غَفْلَةٍ مِّنْ أَهْلِهَا فَوَجَدَ فِيهَا رَجُلَيْنِ يَقْتَتِلَانِ هَٰذَا مِن شِيعَتِهِۦ وَهَٰذَا مِنْ عَدُوِّهِۦ ۖ فَٱسْتَغَٰثَهُ ٱلَّذِى مِن شِيعَتِهِۦ عَلَى ٱلَّذِى مِنْ عَدُوِّهِۦ فَوَكَزَهُۥ مُوسَىٰ فَقَضَىٰ عَلَيْهِ ۖ قَالَ هَٰذَا مِنْ عَمَلِ ٱلشَّيْطَٰنِ ۖ إِنَّهُۥ عَدُوٌّ مُّضِلٌّ مُّبِينٌ ﴿١٥﴾ قَالَ رَبِّ إِنِّى ظَلَمْتُ نَفْسِى فَٱغْفِرْ لِى فَغَفَرَ لَهُۥٓ ۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلْغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴿١٦﴾ قَالَ رَبِّ بِمَآ أَنْعَمْتَ عَلَىَّ فَلَنْ أَكُونَ ظَهِيرًا لِّلْمُجْرِمِينَ ﴿١٧﴾} [القصص: ١٤-١٧].......

‹‹ብርታቱንም በደረሰና በተስተካከለ ጊዜ፣ጥበብንና ዕውቀትን ሰጠነው፤እንዲሁም መልካም ሠሪዎችን እንመነዳለን፡፡ ከተማይቱንም፣ሰዎችዋ በዝንጋቴ ጊዜ ላይ ኾነው ሳሉ ገባ፤በርሷም ውስጥ የሚጋደሉን ሁለት ሰዎች አገኘ፤ይህ ከወገኑ ነው፤ይህም ከጠላቱ ነው፤ያም ከወገኑ የኾነው ሰው፣በዚያ ከጠላቱ በኾነው ሰው ላይ እርዳታን ጠየቀው፤ሙሳም በጡጫ መታው፤ገደለውም፤ይህ ከሰይጣን ሥራ ነው፤እርሱ ግልጽ ጠላት ነውና፣አለ፡፡ ጌታዬ ሆይ! እኔ ነፍሴን በደልኩ፤ለኔም ማር አለ፤ለርሱም ምሕረት አደረገለት፤እርሱ መሓሪ፣አዛኝ ነውና፡፡ ጌታዬ ሆይ! በኔ ላይ በመለገስህ ይኹንብኝ (ከስሕተቴ እጸጸታለሁ)፤ለአመጠኞችም ፈጽሞ ረዳት አልኾንም፣አለ፡፡›[አልቀሶስ:14-17]

የራሱና የእስራኤላዊው ጠላት የሆነውን ግለሰብ ከገደለ በኋላ ግን፦

{فَأَصْبَحَ فِى ٱلْمَدِينَةِ خَآئِفًا يَتَرَقَّبُ فَإِذَا ٱلَّذِى ٱسْتَنصَرَهُۥ بِٱلْأَمْسِ يَسْتَصْرِخُهُۥ ۚ قَالَ لَهُۥ مُوسَىٰٓ إِنَّكَ لَغَوِىٌّ مُّبِينٌ ﴿١٨﴾ فَلَمَّآ أَنْ أَرَادَ أَن يَبْطِشَ بِٱلَّذِى هُوَ عَدُوٌّ لَّهُمَا قَالَ يَٰمُوسَىٰٓ أَتُرِيدُ أَن تَقْتُلَنِى كَمَا قَتَلْتَ نَفْسًۢا بِٱلْأَمْسِ ۖ إِن تُرِيدُ إِلَّآ أَن تَكُونَ جَبَّارًا فِى ٱلْأَرْضِ وَمَا تُرِيدُ أَن تَكُونَ مِنَ ٱلْمُصْلِحِينَ ﴿١٩﴾ وَجَآءَ رَجُلٌ مِّنْ أَقْصَا ٱلْمَدِينَةِ يَسْعَىٰ قَالَ يَٰمُوسَىٰٓ إِنَّ ٱلْمَلَأَ يَأْتَمِرُونَ بِكَ لِيَقْتُلُوكَ فَٱخْرُجْ إِنِّى لَكَ مِنَ







https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ٱلنَّٰصِحِينَ ﴿٢٠﴾ فَخَرَجَ مِنۡهَا خَآئِفٗا يَتَرَقَّبُۖ قَالَ رَبِّ نَجِّنِي مِنَ ٱلۡقَوۡمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٢١﴾}[القصص: ١٨ـ ٢١]،

‹‹በከተማይቱም ውስጥ ፈሪ፣የሚጠባበቅ ኾኖ አደረ፤በድንገትም ያ ትላንት እርዳታን የጠየቀው ሰው በጩኸት እርዳታን ይጠይቀዋል፤ሙሳ ለርሱ፦ አንተ በእርግጥ ግልጽ ጠማማ ነህ አለው:: (ሙሳ) ያንን እርሱ ለሁለቱም ጠላት የኾነውን ሰው፣በኀይል ሊይዘው በፈለገም ጊዜ፣ሙሳ ሆይ! በትላንትናው ቀን ነፍስን እንደ ገደልክ፣ልትገድለኝ ትፈልጋለህን? በምድር ላይ ጨካኝ መኾንን እንጅ ሌላ አትፈልግም፤ከመልካም ሠሪዎችም መኾንን አትፈልግም፤አለው:: ከከተማይቱም ዳርቻ አንድ ሰው እየሮጠ መጣ፤ሙሳ ሆይ! ሹማምንቶቹ ሊገድሉህ ባንተ ይመካከራሉና ውጣ፤እኔ ላንተ ከመካሪዎች ነኝና አለው:: የፈራና የሚጠባበቅ ኾኖም ከርሷ ወጣ፤ጌታዬ ሆይ! ከበደለኞቹ ሕዝቦች አድነኝ አለ::››[አልቀሶስ:18-21]

ግብጽን ለቆ ወደ መድየን አቅጣጫ አመራ፦

{وَلَمَّا تَوَجَّهَ تِلۡقَآءَ مَدۡيَنَ قَالَ عَسَىٰ رَبِّيٓ أَن يَهۡدِيَنِي سَوَآءَ ٱلسَّبِيلِ ﴿٢٢﴾ وَلَمَّا وَرَدَ مَآءَ مَدۡيَنَ وَجَدَ عَلَيۡهِ أُمَّةٗ مِّنَ ٱلنَّاسِ يَسۡقُونَ وَوَجَدَ مِن دُونِهِمُ ٱمۡرَأَتَيۡنِ تَذُودَانِۖ قَالَ مَا خَطۡبُكُمَاۖ قَالَتَا لَا نَسۡقِي حَتَّىٰ يُصۡدِرَ ٱلرِّعَآءُۖ وَأَبُونَا شَيۡخٞ كَبِيرٞ ﴿٢٣﴾ فَسَقَىٰ لَهُمَا ثُمَّ تَوَلَّىٰٓ إِلَى ٱلظِّلِّ فَقَالَ رَبِّ إِنِّي لِمَآ أَنزَلۡتَ إِلَيَّ مِنۡ خَيۡرٖ فَقِيرٞ ﴿٢٤﴾}[القصص: ٢٢ـ ٢٤]،

‹‹ወደ መድየን አግጣጫ ፊቱን ባዞረ ጊዜም፣ጌታዬ ቀጥተኛውን መንገድ ሊመራኝ እከጅላለሁ አለ:: ወደ መድየንም ውሃ በመጣ ጊዜ፣በርሱ ላይ ከሰዎች ጭፍሮችን (መንጋዎቻቸውን) የሚያጠጡ ኾነው አገኘ፤ከነሱ በታችም (ከውሃው መንጎቻቸውን) የሚከለክሉን ሁለት ሴቶች አገኘ፤ነገራችሁ ምንድን ነው? አላቸው፤እረኞቹ ሁሉ (መንጎቻቸውን) እስከሚመልሱ አናጠጣም፤አባታችንም ትልቅ ሽማግሌ ነው አሉት:: ለሁለቱም አጠጣላቸው፤ከዚያም ወደ ጥላው ዘወር አለ፤ጌታዬ ሆይ! እኔ ከመልካም ነገር ወደኔ ለምታደርገው ፈላጊ ነኝ፣አለ::››[አልቀሶስ:22-24]

https://www.path-2-happiness.com/am





ሁለቱ ሴቶች ሙሳ የሰራውን በጎ ሥራ ለአባታቸው ለነቢዩ ሹዐይብ عليه السلام ተናገሩ:: ሹዐይብም ሙሳን عليه السلام ትጠራው ዘንድ አንደኛቱን ልጃቸውን ላኩ፦

{فَجَآءَتۡهُ إِحۡدَىٰهُمَا تَمۡشِي عَلَى ٱسۡتِحۡيَآءٖ قَالَتۡ إِنَّ أَبِي يَدۡعُوكَ لِيَجۡزِيَكَ أَجۡرَ مَا سَقَيۡتَ لَنَا}[القصص: ٢٥]،

‹‹ከሁለቱ አንደኛይቱም ከሕፍረት ጋር የምትኼድ ኾና መጣችው፤አባቴ ለኛ ያጠጣህልንን ዋጋ ሊሰጥህ ይጠረሃል፣አለችው፤››[አልቀሶስ:25]

ሙሳም [የአላህ ሰላም በሁለቱም ላይ ይሁን] ወደ ሹዐይብ መጡ::

{فَلَمَّا جَآءَهُۥ وَقَصَّ عَلَيۡهِ ٱلۡقَصَصَ قَالَ لَا تَخَفۡۖ نَجَوۡتَ مِنَ ٱلۡقَوۡمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٢٥﴾}[القصص: ٢٥]،

‹‹ወደርሱ በመጣና ወሬውን በርሱ ላይ በተረከለትም ጊዜ፣አትፍራ፤ከበደለኞቹ ሕዝቦች ድነሃል አለው::››[አልቀሶስ:25]

ልጅቱ የሙሳን عليه السلام ታማኝነት ባስተዋለች ጊዜ፦

{قَالَتۡ إِحۡدَىٰهُمَا يَٰٓأَبَتِ ٱسۡتَـٔۡجِرۡهُۖ إِنَّ خَيۡرَ مَنِ ٱسۡتَـٔۡجَرۡتَ ٱلۡقَوِيُّ ٱلۡأَمِينُ ﴿٢٦﴾}[القصص: ٢٦]،

‹‹ከሁለቱ አንደኛይቱም አባቴ ሆይ! ቅጠረው፤ከቀጠርከው ሰው ሁሉ በላጩ፣ብርቱው፣ታማኙ፣ ነውና አለችው::››[አልቀሶስ:26]

ሹዐይብም ለሙሳ [የአላህ ሰላም በሁለቱም ላይ ይሁን] ፦

{قَالَ إِنِّيٓ أُرِيدُ أَنۡ أُنكِحَكَ إِحۡدَى ٱبۡنَتَيَّ هَٰتَيۡنِ عَلَىٰٓ أَن تَأۡجُرَنِي ثَمَٰنِيَ حِجَجٖۖ فَإِنۡ أَتۡمَمۡتَ عَشۡرٗا فَمِنۡ عِندِكَۖ وَمَآ أُرِيدُ أَنۡ أَشُقَّ عَلَيۡكَۚ سَتَجِدُنِيٓ إِن شَآءَ ٱللَّهُ مِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿٢٧﴾ قَالَ ذَٰلِكَ بَيۡنِي وَبَيۡنَكَۖ أَيَّمَا ٱلۡأَجَلَيۡنِ قَضَيۡتُ فَلَا عُدۡوَٰنَ عَلَيَّۖ وَٱللَّهُ عَلَىٰ مَا نَقُولُ وَكِيلٞ ﴿٢٨﴾}[القصص: ٢٧ـ ٢٨].

‹‹ስምንትን ዓመታት ልታገለግለኝ፣እኔ ከነዚህ ሁለት ሴቶች ልጆቼ አንዲቱን ላጋባህ እሻለሁ፤ዐሥርን ብትሞላም ከአንተ ነው፤ባንተ ላይ ማስቸገርንም አልሻም፤አላህ የሻ እንደኾነ ከመልካሞቹ ሰዎች ኾኜ ታገኘኛለህ አለው::



(ሙሳም) ይህ፣(ውለታ) በኔና ባንተ መካከል (ረጊ) ነው፣ከሁለቱ ጊዜያቶች ማንኛውንም ብፈጽም፣በኔ ላይ ወሰን ማለፍ የለም፤አላህም በምንለው ላይ ምስክር ነው አለ::››[አልቀሶስ:27-28]

የተስማሙበትን የሥራ ጊዜ ካጠናቀቁ በኋላ ሙሳ ﷺ ቤተሰባቸውን ይዘው ተጓዙ፦

{فَلَمَّا قَضَىٰ مُوسَى ٱلْأَجَلَ وَسَارَ بِأَهْلِهِۦٓ ءَانَسَ مِن جَانِبِ ٱلطُّورِ نَارًاۖ قَالَ لِأَهْلِهِ ٱمْكُثُوٓاْ إِنِّيٓ ءَانَسْتُ نَارًا لَّعَلِّيٓ ءَاتِيكُم مِّنْهَا بِخَبَرٍ أَوْ جَذْوَةٍ مِّنَ ٱلنَّارِ لَعَلَّكُمْ تَصْطَلُونَ ﴿٢٩﴾}[القصص: ٢٩]،

‹‹ሙሳም ጊዜውን በጨረሰና ከቤተሰቦቹ ጋር በኼደ ጊዜ፣ከጡር ተራራ ጎን እሳትን አየ፤ለቤተሰቡ (እዚህ) ቆዩ፤እኔ እሳትን አየሁ፤ከርሷ ወሬን ወይም ትሞቁ ዘንድ ከእሳት ትንታግን አመጣላችኋለሁ አለ::››[አልቀሶስ:29]

በዚህን ጊዜ አላህ (ሱ.ወ.) ወሕይ ላከባቸው፦

{فَلَمَّآ أَتَىٰهَا نُودِيَ مِن شَٰطِيِٕ ٱلْوَادِ ٱلْأَيْمَنِ فِي ٱلْبُقْعَةِ ٱلْمُبَٰرَكَةِ مِنَ ٱلشَّجَرَةِ أَن يَٰمُوسَىٰٓ إِنِّيٓ أَنَا ٱللَّهُ رَبُّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٣٠﴾ وَأَنْ أَلْقِ عَصَاكَۚ فَلَمَّا رَءَاهَا تَهْتَزُّ كَأَنَّهَا جَآنٌّ وَلَّىٰ مُدْبِرًا وَلَمْ يُعَقِّبْۚ يَٰمُوسَىٰٓ أَقْبِلْ وَلَا تَخَفْۖ إِنَّكَ مِنَ ٱلْءَامِنِينَ ﴿٣١﴾ ٱسْلُكْ يَدَكَ فِي جَيْبِكَ تَخْرُجْ بَيْضَآءَ مِنْ غَيْرِ سُوٓءٍ وَٱضْمُمْ إِلَيْكَ جَنَاحَكَ مِنَ ٱلرَّهْبِۖ فَذَٰنِكَ بُرْهَٰنَانِ مِن رَّبِّكَ إِلَىٰ فِرْعَوْنَ وَمَلَإِيْهِۦٓۚ إِنَّهُمْ كَانُواْ قَوْمًا فَٰسِقِينَ ﴿٣٢﴾}[القصص: ٣٠-٣٢]،

‹‹በመጣትም ጊዜ፣ከሸለቆው ቀኝ ዳርቻ፣ከዛፊቱ በኩል በተባረከችው ስፍራ ውስጥ ሙሳ ሆይ! እኔ የዓለማት ጌታ አላህ ነኝ በማለት ተጣራ:: በትርህንም ጣል (ተባለ)፤እንደ ትንሽ እባብ ስትስለከለክ ባያትም ጊዜ፣ወደ ኋላ ዞሮ ሸሸ፤አልተመለሰምም፤ሙሳ ሆይ! ተመለስ፤አትፍራም፤አንተ ከጥብቆቹ ነህና (ተባለም):: እጅህን በአንገትጌህ ውስጥ አግባ፤ያለ ነውር ነጭ ኾና ትወጣለችና፤ክንፍህንም ከፍርሃት (ለመዳን) ወዳንተ አጣብቅ፤እነዚህም ከጌታህ የኾኑ ወደ ፈርዖንና ወደ መኳንንቶቹ የሚደርሱ ሁለት አስረጅዎች ናቸው፤እነርሱ አመጠኞች ሕዝቦች ነበሩና::››[አልቀሶስ:30-32]

ነቢዩ ሙሳ ﷺ ግን ቀደም ሲል በገደሉት ጠላታቸውና ባልተባ ምላሳቸው ምክንያት ፈርዖንን ፈሩ፦

{قَالَ رَبِّ إِنِّي قَتَلْتُ مِنْهُمْ نَفْسًا فَأَخَافُ أَن يَقْتُلُونِ ﴿٣٣﴾ وَأَخِي هَٰرُونُ هُوَ أَفْصَحُ مِنِّي لِسَانًا فَأَرْسِلْهُ مَعِيَ رِدْءًا يُصَدِّقُنِيٓۖ إِنِّيٓ أَخَافُ أَن يُكَذِّبُونِ ﴿٣٤﴾}[القصص: ٣٣-٣٤]،

‹‹(ሙሳ) አለ፦ ጌታዬ ሆይ! እኔ ከነሱ ነፍስን ገድያለሁ፣ስለዚህ እንዳይገድሉኝ እፈራለሁ፤ወንድሜም ሃሩን እርሱ ምላሱ ከኔ የተባ ነው፤እውነተኛነቴንም የሚያረጋግጥልኝ ረዳት ኾኖ ከኔ ጋር ላከው፤እኔ ሊያስተባብሉኝ እፈራለሁና::››[አልቀሶስ:33-34]

ወንድማቸው ሃሩንን ረዳታቸው ያደርግ ዘንድም አላህን (ሱ.ወ.) ለመኑ፦

{وَٱجْعَل لِّي وَزِيرًا مِّنْ أَهْلِي ﴿٢٩﴾ هَٰرُونَ أَخِي ﴿٣٠﴾ ٱشْدُدْ بِهِۦٓ أَزْرِي ﴿٣١﴾ وَأَشْرِكْهُ فِيٓ أَمْرِي ﴿٣٢﴾ كَيْ نُسَبِّحَكَ كَثِيرًا ﴿٣٣﴾ وَنَذْكُرَكَ كَثِيرًا ﴿٣٤﴾ إِنَّكَ كُنتَ بِنَا بَصِيرًا ﴿٣٥﴾ قَالَ قَدْ أُوتِيتَ سُؤْلَكَ يَٰمُوسَىٰ ﴿٣٦﴾}[طه: ٢٩-٣٦].

‹‹ከቤተሰቦቼም ለኔ ረዳትን አድርግልኝ፤ሃሩንን ወንድሜን:: ኀይሌን በርሱ አበርታልኝ:: በነገሬም አጋራው:: በብዙ እናጠራህ ዘንድ:: በብዙም እንድናወሳህ:: አንተ በኛ ነገር ዐዋቂ ነህና:: (አላህም) አለ፦ ሙሳ ሆይ! ልመናህን በእርግጥ ተሰጠህ::››[ጣሃ:29-36]

ሙሳና ሃሩን ወደ ፈርዖን ሄደው አንድ አላህን ብቻ መግገዛትን፣በርሱ አለማጋራትን፣እስራኤላውያንን በፈለጉበት ቦታ አንድ አላህን ብቻ መግገዛት ይችሉ ዘንድ ከጭቆና አገዛዙ ነጻ መልቀቅን በተመለከተ የተላኩበትን የአላህን (ሱ.ወ.) መልእክት አደረሱት:: ፈርዖንም በትእቢት ተወጥሮ በመኩራራት ሙሳን በንቀት ዓይን ተመለከተ:: እንዲህም አለ፦

{أَلَمْ نُرَبِّكَ فِينَا وَلِيدًا وَلَبِثْتَ فِينَا مِنْ عُمُرِكَ سِنِينَ ﴿١٨﴾ وَفَعَلْتَ فَعْلَتَكَ ٱلَّتِي فَعَلْتَ وَأَنتَ مِنَ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿١٩﴾}[الشعراء: ١٨-١٩]،

‹‹(ፈርዖንም) አለ ፦ ልጅ ኾነህ በኛ ውስጥ አላሳደግንህምን? በኛ ውስጥም ከዕድሜህ ብዙ ዓመታትን አልተቀመጥክምን? ያችንም የሠራሃትን ሥራህን አልሠራህምን? አንተም ከውለታ ቢሶቹ ነህ (አለ)::››[አል ሹዐራ:18-19]

ሙሳም ﷺ መልስ ሰጡት፦

{قَالَ فَعَلْتُهَآ إِذًا وَأَنَا۠ مِنَ ٱلضَّآلِّينَ ﴿٢٠﴾}[الشعراء: ٢٠]؛

‹‹(ሙሳም) አለ፦ ያን ጊዜ እኔም ከተሳሳቱት ኾኜ ሠራኋት::››[አል ሹዐራ:20]

ያን የፈጸምኩት የአላህ መልክት ሳይመጣልኝና ወሕይ ሳይገለጥልኝ በፊት ነው፣አሉት::

{فَفَرَرْتُ مِنكُمْ لَمَّا خِفْتُكُمْ فَوَهَبَ لِي رَبِّي حُكْمًا وَجَعَلَنِي مِنَ ٱلْمُرْسَلِينَ ﴿٢١﴾}[الشعراء: ٢١]،

‹‹በፈራኋችሁም ጊዜ ከናንተ ሸሸሁ፤ጌታየም ለኔ ጥበብን ሰጠኝ፤ከመልክተኞቹም

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

አደረገኝ፡፡››[አል ሹዐራ፡21]

በማሳደግና በመንከባከብ ስላደረገላቸው ውለታ ፈርዖን ሲመጻደቅ ሙሳ ﵇ መልስ ሰጡት፡፡

{وَتِلْكَ نِعْمَةٌ تَمُنُّهَا عَلَيَّ أَنْ عَبَّدتَّ بَنِي إِسْرَائِيلَ ﴿٢٢﴾}[الشعراء: ٢٢]؛

‹‹ይህችም፣የእስራኤልን ልጆች ባሪያ በማድረግህ በኔ ላይ የምትመጻደቅባት ጸጋ ናት፡፡››[አል ሹዐራ፡22]

መላውን የእስራኤል ሕዝብ በባርነት ይዘህ ጉልበታቸውን በመበዝበዝና በመጨቆን ለዘመናት የሰቆቃ ሕይወት እንዲመሩ እያደረግህ፣ለኔ ለአንዱ እስራኤላዊ ብቻ በዋልከው ውለታ አትመጻደቅ፣አሉት፡፡ በመቀጠልም ሙሳ ላከኝ የሚሉት ጌታ አምላክ የቱ እንደሆነ ፈርዖን ጠየቃቸው፡፡

{قَالَ فِرْعَوْنُ وَمَا رَبُّ الْعَالَمِينَ ﴿٢٣﴾}[الشعراء: ٢٣]،

‹‹ፈርዖን አለ፦ (ላከኝ የምትለው) የዓለማትም ጌታ ምንድነው?››[አል ሹዐራ፡23]

አሳማኝ መልስም ተሰጠው፦

{قَالَ رَبُّ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا إِن كُنتُم مُّوقِنِينَ ﴿٢٤﴾}[الشعراء: ٢٤]،

‹‹(ሙሳ) ፦ የሰማያትና የምድር፣በመካከላቸውም ያለው ሁሉ ጌታ ነው፤የምታረጋግጡ ብትኾኑ (ነገሩ ይህ ነው)፤አለው፡፡››[አል ሹዐራ፡24]

ፈርዖንም መሳለቅ ጀመረ፡፡

{قَالَ لِمَنْ حَوْلَهُ أَلَا تَسْتَمِعُونَ ﴿٢٥﴾}[الشعراء: ٢٥]،

‹‹(ፈርዖንም) በዙሪያው ላሉት ሰዎች፦ አትሰሙምን? አለ፡፡››[አል ሹዐራ፡25]

ሙሳም ﵇ ለማንም ቁብ ሳይሰጡ ጥሪያቸውን ቀጠሉ፡፡

{قَالَ رَبُّكُمْ وَرَبُّ آبَائِكُمُ الْأَوَّلِينَ ﴿٢٦﴾}[الشعراء: ٢٦]،

‹‹(ሙሳ)፦ ጌታችሁና የመጀመሪያዎቹ አባቶቻችሁም ጌታ ነው አለው፡፡››[አል ሹዐራ፡26]

ፈርዖን በትእቢቱ ገፋበት፦

{قَالَ إِنَّ رَسُولَكُمُ الَّذِي أُرْسِلَ إِلَيْكُمْ لَمَجْنُونٌ ﴿٢٧﴾}[الشعراء: ٢٧]،

‹‹(ፈርዖን) ፦ ያ ወደናንተ የላከው መልክተኛችሁ፣በእርግጥ ዕብድ ነው፤አለ፡፡››[አል ሹዐራ፡27]

የአላህ መልክተኛ ሙሳ ግን ከዓላማቸው ፍንክች





አላሉም ፦

{قَالَ رَبُّ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَمَا بَيْنَهُمَا إِن كُنتُمْ تَعْقِلُونَ ﴿٢٨﴾}[الشعراء: ٢٨]،

‹‹(ሙሳ)፦ የምሥራቅና የምዕራብ፣በመካከላቸውም ያለው ነገር ሁሉ ጌታ ነው፣ታውቁ እንደ ኾናችሁ፣(እመኑበት) አለው፡፡››[አል ሹዐራ፡28]

ከማስረጃ ከአመዛዛኝ አእምሮም ሆነ ከአመክዮ የተራቆተው አምባገነኑ ትእቢተኛ ገዥ ፈርዖን ማስፈራራት ጀመረ፡፡

{قَالَ لَئِنِ اتَّخَذْتَ إِلَٰهًا غَيْرِي لَأَجْعَلَنَّكَ مِنَ الْمَسْجُونِينَ ﴿٢٩﴾}[الشعراء: ٢٩]،

‹‹(ፈርዖን)፦ ከኔ ሌላ አምላክን ብትይዝ በውነቱ ከእስረኞቹ አደርግሃለሁ አለ፡፡››[አል ሹዐራ፡29]

በፈርዖን ሹፈትና በስላቁ ጥሪውን ያላቆሙት ሙሳ ﵇፣በፈርዖን ማስፈራሪያም አልተበገሩም፡፡ መልስ ሰጡት፦

{قَالَ أَوَلَوْ جِئْتُكَ بِشَيْءٍ مُّبِينٍ ﴿٣٠﴾ قَالَ فَأْتِ بِهِ إِن كُنتَ مِنَ الصَّادِقِينَ ﴿٣١﴾ فَأَلْقَىٰ عَصَاهُ فَإِذَا هِيَ ثُعْبَانٌ مُّبِينٌ ﴿٣٢﴾ وَنَزَعَ يَدَهُ فَإِذَا هِيَ بَيْضَاءُ لِلنَّاظِرِينَ ﴿٣٣﴾}[الشعراء: ٣٠-٣٤]،

‹‹(ሙሳ)፦ በግልጽ አስረጅ ብመጣህም እንኳ? አለው፡፡ እንግዲያውስ ከውነተኞች እንደ ኾንክ (አስረጁን) አምጣው አለ፡፡ በትሩንም ጣለ፤እርሷም ወዲያውኑ ግልጽ እባብ ኾነች፡፡ እጁንም አወጣ፤ወዲያውም እርሷ ለተመልካቾች (የምታበራ) ነጭ ኾነች፡፡›› [አል ሹዐራ፡30-33]

ሕዝቡ በሙሳ ﵇ እንዳያምን ፈርዖን ስጋት ላይ ወደቀ፡፡

{قَالَ لِلْمَلَإِ حَوْلَهُ إِنَّ هَٰذَا لَسَاحِرٌ عَلِيمٌ ﴿٣٤﴾ يُرِيدُ أَن يُخْرِجَكُم مِّنْ أَرْضِكُم بِسِحْرِهِ فَمَاذَا تَأْمُرُونَ ﴿٣٥﴾ قَالُوا أَرْجِهْ وَأَخَاهُ وَابْعَثْ فِي الْمَدَائِنِ حَاشِرِينَ ﴿٣٦﴾ يَأْتُوكَ بِكُلِّ سَحَّارٍ عَلِيمٍ ﴿٣٧﴾}[الشعراء: ٣٤-٣٧].

‹‹(ፈርዖን) በዙሪያው ላሉት መማክርት፣ይህ በእርግጥ ዐዋቂ ድግምተኛ ነው፤አለ፡፡ ከምድራችሁ በድግምቱ ሊያወጣችሁ ይፈልጋልና ምንን ታዛላችሁ? (አላቸው)፡፡ አሉት፦ እርሱን ወንድሙንም አቆይና በየከተሞቹ፣ሰብሳቢዎችን ላክ፡፡ በጣም ዐዋቂ ድግምተኞችን ሁሉ ያመጡልሃልና፡፡››[አል ሹዐራ፡34-37]

ፈርዖን ሁሉንም አሳማኝ ማስረጃዎች ካየ በኋላም ማስተባበሉንና ክህደቱን በእብሪት ቀጠለ፡፡

{وَلَقَدْ أَرَيْنَاهُ آيَاتِنَا كُلَّهَا فَكَذَّبَ وَأَبَىٰ ﴿٥٦﴾ قَالَ أَجِئْتَنَا لِتُخْرِجَنَا مِنْ أَرْضِنَا بِسِحْرِكَ يَا مُوسَىٰ ﴿٥٧﴾ فَلَنَأْتِيَنَّكَ بِسِحْرٍ مِّثْلِهِ فَاجْعَلْ بَيْنَنَا وَبَيْنَكَ مَوْعِدًا لَّا



https://www.path-2-happiness.com/am

نُخْلِفُهُۥ نَحْنُ وَلَآ أَنتَ مَكَانًا سُوًى ﴿٥٨﴾ قَالَ مَوْعِدُكُمْ يَوْمُ ٱلزِّينَةِ وَأَن يُحْشَرَ ٱلنَّاسُ ضُحًى ﴿٥٩﴾ فَتَوَلَّىٰ فِرْعَوْنُ فَجَمَعَ كَيْدَهُۥ ثُمَّ أَتَىٰ ﴿٦٠﴾}[طه: ٥٦- ٦٠]،

‹‹ታምራቶቻችንንም ሁሏንም (ለፈርዖን) በእርግጥ አሳየነው፤አስተባበለም፤እምቢም አለ:: ከምድራችን በድግምትህ ልታወጣን መጣህብን? ሙሳ ሆይ! አለ:: መሰሉንም ድግምት እናመጣብሃለን፤በኛና ባንተም መካከል እኛም አንተም የማንጥሰው የኾነ ቀጠሮን፣በመካከለኛ ስፍራ አድርግልን፣አለ:: ቀጠሯችሁ በማጌጫው ቀን ሰዎቹም በረፋድ በሚሰበሰቡበት ነው አለ:: ፈርዖንም ዞረ፤ተንኮሉንም ሰበሰበ፤ከዚያም መጣ::››[ጣሃ:56-60]

ሙሳ ﷺ በሕዝቡ ላይ የአላህ (ሱ.ወ.) ቅጣት እንዳይወርድ ፈሩላቸው::

{قَالَ لَهُم مُّوسَىٰ وَيْلَكُمْ لَا تَفْتَرُوا۟ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا فَيُسْحِتَكُم بِعَذَابٍ ۖ وَقَدْ خَابَ مَنِ ٱفْتَرَىٰ ﴿٦١﴾}[طه: ٦١]؛

‹‹ሙሳ ለነሱ አላቸው ፦ ወዮላችሁ በአላህ ላይ ውሸትን አትቅጠፉ፤በቅጣት ያጠፋችኋልና፤የቀጠፈም ሰው በእርግጥ አፈረ::››[ጣሃ:61]

የፈርዖን ድግምተኞች በሀሳብ ተለያዩ፤አንዳንዶቻቸው ይህ የድግምተኛ ጠንቋይ ንግግር አይደለም አሉ::

{فَتَنَٰزَعُوٓا۟ أَمْرَهُم بَيْنَهُمْ وَأَسَرُّوا۟ ٱلنَّجْوَىٰ ﴿٦٢﴾}[طه: 62].

‹‹(ድግምተኞቹ) በመካከላቸውም ነገራቸውን ተጨቃጨቁ፤ውይይትንም ደበቁ::››[ጣሃ:62]

ይሁን እንጂ አብዛኞቻቸው ከአቋማቸው ተመለሱና፦

{قَالُوٓا۟ إِنْ هَٰذَٰنِ لَسَٰحِرَٰنِ يُرِيدَانِ أَن يُخْرِجَاكُم مِّنْ أَرْضِكُم بِسِحْرِهِمَا وَيَذْهَبَا بِطَرِيقَتِكُمُ ٱلْمُثْلَىٰ ﴿٦٣﴾ فَأَجْمِعُوا۟ كَيْدَكُمْ ثُمَّ ٱئْتُوا۟ صَفًّا ۚ وَقَدْ أَفْلَحَ ٱلْيَوْمَ مَنِ ٱسْتَعْلَىٰ ﴿٦٤﴾}[طه: ٦٣- ٦٤].

{قَالُوا۟ يَٰمُوسَىٰٓ إِمَّآ أَن تُلْقِىَ وَإِمَّآ أَن نَّكُونَ أَوَّلَ مَنْ أَلْقَىٰ ﴿٦٥﴾ قَالَ بَلْ أَلْقُوا۟ ۖ فَإِذَا حِبَالُهُمْ وَعِصِيُّهُمْ يُخَيَّلُ إِلَيْهِ مِن سِحْرِهِمْ أَنَّهَا تَسْعَىٰ ﴿٦٦﴾}[طه: ٦٦]؛

‹‹እነዚህ በእርግጥ ደጋሚዎች ናቸው፤ከምድራችሁ በድግምታቸው ሊያወጧችሁ፣በላጭቱንም መንገዳችሁን ሊያስወግዱባችሁ ይሻሉ አሉ:: ተንኮላችሁንም አጠንክሩ፤ከዚያም ተሰልፋችሁ ኑ፤ዛሬ ያሸነፈም ሰው ምኞቱን አገኘ (ተባባሉ)::›[ጣሃ:63-64] ‹‹ሙሳ ሆይ! ወይ ትጥላለህ፣ወይም በመጀመሪያ የምንጥል እንኾናለን፣(ምረጥ) አሉ:: አይደለም ጣሉ፣አላቸው፤ወዲያውም ገመዶቻቸውና ዘንጎቻቸው ከድግምታቸው የተነሳ እነርሱ የሚሮጡ (እባቦች) ኾነው ወደርሱ ተመለሱ::››[ጣሃ:65-66]

ሙሳም ﷺ ሕዝቡ በድግምተኛ ጠንቋዮች እንዳይፈታተን ሰጋ::

{فَأَوْجَسَ فِى نَفْسِهِۦ خِيفَةً مُّوسَىٰ ﴿٦٧﴾}[طه: ٦٧]،

‹‹ሙሳም በነፍሱ ውስጥ ፍርሃትን አሳደረ::››[ጣሃ:67]

ከአላህ (ሱ.ወ.) ዘንድም ትእዛዝ መጣላቸው፦





{قُلْنَا لَا تَخَفْ إِنَّكَ أَنتَ ٱلْأَعْلَىٰ ﴿٦٨﴾ وَأَلْقِ مَا فِى يَمِينِكَ تَلْقَفْ مَا صَنَعُوٓا۟ ۖ إِنَّمَا صَنَعُوا۟ كَيْدُ سَٰحِرٍ ۖ وَلَا يُفْلِحُ ٱلسَّاحِرُ حَيْثُ أَتَىٰ ﴿٦٩﴾}[طه: ٦٨- ٦٩]، {وَأَوْحَيْنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰٓ أَنْ أَلْقِ عَصَاكَ ۖ فَإِذَا هِىَ تَلْقَفُ مَا يَأْفِكُونَ ﴿١١٧﴾ فَوَقَعَ ٱلْحَقُّ وَبَطَلَ مَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴿١١٨﴾}[الأعراف: ١١٧- ١١٨]،

‹‹፦ አትፍራ አንተ የበላዩ አንተ ነህና አልነው:: በቀኝ እጅህ ያለችውንም በትር በጣል፤ያንን የሠሩትን ትውጣለችና፤ያ የሠሩት ሁሉ የድግምተኛ ተንኮል ነውና፤ድግምተኛ በመጣበት ስፍራ ሁሉ አይቀናውም (አልን)::››[ጣሃ:68-69] ‹‹ወደ ሙሳም፦በትርህን ጣል ስንል ላክን፤(ጣላትም) ወዲያውኑም የሚቀጣጥፉትን (ማታለያ) ትውጣለች:: እውነቱም ተገለጸ፤ይሠሩት የነበሩትም (ድግምት) ተበላሸ::››[አልአዕራፍ:117-118]

ያልተጠበቀ ታምር ተከሰተ፦

{فَغُلِبُوا۟ هُنَالِكَ وَٱنقَلَبُوا۟ صَٰغِرِينَ ﴿١١٩﴾ وَأُلْقِىَ ٱلسَّحَرَةُ سَٰجِدِينَ ﴿١٢٠﴾ قَالُوٓا۟ ءَامَنَّا بِرَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿١٢١﴾ رَبِّ مُوسَىٰ وَهَٰرُونَ ﴿١٢٢﴾}[الأعراف: ١١٩- ١٢٢]، {فَأُلْقِىَ ٱلسَّحَرَةُ سُجَّدًا قَالُوٓا۟ ءَامَنَّا بِرَبِّ هَٰرُونَ وَمُوسَىٰ ﴿٧٠﴾}[طه: ٧٠]،

‹‹እዚያ ዘንድ ተሸነፉም፤ወራዶችም ኾነው ተመለሱ:: ድግምተኞቹም ሰጋጆች ኾነው ወደቁ:: አሉ፦ በዓለማት ጌታ አመንን፤በሙሳና በሃሩን ጌታ::››[አልአዕራፍ:119-122] ‹‹ድግምተኞቹም ሰጋጆች ኾነው ወደቁ፤በሃሩንና በሙሳ ጌታ አመንን፣አሉ::››[ጣሃ:70]

የፈርዖን ምላሽም የጅላጅል ማስፈራሪያ ብቻ ነበር::

{قَالَ ءَامَنتُمْ لَهُۥ قَبْلَ أَنْ ءَاذَنَ لَكُمْ ۖ إِنَّهُۥ لَكَبِيرُكُمُ ٱلَّذِى عَلَّمَكُمُ ٱلسِّحْرَ ۖ فَلَأُقَطِّعَنَّ أَيْدِيَكُمْ وَأَرْجُلَكُم مِّنْ خِلَٰفٍ وَلَأُصَلِّبَنَّكُمْ فِى جُذُوعِ ٱلنَّخْلِ}[طه: ٧١]،

‹‹(ፈርዖንም) ለናንተ ሳልፈቅድላችሁ በፊት ለርሱ አመናችሁን? እርሱ በእርግጥ ያ ድግምትን ያስተማራችሁ ትልቃችሁ ነው፤እጆቻችሁንና እግሮቻችሁን በማናጋት (ግራና ቀኙን በማፈራረቅ) እቆርጣችኋለሁ፤በዘምባባም ግንዶች ላይ እሰቅላችኋለሁ፤››[ጣሃ:71]

የድግምተኞቹ ምላሽ ለፈርዖን ዱብ እዳ ከመሆኑም በላይ እምነት በምእመናን ላይ የሚያሳድረውን ከባድ ተጽእኖም የሚያብራራ ነበር::

{قَالُوا۟ لَا ضَيْرَ ۖ إِنَّآ إِلَىٰ رَبِّنَا مُنقَلِبُونَ ﴿٥٠﴾ إِنَّا نَطْمَعُ أَن يَغْفِرَ لَنَا رَبُّنَا خَطَٰيَٰنَآ أَن كُنَّآ أَوَّلَ ٱلْمُؤْمِنِينَ



https://www.path-2-happiness.com/am

﴿٥١﴾} [الشعراء: ٥٠- ٥١].

‹‹(እነርሱም) አሉ፦ ጉዳት የለብንም፤እኛ ወደ ጌታችን ተመላሾች ነን:: እኛ የምእመናን መጀመሪያ በመኾናችን፣ጌታችን ኀጢአቶቻችንን ለኛ ሊምር እንከጅላለን::››[አልሹዐራ:50-51]

ፈርዖን ምእመናኑን ማሰቃየት ሲቀጥል አላህ (ሱ.ወ.) እርሱንና ከርሱ ጋር ያሉትን ከሓዲዎች ቀጣቸው::

{وَلَقَدْ أَخَذْنَآ ءَالَ فِرْعَوْنَ بِٱلسِّنِينَ وَنَقْصٍ مِّنَ ٱلثَّمَرَٰتِ لَعَلَّهُمْ يَذَّكَّرُونَ ﴿١٣٠﴾ فَإِذَا جَآءَتْهُمُ ٱلْحَسَنَةُ قَالُوا۟ لَنَا هَٰذِهِۦ ۖ وَإِن تُصِبْهُمْ سَيِّئَةٌ يَطَّيَّرُوا۟ بِمُوسَىٰ وَمَن مَّعَهُۥٓ ۗ أَلَآ إِنَّمَا طَٰٓئِرُهُمْ عِندَ ٱللَّهِ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ﴿١٣١﴾} [الأعراف: ١٣٠- ١٣١]،

‹‹የፈርዖንንም ቤተሰቦች፣እንዲገሠጹ በድርቅ ዓመታትና ከፍሬዎችም በመቀነስ በእርግጥ ያዝናቸው:: ደጊቱም ነገር (ምቾት) በመጣችላቸው ጊዜ፣ይህች ለኛ (ተገቢ) ናት፣ይላሉ፤ክፉትም ብታገኛቸው በሙሳና አብረውት ባሉት ገደቢስነት ያመካኛሉ፤ንቁ! ገደቢስነታቸው አላህ ዘንድ ብቻ ነው፤ግን አብዛኞዎቻቸው አያውቁም::››[አል አዕራፍ:130-131]

አላመኑም፤ከክሕደታቸውም ተጸጽተው አልተመለሱም::

{وَقَالُوا۟ مَهْمَا تَأْتِنَا بِهِۦ مِنْ ءَايَةٍ لِّتَسْحَرَنَا بِهَا فَمَا نَحْنُ لَكَ بِمُؤْمِنِينَ ﴿١٣٢﴾ فَأَرْسَلْنَا عَلَيْهِمُ ٱلطُّوفَانَ وَٱلْجَرَادَ وَٱلْقُمَّلَ وَٱلضَّفَادِعَ وَٱلدَّمَ ءَايَٰتٍ مُّفَصَّلَٰتٍ فَٱسْتَكْبَرُوا۟ وَكَانُوا۟ قَوْمًا مُّجْرِمِينَ ﴿١٣٣﴾} [الأعراف: ١٣٢- ١٣٣]،

‹‹(ለሙሳም)፦ በማንኛይቱም ታምር በርሷ ልትደግምብን ብትመጣብን፣እኛ ለአንተ የምናምንልህ አይደለንም አሉ፤ወዲያውም የውሃን ማጥለቅለቅ፣አንበጣንም፣ነቀዝንም፣እንቁራሪቶችንም፣ደምንም፣የተለያዩ ታምራት ሲኾኑ፣በነሱ ላይ ላክን፤ኮሩም፤ተንኮለኞችም ሕዝቦች ነበሩ::››[አል አዕራፍ:132-133]

ቅጣቱ ሲጸናባቸው፦

{وَلَمَّا وَقَعَ عَلَيْهِمُ ٱلرِّجْزُ قَالُوا۟ يَٰمُوسَى ٱدْعُ لَنَا رَبَّكَ بِمَا عَهِدَ عِندَكَ ۖ لَئِن كَشَفْتَ عَنَّا ٱلرِّجْزَ لَنُؤْمِنَنَّ لَكَ وَلَنُرْسِلَنَّ مَعَكَ بَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ ﴿١٣٤﴾ فَلَمَّا كَشَفْنَا عَنْهُمُ ٱلرِّجْزَ إِلَىٰٓ أَجَلٍ هُم بَٰلِغُوهُ إِذَا هُمْ يَنكُثُونَ ﴿١٣٥﴾} [الأعراف: ١٣٤- ١٣٥]،

‹‹በነርሱም ላይ ቅጣቱ በወደቀባቸው ጊዜ፦ ሙሳ ሆይ! ጌታህን ላንተ ቃል ኪዳን በገባልህ ነገር ለኛ ለምንልን፤ከኛ ቅጣቱን ብታነሳልን ለአንተ በእርግጥ እናምንልሃለን፤የእስራኤልንም ልጆች ከአንተ ጋር በእርግጥ እንለቃለን፤አሉ:: እነርሱም ደራሾቹ እኾኑበት ጊዜ ድረስ ቅጣትን ከነሱ ላይ ባነሳን ጊዜ፣ወዲያውኑ እነርሱ ቃላቸውን ያፈርሳሉ::››[አል አዕራፍ:134-135]

የገቡትን ቃል ሲያፈርሱና ያሉትን ሳይፈጽሙ ሲቀሩም አላህ (ሱ.ወ.) ተበቀላቸው::

{فَٱنتَقَمْنَا مِنْهُمْ فَأَغْرَقْنَٰهُمْ فِى ٱلْيَمِّ بِأَنَّهُمْ كَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا وَكَانُوا۟ عَنْهَا غَٰفِلِينَ ﴿١٣٦﴾} [الأعراف: ١٣٦].

‹‹እነርሱ በታምራታችን ስለ አስተባበሉም፣ከርሷ ዘንጊዎች ስለኾኑም፤ከነሱ ተበቀልን፤በባሕርም ውስጥ አሰጠምናቸው::››[አል አዕራፍ:136]

የግብጽ ሰዎች ንጉሣቸውን ፈርዖንን በመከተልና የአላህን (ሱ.ወ.) ነቢይና መልክተኛውን ሙሳን ﷺ በመጻረር፣በክሕደታቸው በትዕቢታቸውና በእምቢታቸው በገፉ ጊዜ አላህ (ሱ.ወ.) የግብጽን ሕዝብ ኃያልና አስገዳጅ የሆኑ አስገራሚና አስደማሚ ታምራቶቹን አሳያቸው:: ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ሰዎቹ ከትዕቢታቸው የሚገቱና ከጥመታቸው የሚመለሱ አልሆኑም:: ከፈርዖን ሕዝብ በጣም ጥቂቶች ብቻ እንጅ አላመኑም:: ሁሉም ድግምተኞችና ሁሉም የእስራኤል ሕዝብ ያመኑ ሲሆን፣የፈርዖንን ግፍና ጭካኔ በመፍራት እምነታቸውን ይደብቁ ነበር:: አላህን እንዲገዙባቸውና በሚታዘዙ ጊዜ ለጉዞ ዝግጁ ሆነው አንዱ የሌላውን ቤት ለይቶ አውቀው ይጠብቁ ዘንድ፣የተከታዮቻቸው ቤቶች ከፈርዖን ተከታዮች ቤቶች የተለዩ እንዲሆኑ አላህ (ሱ.ወ.) ለሙሳና ለሃሩን [የአላህ ሰላም በሁለቱም ላይ ይሁን] አሳወቀ::

{وَأَوْحَيْنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰ وَأَخِيهِ أَن تَبَوَّءَا لِقَوْمِكُمَا بِمِصْرَ بُيُوتًا وَٱجْعَلُوا۟ بُيُوتَكُمْ قِبْلَةً وَأَقِيمُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ ۗ وَبَشِّرِ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿٨٧﴾} [يونس: ٨٧].

‹‹ወደ ሙሳና ወደ ወንድሙ፦ ለሕዝቦቻችሁ በምስር ቤቶችን ሥሩ፤ቤቶቻችሁንም መስገጃ አድርጉ፤ሶላትንም በደንቡ ስገዱ፤(ለሙሳ) ምእመናኖቹንም አብስር ስንል ላክን::››[ዩኑስ:87]

ከዚያም አላህ (ሱ.ወ.) ለባሪያው ለሙሳ ﷺ ወሕይ አስተላለፈ፦

{وَأَوْحَيْنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰٓ أَنْ أَسْرِ بِعِبَادِىٓ إِنَّكُم مُّتَّبَعُونَ ﴿٥٢﴾} [الشعراء: ٥٢]،

‹‹ወደ ሙሳም ፦ ባሮቼን ይዘህ ሌሊት ኺድ፣እናንተ የሚከተሏችሁ ናችሁና ስንል ላክን::››[አል ሹዐራ:52]

የፈርዖን መልስ ግን የሚከተለው ነበር፦

{فَأَرْسَلَ فِرْعَوْنُ فِى ٱلْمَدَآئِنِ حَٰشِرِينَ ﴿٥٣﴾ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ لَشِرْذِمَةٌ قَلِيلُونَ ﴿٥٤﴾ وَإِنَّهُمْ لَنَا لَغَآئِظُونَ ﴿٥٥﴾ وَإِنَّا لَجَمِيعٌ حَٰذِرُونَ ﴿٥٦﴾} [الشعراء: ٥٣- ٥٦]،

‹‹፦ ፈርዖንም በየከተሞቹ ሰብሳቢዎችን (እንዲህ ሲል) ላከ፤ ፦ እነዚህ ጥቂቶች ጭፍሮች ናቸው:: እነርሱም ለኛ አስቆጪዎች ናቸው:: እኛም ብዙዎች ጥንቁቆች ነን፤(አለ)::››[አል ሹዐራ:53-56]

የአላህ (ሱ.ወ.) ፈቃድ ግን ሌላ ሆነ፦

{فَأَخْرَجْنَٰهُم مِّن جَنَّٰتٍ وَعُيُونٍ ﴿٥٧﴾ وَكُنُوزٍ وَمَقَامٍ كَرِيمٍ ﴿٥٨﴾ كَذَٰلِكَ ۖ وَأَوْرَثْنَٰهَا بَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ ﴿٥٩﴾} [الشعراء: ٥٧- ٥٩]،

‹‹አወጣናቸውም፤ከአትክልቶችና ከምንጮች፤ከድልቦችም፣ከመልካም መቀመጫዎችም:: እንደዚሁ፣ለእስራኤል ልጆች አወረስናትም::››[አል ሹራ:51]

ፈርዖንና ሰራዊቱ የእስራኤል ልጆችን ይዘው ለመመለስ ተከተሏቸው::

{فَأَتْبَعُوهُم مُّشْرِقِينَ ﴿٦٠﴾} [الشعراء: ٦٠]،

‹‹ፀሐይዋ ስትወጣም፣ተከተሉዋቸው::››[አል ሹዐራ:60]

https://www.path-2-happiness.com/am

ሲደርሱባቸውም፦

{فَلَمَّا تَرَٰٓءَا ٱلۡجَمۡعَانِ قَالَ أَصۡحَٰبُ مُوسَىٰٓ إِنَّا لَمُدۡرَكُونَ ٦١}[الشعراء: ٦١]،

‹‹ሁለቱ ጭፍሮችም በተያዩ ጊዜ፣የሙሳ ጓዶች እኛ (የፈርዖን ሰዎች) የሚደርሱብን ነን፣አሉ፡፡››[አል ሹዐራ፡61]

የአላህ መልክተኛ የሙሳ عليه السلام ምላሽ ግን በአላህ ላይ ሙሉ በሙሉ በመተማመን፣እርሱን በማወቅና በርሱ ብቻ በመመካት የተሞላ ነበር፡፡

{قَالَ كَلَّآۖ إِنَّ مَعِيَ رَبِّي سَيَهۡدِينِ ٦٢}[الشعراء: ٦٢]،

‹‹(ሙሳ)፦ ተውዉ!ጌታዬ ከኔ ጋር ነው፤በእርግጥ ይመራኛል፣አለ፡፡››[አል ሹዐራ፡62]

የአላህ መመሪያና እዝነቱ ለሙሳና ለተከታዮቻቸው ከተፍ አለ፦

{فَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰٓ أَنِ ٱضۡرِب بِّعَصَاكَ ٱلۡبَحۡرَۖ فَٱنفَلَقَ فَكَانَ كُلُّ فِرۡقٖ كَٱلطَّوۡدِ ٱلۡعَظِيمِ ٦٣ وَأَزۡلَفۡنَا ثَمَّ ٱلۡأٓخَرِينَ ٦٤ وَأَنجَيۡنَا مُوسَىٰ وَمَن مَّعَهُۥٓ أَجۡمَعِينَ ٦٥ ثُمَّ أَغۡرَقۡنَا ٱلۡأٓخَرِينَ ٦٦ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗۖ وَمَا كَانَ أَكۡثَرُهُم مُّؤۡمِنِينَ ٦٧ وَإِنَّ رَبَّكَ لَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ٦٨}[الشعراء: ٦٣ـ ٦٨].

‹‹ወደ ሙሳም ባሕሩን በበትርህ ምታው ስንል ላክንበት፣(መታውና) ተከፈለም፤ክፍሉም ሁሉ እንደ ታላቅ ጋራ ኾነ፡፡ እዚያም ዘንድ ሌሎችን አቀረብን፡፡ ሙሳንና ከርሱ ጋር ያሉትንም ሰዎች፣ሁሉንም አዳን፡፡ ከዚያም ሌሎቹን አሰጠምን፡፡ በዚህ ውስጥ ታላቅ ታምር አለበት፤አብዛኞቻቸውም አማኞች አልነበሩም፡፡ ጌታህም፣እርሱ አሸናፊው፣አዛኙ ነው፡፡››[አል ሹዐራ፡63-68]

በዚህ አስፈሪ ወቅትም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ አለ፦





{وَجَٰوَزۡنَا بِبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ٱلۡبَحۡرَ فَأَتۡبَعَهُمۡ فِرۡعَوۡنُ وَجُنُودُهُۥ بَغۡيٗا وَعَدۡوًا}[يونس: ٩٠]،

‹‹የእስራኤልንም ልጆች፣ባሕሩን አሳለፍናቸው፤ፈርዖንና ሰራዊቱም ወሰን ለማለፍና ለመበደል ተከተሏቸው፤››[ዩኑስ፡90]

እዚህ ላይም ፈርዖን ሞትና መስጠም አይቀሬ መሆኑን አረጋገጠ፦

{حَتَّىٰٓ إِذَآ أَدۡرَكَهُ ٱلۡغَرَقُ قَالَ ءَامَنتُ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا ٱلَّذِيٓ ءَامَنَتۡ بِهِۦ بَنُوٓاْ إِسۡرَٰٓءِيلَ وَأَنَا۠ مِنَ ٱلۡمُسۡلِمِينَ ٩٠}[يونس: ٩٠]،

‹‹መስጠምም ባገኘው ጊዜ ፦ አመንኩ፤እነሆ ከዚያ የእስራኤል ልጆች በርሱ ከአመኑበት በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፣እኔም ከታዛዦቹ ነኝ አለ፡፡››[ዩኑስ፡90]

ፈርዖን መማጸን ቢጀምርም ሞት ተረጋግጦበታልና አሁን ጊዜው በጣም ዘግይቷል፦

{ءَآلۡـَٰٔنَ وَقَدۡ عَصَيۡتَ قَبۡلُ وَكُنتَ مِنَ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ٩١}[يونس: ٩١]،

‹‹፦ ከአሁን በፊት በእርግጥ ያመጥክ፣ከአጥፊዎችም የነበርክ ስትኾን፣አሁን?(ተባለ)፡፡››[ዩኑስ፡91]

ጠላታቸውን በማስጠም አላህ (ሱ.ወ.) በእስራኤል ልጆች ላይ ጸጋውን አሟላ፡፡ ባሕሩን አቋርጠው ከተሸገሩ በኋላ ግን፦

{وَجَٰوَزۡنَا بِبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ٱلۡبَحۡرَ فَأَتَوۡاْ عَلَىٰ قَوۡمٖ يَعۡكُفُونَ عَلَىٰٓ أَصۡنَامٖ لَّهُمۡۚ قَالُواْ يَٰمُوسَى ٱجۡعَل لَّنَآ إِلَٰهٗا كَمَا لَهُمۡ ءَالِهَةٞ}[الأعراف: ١٣٨]؛

‹‹የእስራኤልንም ልጆች ባሕሩን አሻገርናቸው፤ለነርሱ በኾኑ ጣዖታት (መግገዛት) ላይ በሚዘወትሩ ሕዝቦች ላይ አለፉም፤ሙሳ ሆይ! ለነርሱ (ለሰዎቹ) አማልክት እንዳሏቸው ሁሉ ለኛም አምላክን አድርግልን፣አሉት፤››[አል አዕራፍ፡ 138]

አላህ ከፈርዖንና ከሰራዊቱ ካዳናቸውና በተውሒድ ካከበራቸው በኋላ ግን የጅል ማይማዊ ጥያቄ አቀረቡ፦

{قَالَ إِنَّكُمۡ قَوۡمٞ تَجۡهَلُونَ ١٣٨ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ مُتَبَّرٞ مَّا هُمۡ فِيهِ وَبَٰطِلٞ مَّا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ١٣٩}[الأعراف: ١٣٨ـ ١٣٩]،

‹‹እናንተ የምትሳሳቱ ሕዝቦች ናችሁ፣አላቸው፡፡ እነዚህ፣እነርሱ በውስጡ ያሉበት ነገር ጠፊ ነው፣ይሠሩት የነበሩትም ብልሹ ነው (አላቸው)፡፡››[አል አዕራፍ፡139]

ከዚያም ሙሳ عليه السلام ለጌታቸው ቀጠሮ ሄዱ፡፡

{وَوَٰعَدۡنَا مُوسَىٰ ثَلَٰثِينَ لَيۡلَةٗ وَأَتۡمَمۡنَٰهَا بِعَشۡرٖ فَتَمَّ مِيقَٰتُ رَبِّهِۦٓ أَرۡبَعِينَ لَيۡلَةٗۚ وَقَالَ مُوسَىٰ لِأَخِيهِ هَٰرُونَ ٱخۡلُفۡنِي فِي قَوۡمِي وَأَصۡلِحۡ وَلَا تَتَّبِعۡ سَبِيلَ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ١٤٢}[الأعراف: ١٤٢]،





https://www.path-2-happiness.com/am



‹‹ሙሳንም ሠላሳ ሌሊት (ሊጾምና ልናነጋግረው) ቀጠርነው፤በዐሥርም (ሌሊት) ሞላናት፤የጌታውም ቀጠሮ አርባ ሌሊት ሲኾን ተፈጸመ፤ሙሳም ለወንድሙ ሃሩን፦ በሕዝቦቼ ላይ ተተካኝ፤አሳምርም፤የአጥፊዎችንም መንገድ አትከተል አለው።››[አል አዕራፍ፡142]

አላህ (ሱ.ወ.) ሙሳን عليه السلام አነጋገረ፤በንግግሩና በመልክቱም ልዩ አደረጋቸው።

{قَالَ يَٰمُوسَىٰٓ إِنِّي ٱصۡطَفَيۡتُكَ عَلَى ٱلنَّاسِ بِرِسَٰلَٰتِي وَبِكَلَٰمِي فَخُذۡ مَآ ءَاتَيۡتُكَ وَكُن مِّنَ ٱلشَّٰكِرِينَ ١٤٤}[الأعراف: ١٤٤]،

‹‹(አላህም) አለው፦ ሙሳ ሆይ! እኔ በመልክቶቼና በማናገሬ በሰዎች ላይ (በዘመንህ ካሉት) መረጥኩህ፤የሰጠሁህንም ያዝ፤ከአመስጋኞቹም ኹን።››[አል አዕራፍ፡144]

በግሣጼና ሕግጋቱን በያዘው ተውራትም አላህ (ሱ.ወ.) ጸጋውን ለነቢዩ ሙሳ عليه السلام ዘረጋ።

{وَكَتَبۡنَا لَهُۥ فِي ٱلۡأَلۡوَاحِ مِن كُلِّ شَيۡءٖ مَّوۡعِظَةٗ وَتَفۡصِيلٗا لِّكُلِّ شَيۡءٖ فَخُذۡهَا بِقُوَّةٖ وَأۡمُرۡ قَوۡمَكَ يَأۡخُذُواْ بِأَحۡسَنِهَاۚ سَأُوْرِيكُمۡ دَارَ ٱلۡفَٰسِقِينَ ١٤٥}[الأعراف: ١٤٥]،

‹‹ለርሱም በሰሌዳዎቹ ላይ ከነገሩ ሁሉ ግሣጼንና ለነገሩም ሁሉ መማብራራትን ጻፍንለት፤(አልንም)፦ በብርታትም ያዛት፤ሕዝቦችህንም በመልካሟ እንዲይዙ እዘዛቸው፤የአመጠኞቹን አገር በእርግጥ አሳያችኋለሁ።››[አል አዕራፍ፡145]

ሙሳ عليه السلام ቀጠሮውን ካጠናቀቁና ጌታቸው ተውራትን ሰጥቷቸው ወደ ሕዝባቸው ተመልሰው በመጡ ጊዜ፦

{وَٱتَّخَذَ قَوۡمُ مُوسَىٰ مِنۢ بَعۡدِهِۦ مِنۡ حُلِيِّهِمۡ عِجۡلٗا جَسَدٗا لَّهُۥ خُوَارٌۚ أَلَمۡ يَرَوۡاْ أَنَّهُۥ لَا يُكَلِّمُهُمۡ وَلَا يَهۡدِيهِمۡ سَبِيلًاۘ ٱتَّخَذُوهُ وَكَانُواْ ظَٰلِمِينَ ١٤٨ وَلَمَّا سُقِطَ فِيٓ أَيۡدِيهِمۡ وَرَأَوۡاْ أَنَّهُمۡ قَدۡ ضَلُّواْ قَالُواْ لَئِن لَّمۡ يَرۡحَمۡنَا رَبُّنَا وَيَغۡفِرۡ لَنَا لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ١٤٩}[الأعراف: 148ـ 149].

‹‹የሙሳም ሕዝቦች፤ከርሱ(መኼድ)በኋላ፤ከጌጣቻቸው ወይፈንን፤አካልን፤ለርሱ ማግሳት ያለውን፤(አምላክ አድርገው) ያዙ፤እርሱ የማያናግራቸው፤መንገድንም የማይመራቸው መኾኑን አይመለከቱምን? (አምላክ አድርገው) ያዙት፤በዳዮችም ኾኑ። በተጸጸቱና እነሱም በእርግጥ የተሳሳቱ መኾናቸውን ባዩ ጊዜ፦ ጌታችን ባያዝንልንና ባይምረን በእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንኾናለን አሉ።››[አል አዕራፍ፡148-149]



ክስተቱ ለሙሳ عليه السلام በጣም አስበርጋጊ ነበር።

{وَلَمَّا رَجَعَ مُوسَىٰٓ إِلَىٰ قَوۡمِهِۦ غَضۡبَٰنَ أَسِفٗا قَالَ بِئۡسَمَا خَلَفۡتُمُونِي مِنۢ بَعۡدِيٓۖ أَعَجِلۡتُمۡ أَمۡرَ رَبِّكُمۡۖ وَأَلۡقَى ٱلۡأَلۡوَاحَ وَأَخَذَ بِرَأۡسِ أَخِيهِ يَجُرُّهُۥٓ إِلَيۡهِۚ قَالَ ٱبۡنَ أُمَّ إِنَّ ٱلۡقَوۡمَ ٱسۡتَضۡعَفُونِي وَكَادُواْ يَقۡتُلُونَنِي فَلَا تُشۡمِتۡ بِيَ ٱلۡأَعۡدَآءَ وَلَا تَجۡعَلۡنِي مَعَ ٱلۡقَوۡمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ١٥٠ قَالَ رَبِّ ٱغۡفِرۡ لِي وَلِأَخِي وَأَدۡخِلۡنَا فِي رَحۡمَتِكَۖ وَأَنتَ أَرۡحَمُ ٱلرَّٰحِمِينَ ١٥١}[الأعراف: ١٥٠ـ ١٥١]،

‹‹ሙሳም እየተቆጣና እያዘነ ወደ ሕዝቦቹ በተመለሰ ጊዜ ፦ ከኔ በኋላ የተተካችሁኝ ነገር ከፋ! የጌታችሁን ትእዛዝ ተቻኮላችሁን? አላቸው፤ሰሌዳዎቹንም ጣላቸው፤የወንድሙንም ራስ (ጸጉር) ወደርሱ የሚጎትተው ሲኾን ያዘ፤(ወንድሙም)፦ የናቴ ልጅ ሆይ! ሕዝቦቹ ናቁኝ፤ሊገድሉኝም ተቃረቡ፤ስለዚህ በኔ ጠላቶችን አታስደስትብኝ፤ከአመጠኞች ሕዝቦችም ጋር አታድርገኝ አለው። (ሙሳም)፦ ጌታዬ ሆይ! ለእኔም ለወንድሜም ማር፤በእዝነትህም ውስጥ አግባን፤አንተም ከአዛኞች ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነህ፤አለ።››[አል አዕራፍ፡150-151]

በመቀጠልም ጥጃውን ቀርጾ የሠራውን ሳምራዊ ሙሳ ጠየቁት፦

{فَمَا خَطۡبُكَ يَٰسَٰمِرِيُّ ٩٥}[طه: ٩٥]؟

‹‹(ሙሳ)፦ ሳምራዊው ሆይ! ነገርህም ምንድነው? አለ።››[ጣሃ፡95]

ሳምራዊውም መለሰላቸው፦

{قَالَ بَصُرۡتُ بِمَا لَمۡ يَبۡصُرُواْ بِهِۦ فَقَبَضۡتُ قَبۡضَةٗ مِّنۡ أَثَرِ ٱلرَّسُولِ فَنَبَذۡتُهَا وَكَذَٰلِكَ سَوَّلَتۡ لِي نَفۡسِي ٩٦}[طه: ٩٦]؛

‹‹ያላዩትን ነገር (የጂብሪል ባዝራ ፈረስ የረገጠችው መለምለሙን) አየሁ፤ከመልክተኛው (ከፈረሱ ኮቴ) ዱካም ጭብጥ ዐፈርን ዘገንኩ፤(በቅርጹ ላይ) ጣልኳትም፤እንደዚሁም ነፍሴ ሸለመችልኝ፤አለ።››[ጣሃ፡96]

የሙሳ عليه السلام ምላሽ ግን በማጋራትና በጣዖት አምልኮ ላይ ቁርጥ ያለ ብርቱ ምላሽ ነበር፦





https://www.path-2-happiness.com

https://www.path-2-happiness.com/am



{قَالَ فَٱذۡهَبۡ فَإِنَّ لَكَ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ أَن تَقُولَ لَا مِسَاسَۖ وَإِنَّ لَكَ مَوۡعِدٗا لَّن تُخۡلَفَهُۥۖ وَٱنظُرۡ إِلَىٰٓ إِلَٰهِكَ ٱلَّذِي ظَلۡتَ عَلَيۡهِ عَاكِفٗاۖ لَّنُحَرِّقَنَّهُۥ ثُمَّ لَنَنسِفَنَّهُۥ فِي ٱلۡيَمِّ نَسۡفًا ﴿٩٧﴾ إِنَّمَآ إِلَٰهُكُمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِي لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۚ وَسِعَ كُلَّ شَيۡءٍ عِلۡمٗا ﴿٩٨﴾}[طه: ٩٧-٩٨]،

‹‹አለው፦ኺድ ላንተም በሕይወትህ (ለአየኸው ሰው ሁሉ) መነካካት የለም ማለት አለህ፤ለአንተም ፈጽሞ የማትጥሰው (አላህ የማይጥሰው የማይቀር) ቀጠሮ አለህ፤ወደዚያም በርሱ ላይ ተገዢው ኾነህ ወደ ቆየህበት አምላክህ ተመልከት፤በእርግጥ እናቃጥለዋለን፤ከዚያም በባሕሩ ውስጥ መበተንን እንበትነዋለን። ጌታችሁ ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ የኾነው አላህ ብቻ ነው፤ዕውቀቱ ነገርን ሁሉ አዳረሰ።››[ጣሃ:97-98]

ከዚያም ሰሌዳዎቹን ከተቀበሉ በኋላ ሙሳ عليه السلام ወደ ቅድስት አገር አቀኑ።

{وَلَمَّا سَكَتَ عَن مُّوسَى ٱلۡغَضَبُ أَخَذَ ٱلۡأَلۡوَاحَۖ وَفِي نُسۡخَتِهَا هُدٗى وَرَحۡمَةٞ لِّلَّذِينَ هُمۡ لِرَبِّهِمۡ يَرۡهَبُونَ ﴿١٥٤﴾}[الأعراف: ١٥٤]،

‹‹ከሙሳም፣ቁጣው በበረደ ጊዜ፣ሰሌዳዎቹን፣በግልባጫቸው ውስጥ ለነዚያ እነርሱ ጌታቸውን የሚፈሩ ለኾኑት መምሪያና እዝነት ያለባቸው ሲኾኑ ያዘ።››[አል አዕራፍ:154]

ከእስራኤል ልጆች መካከል ከፊሉ በተውራት ውስጥ የተካተቱትን ሕግጋት ለመቀበል ፍላጎት ስላልነበራቸው፣አላህ (ሱ.ወ.) ላይ ተራራ ነቅሎ በላያቸው ላይ እንደ ጥላ አንዣበበባቸው።

{وَإِذۡ نَتَقۡنَا ٱلۡجَبَلَ فَوۡقَهُمۡ كَأَنَّهُۥ ظُلَّةٞ وَظَنُّوٓاْ أَنَّهُۥ وَاقِعُۢ بِهِمۡ خُذُواْ مَآ ءَاتَيۡنَٰكُم بِقُوَّةٖ وَٱذۡكُرُواْ مَا فِيهِ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ﴿١٧١﴾}[الأعراف: ١٧١]،

‹‹የጡርን ተራራ ነቅለን ከበላያቸው እንደ ጥላ ኾኖ በአነሳነውና እርሱም በነሱ ላይ ወዳቂ መኾኑን ባረጋገጡ ጊዜ (አስታውስ)፤የሰጠናችሁን በብርታት ያዙ፤ትጠነቀቁም ዘንድ በውስጡ ያለውን ተገንዘቡ (አልን)።››[አል አዕራፍ:171]

መጽሐፉ በመመሪያና በእዝነት የተሞላ ቢሆንም ተራራው እንዳይወድቅባቸው በመፍራት ብቻ ተቀበሉት። የእስራኤል ልጆች ጥመትና ዝንፈት ለነቢዩ ሙሳ عليه السلام አስቸጋሪ እንደሆነ ቀጠለ። አንዴ ነፍስ ገደሉ። ሚቹ ሀብታም የሆነ እስራኤላዊ ሰው ሲሆን የወንድሙ ልጅ ነበር ማታ አርዶ የገደለው! ገዳዩ ባለመታወቁ ሁሉም እርስ በርስ መወነጃጀል ያዙ። ጉዳዩን ለነቢዩ ሙሳ አቀረቡና ‹‹እውነት የአላህ ነቢይ ከሆንክ ገዳዩ ማን እንደሆነ ጌታህን ጠይቀህ ንገረን!›› በማለት ስነምግባር በጎደለው ሁኔታ የትእቢት ጥያቄ አቀረቡ። አላህ (ሱ.ወ.) የእስራኤል ልጆችን አንድ ላም አርደው አንዱን ብልት በመውሰድ የሟቹን በድን እንዲመቱ ነገራቸው፣እኔ በፈቃዴ ሕያው አደርገውና ማን እንደ ገደለው ይናገራል፣ሲል ሙሳን አዘዛቸው። ይህን በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذۡ قَتَلۡتُمۡ نَفۡسٗا فَٱدَّٰرَٰٔتُمۡ فِيهَاۖ وَٱللَّهُ مُخۡرِجٞ مَّا كُنتُمۡ تَكۡتُمُونَ ﴿٧٢﴾ فَقُلۡنَا ٱضۡرِبُوهُ بِبَعۡضِهَاۚ كَذَٰلِكَ يُحۡيِ ٱللَّهُ ٱلۡمَوۡتَىٰ وَيُرِيكُمۡ ءَايَٰتِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ ﴿٧٣﴾}[البقرة: ٧٢-٧٣]؛

‹‹ነፍስንም በገደላችሁና በርሷም (ገዳይ) በተከራከራችሁ ጊዜ (አስታውስ)፤አላህም ትደብቁት የነበራችሁትን ሁሉ ገላጭ ነው። (በድኑን) በከፊሏም ምቱት አልን (መቱትምና ተነሳ፤ገዳዩንም ተናገረና ሞተ)፤እንደዚሁ አላህ ሙታንን ያስነሳል፤ታውቁም ዘንድ ታምራቶችን ያሳያችኋል።››[አል በቀራህ: 72-73]

ሙሳም ላም እረዱ አሏቸው። ማንኛይቱንም ላም አምጥተው ማረድ በቂያቸው ነበር። በትእቢታቸው ምክንያት ነገሩን አወሳሰቡ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱللَّهَ يَأۡمُرُكُمۡ أَن تَذۡبَحُواْ بَقَرَةٗۖ قَالُوٓاْ أَتَتَّخِذُنَا هُزُوٗاۖ قَالَ أَعُوذُ بِٱللَّهِ أَنۡ أَكُونَ مِنَ ٱلۡجَٰهِلِينَ ﴿٦٧﴾}[البقرة: ٦٧]،

‹‹፦ አላህ ላምን እንድታርዱ ያዛችኋል ባለ ጊዜ (አስታውሱ)፤መሳለቂያ አድርገህ ትይዘናለህን? አሉት፤- ከተሳላቂዎች ከመኾን በአላህ እጠበቃለሁ፣ አላቸው።››[አል በቀራህ:67]

ሰዎቹም እንዲህ ሲሉ መለሱ፦

{قَالُواْ ٱدۡعُ لَنَا رَبَّكَ يُبَيِّن لَّنَا مَا هِيَ}[البقرة: ٦٨]،

‹‹ለኛ ጌታህን ጠይቅልን፤እርሷ ምን እንደ ኾነች (ዕድሜዋን) ያብራራልን አሉ፤››[አል በቀራህ:68]

በራሳቸው ላይ አጠበቁና አላህም (ሱ.ወ.) አጠበቀባቸው፦

{قَالَ إِنَّهُۥ يَقُولُ إِنَّهَا بَقَرَةٞ لَّا فَارِضٞ وَلَا بِكۡرٌ}[البقرة: ٦٨]؛

‹‹እርሱ እርሷ ያላረጀች፣ጥጃም ያልኾነች . . ናት ይላችኋል . . አላቸው።››[አል በቀራህ:68]

ያላረጀችና ትንሽ ጥጃም ያልሆነች መሆኗ ተነገራቸው።

{قَالَ إِنَّهُۥ يَقُولُ إِنَّهَا بَقَرَةٞ لَّا فَارِضٞ وَلَا بِكۡرٌ عَوَانُۢ بَيۡنَ ذَٰلِكَۖ فَٱفۡعَلُواْ مَا تُؤۡمَرُونَ ﴿٦٨﴾}[البقرة: ٦٨]،

‹‹እርሱ እርሷ ያላረጀች፣ጥጃም ያልኾነች፣በዚህ መካከል ልከኛ የኾነች ጊደር

https://www.path-2-happiness.com/am



ናት ይላችኋል፤የታዘዛችሁትንም ሥሩ፤አላቸው::››[አል በቀራህ:68]

በራሳቸው ላይ በማጥበቅ ነገሩን አወሳሰቡት፦

{قَالُوا ادْعُ لَنَا رَبَّكَ يُبَيِّن لَّنَا مَا لَوْنُهَا} [البقرة: ٦٩]،

‹‹ለኛ ጌታህን ጠይቅልን፤መልኳ ምን እንደ ኾነ ለኛ ይግለጽልን አሉ፤››[አል በቀራህ:69]

አላህ (ሱ.ወ.) ግን የቆዳ ቀለም አልጠየቃቸውም፤የተለየ የላም መለያም መስፈርት አላደረገባቸውም ነበር፦

{قَالَ إِنَّهُ يَقُولُ إِنَّهَا بَقَرَةٌ صَفْرَاءُ فَاقِعٌ لَّوْنُهَا تَسُرُّ النَّاظِرِينَ ﴿٦٩﴾} [البقرة: ٦٩]،

‹‹እርሱ እርሷ መልኳ ደማቅ ተመልካቾችን የምታስደስት ዳለቻ ላም ናት፤ይላችኋል አላቸው::››[አል በቀራህ:69]

ዝግ ስብሰባ ካደረጉ በኋላ ተመልሰው ወደ ሙሳ عليه السلام መጡ፦

{قَالُوا ادْعُ لَنَا رَبَّكَ يُبَيِّن لَّنَا مَا هِيَ إِنَّ الْبَقَرَ تَشَابَهَ عَلَيْنَا وَإِنَّا إِن شَاءَ اللَّهُ لَمُهْتَدُونَ ﴿٧٠﴾} [البقرة: ٧٠]،

‹‹ለኛ ጌታህን ጠይቅልን፤እርሷ ምን እንደ ኾነች ግለጽልን፤ከብቶች በኛ ላይ ተመሳሰሉብን፤እኛም አላህ የሻ እንደ ኾነ በእርግጥ ተመሪዎች ነን አሉ::››[አል በቀራህ:70]

ሙሳም መልስ ሰጣቸው፦

{قَالَ إِنَّهُ يَقُولُ إِنَّهَا بَقَرَةٌ لَّا ذَلُولٌ تُثِيرُ الْأَرْضَ وَلَا تَسْقِي الْحَرْثَ مُسَلَّمَةٌ لَّا شِيَةَ فِيهَا قَالُوا الْآنَ جِئْتَ بِالْحَقِّ فَذَبَحُوهَا وَمَا كَادُوا يَفْعَلُونَ ﴿٧١﴾} [البقرة: ٧١]،



## የጥጃው ቀራጺ ሳምራዊው ነው

‹‹የአላህ ነቢይ ሃሩን የጥጃው ቀራጺና የጣዖት አምልኮ አስተማሪ ፈጽሞ ሊሆኑ አይችሉም፤ሁሉም ነቢያት ለአላህ (ሱ.ወ.) አንድነት ለተውሒድ ጥሪ የሚያደርጉ ናቸውና:: ከዚህ ውጭ ያለው ዘገባ የተዛነፈና የተበረዘ ነው:: ከመሰል የተዛነፉ ዘገባዎች መካከል የሚከተለውን እናገኛለን፦ ‹‹አሮንም፦ በሚስቶቻችሁ በወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ጆሮ ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች ሰብራችሁ አምጡልኝ አላቸው:: ሕዝቡም ሁሉ በጆሮቻቸው ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች ሰብረው ወደ አሮን አመጡለት:: ከእጃቸውም ተቀብሎ በመቅጫ ቀረጸው፤ቀልጦ የተሠራ ጥጃም አደረገው፤እርሱም፦ እስራኤል ሆይ፤እነዚህ ከግብጽ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው አላቸው::›› ዘጸአት 32፣2-4

‹‹እርሱ እርሷ ያልተገራች፤ምድርን (በማረስ) የማታስነሳ፤እርሻንም የማታጠጣ፤(ከነውር) የተጠበቀች፤ልዩ ምልክት የሌለባት ናት፤ይላችኋል፤አላቸው፤አሁን በትክክል መጣህ አሉ፤ሲሠሩ ያልተቃረቡም ሲኾኑ አረዱዋት (የጠናቸው ኾነው እየከበዳቸው አረዷት)::››[አል በቀራህ:71]

የእስራኤልን ከተሞችና መንደሮች አንድ በአንድ ካዳረሱ በኋላ በብዙ ችግርና ስቃይ የተባለችውን ላም አግኝተው ማድረጉ እየከበዳቸው አረዷት:: በገዳዩ ማንነት ላይ የተወዛገቡበትን ሟች ሬሳ በታረደችው ላም አንዱ ብልት ሲመቱም በአላህ ፈቃድ ሕያው ሆኖ ተነሳ:: ሙሳ عليه السلام ማን ገደለህ? ብለው ሲጠይቁትም ይህኛው ነው ብሎ አሳያቸው::

{فَقُلْنَا اضْرِبُوهُ بِبَعْضِهَا كَذَٰلِكَ يُحْيِي اللَّهُ الْمَوْتَىٰ وَيُرِيكُمْ آيَاتِهِ لَعَلَّكُمْ تَعْقِلُونَ ﴿٧٣﴾} [البقرة: ٧٣]،

‹‹(በድኑን) በከፊሏም ምቱት አልን (መቱትምና ተነሳ፤ገዳዩንም ተናገረና ሞተ)፤እንደዚሁ አላህ ሙታንን ያስነሳል፤ታውቁም ዘንድ ታምራቶችን ያሳያችኋል::››[አል በቀራህ:73]

ወደ ቅድስት አገር በሚደርሱበት ጊዜም ኃያላን የሆኑ ሕዝቦች አጋጠሟቸው፦

{وَإِذْ قَالَ مُوسَىٰ لِقَوْمِهِ يَا قَوْمِ اذْكُرُوا نِعْمَةَ اللَّهِ عَلَيْكُمْ إِذْ جَعَلَ فِيكُمْ أَنبِيَاءَ وَجَعَلَكُم مُّلُوكًا وَآتَاكُم مَّا لَمْ يُؤْتِ أَحَدًا مِّنَ الْعَالَمِينَ ﴿٢٠﴾ يَا قَوْمِ ادْخُلُوا الْأَرْضَ الْمُقَدَّسَةَ الَّتِي كَتَبَ اللَّهُ لَكُمْ وَلَا تَرْتَدُّوا عَلَىٰ أَدْبَارِكُمْ فَتَنقَلِبُوا خَاسِرِينَ ﴿٢١﴾ قَالُوا يَا مُوسَىٰ إِنَّ فِيهَا قَوْمًا جَبَّارِينَ وَإِنَّا لَن نَّدْخُلَهَا حَتَّىٰ يَخْرُجُوا مِنْهَا فَإِن يَخْرُجُوا مِنْهَا فَإِنَّا دَاخِلُونَ ﴿٢٢﴾} [المائدة: ٢٠-٢٢]، {قَالُوا يَا مُوسَىٰ إِنَّا لَن نَّدْخُلَهَا أَبَدًا مَّا دَامُوا فِيهَا فَاذْهَبْ أَنتَ وَرَبُّكَ فَقَاتِلَا إِنَّا هَاهُنَا قَاعِدُونَ ﴿٢٤﴾} [المائدة: ٢٤]؛

https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹ሙሳም ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፣፦ ሕዝቦቼ ሆይ! የአላህን ጸጋ በውስጣችሁ ነቢያትን ባደረገና ነገሥታትን ባደረጋችሁ፣ከዓለማትም ለአንድም ያልሰጠውን ችሮታ በሰጣችሁ ጊዜ (በናንተ ላይ ያደረገውን ጸጋ) ፦ ሕዝቦቼ ሆይ! ያችን አላህ ለእናንተ ያደረጋትን የተቀደሰችውን መሬት ግቡ፤ወደ ኋላችሁም አትመለሱ፤ከሳሪዎች ኾናችሁ ትመለሳላችሁና። ሙሳ ሆይ! በርሷ ውስጥ ኀያላን ሕዝቦች አልሉ፤ከርስዋም እስከሚወጡ ድረስ፣እኛ ፈጽሞ አንገባትም፣ከርስዋም ቢወጡ እኛ ገቢዎች ነን አሉ። ›[አል ማእዳህ:20-22] ‹‹ሙሳ ሆይ! በውስጧ እስካሉ ድረስ እኛ ፈጽሞ ምንጊዜም አንገባትም፤ስለዚህ ኺድ፤አንተና ጌታህ ተጋደሉም፤እኛ እዚህ ተቀማጮች ነን አሉ።››[አል ማእዳህ:24]

አላህም በስንፍናቸውና በድክመታቸው ወቅሷቸው፣ ጅሃድን በመተዋቸውና ነብያቸውን በመጻረራቸው ምክንያት ለረዥም ዘመን በምድረበዳ ባዝነው እንዲቀሩ በማድረግ ቀጣቸው። ሙሳም እንዲህ አሉ፦

{قَالَ رَبِّ إِنِّي لَآ أَمۡلِكُ إِلَّا نَفۡسِي وَأَخِيۖ فَٱفۡرُقۡ بَيۡنَنَا وَبَيۡنَ ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡفَٰسِقِينَ ﴿٢٥﴾}[المائدة: ٢٥]،

‹‹፦ ጌታየ ሆይ! እኔ ራሴንና ወንድሜን በቀር (ላስገድድ) አልችልም፣በእናና በአመጠኞቹም ሕዝቦች መካከል ለይ፣ አለ።››[አል ማእዳህ:25]

አላህም (ሱ.ወ.) ጸሎታቸውን ተቀበለ፦

{قَالَ فَإِنَّهَا مُحَرَّمَةٌ عَلَيۡهِمۡۛ أَرۡبَعِينَ سَنَةٗۛ يَتِيهُونَ فِي ٱلۡأَرۡضِۚ فَلَا تَأۡسَ عَلَى ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡفَٰسِقِينَ ﴿٢٦﴾}[المائدة: ٢٦]،

‹‹፦ እርሷም (የተቀደሰችው መሬት) በእነሱ ላይ አርባ ዓመት እርም ናት፤በምድረበዳ ይንከራተታሉ። በአመጠኞችም ሕዝቦች ላይ አትዘን፣አለው።››[አል ማእዳህ:26]

መድረሻቸው የት እንደሆነ ሳያውቁ ያለ ምንም ዓላማና ግብ ቀን ከሌሊት፣ጧትና ማታም ዝም ብለው ይጓዙም ነበር።







## 4- ነቢዩ ዒሳ ﷺ፦

የመርየም [የአላህ ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን] አባት ዒምራን ከእስራኤላውያን መካከል አላህን (ሱ.ወ.) አብዝተው በመግገዛት የሚታወቅ ጻድቅ ሰው ነበር። የዘር ሐረጉ ከተከበረ ነቢያዊ ቤተሰብ ከዳዉድ ቤት የሚመዘዝ ሲሆን፣ባለቤቱ የመርየም እናት ልጅ ለመውለድ ያልታደለች ነበረች። ልጅ የመውለድ ፍላጎቷን ያሳካላት ዘንድም ልጅ ከወለደች ለቤተመቅደስ አገልግሎት ብቻ የተሰጠ እንዲሆን ለማድረግ ለአላህ ተሳለች።

{إِذۡ قَالَتِ ٱمۡرَأَتُ عِمۡرَٰنَ رَبِّ إِنِّي نَذَرۡتُ لَكَ مَا فِي بَطۡنِي مُحَرَّرٗا فَتَقَبَّلۡ مِنِّيٓۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ﴿٣٥﴾ فَلَمَّا وَضَعَتۡهَا قَالَتۡ رَبِّ إِنِّي وَضَعۡتُهَآ أُنثَىٰ وَٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِمَا وَضَعَتۡ وَلَيۡسَ ٱلذَّكَرُ كَٱلۡأُنثَىٰۖ وَإِنِّي سَمَّيۡتُهَا مَرۡيَمَ وَإِنِّيٓ أُعِيذُهَا بِكَ وَذُرِّيَّتَهَا مِنَ ٱلشَّيۡطَٰنِ ٱلرَّجِيمِ ﴿٣٦﴾}[آل عمران: ٣٥- ٣٦]؛

‹‹የዒምራን ባለቤት (ሐና)፦ ጌታ ሆይ! እኔ በሆዴ ውስጥ ያለውን (ጽንስ፣ከሥራ) ነጻ የተደረገ ሲኾን ለአንተ ተሳልኩ፤ከኔም ተቀበል፤አንተ ሰሚው፣ዐዋቂው ነህና ባለች ጊዜ (አስታውስ)። በወለደቻትም ጊዜ፦ ጌታዬ ሆይ! እኔ ሴት ኾና ወለድኳት፤አላህም የወለደችውን ዐዋቂ ነው፤ወንድም እንደ ሴት አይደለም፤እኔም መርየም ብዬ ስም አወጣሁላት፣እኔም እስዋንም ዘርያዋንም ከተረገመው ሰይጣን በአንተ እጠብቃቸዋለሁ፣አለች።››[አሊ ዒምራን:35-36]

አላህም (ሱ.ወ.) የእናቷን ስለት ሞላላት፦

{فَتَقَبَّلَهَا رَبُّهَا بِقَبُولٍ حَسَنٖ وَأَنۢبَتَهَا نَبَاتًا حَسَنٗا}[آل عمران: ٣٧]؛

‹‹ጌታዋም በደህና አቀባበል ተቀበላት፤በመልካም አስተዳደግም አፋፋት፤››[አሊ ዒምራን:37]

አስተዳደጓም ውብና መልካም በሆነ የደጋግ የአላህ አገልጋዮች የመታደል መንገድ ላይ የታነጸ ነበር። ለዚህም ነው አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ያለው፦

{وَكَفَّلَهَا زَكَرِيَّا}[آل عمران: ٣٧]؛



https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹ዘከሪያም አሳደጋት፤››[ኣሊ. ዒምራን:37]

የአክስቷ ወይም የእህቷ ባል የሆነው አሳዳጊዋ የአላህ (ሱ.ወ.) ነቢይ መሆኑ የተቸረችው የአላህ (ሱ.ወ.) ታላቅ ጸጋ ነበር::

{كُلَّمَا دَخَلَ عَلَيۡهَا زَكَرِيَّا ٱلۡمِحۡرَابَ وَجَدَ عِندَهَا رِزۡقٗاۖ قَالَ يَٰمَرۡيَمُ أَنَّىٰ لَكِ هَٰذَاۖ قَالَتۡ هُوَ مِنۡ عِندِ ٱللَّهِۖ إِنَّ ٱللَّهَ يَرۡزُقُ مَن يَشَآءُ بِغَيۡرِ حِسَابٍ ٣٧}[آل عمران: ٣٧]؛

‹‹ዘከሪያ በርሷ ላይ በምኩራቧ (በመጸለያ ስፍራዋ) በገባ ቁጥር፣እርሷ ዘንድ ሲሳይን አገኘ፤፦ መርየም ሆይ! ይህ ለአንቺ ከየት ነው? አላት፤- እርሱ ከአላህ ዘንድ ነው፤አላህ ለሚሻው ሰወ ሲሳዩን ያለ ድካም ይሰጣል አለችው::››[ኣሊ.ዒምራን:37]

ይህም ከአላህ (ሱ.ወ.) የተሰጣት የመከበሪያና የባለሟልነት ደረጃ ነበር:: አላህም (ሱ.ወ.) ምርጥና የተከበረች አድርጓት በአምልኮው አዟታል፦

{وَإِذۡ قَالَتِ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ يَٰمَرۡيَمُ إِنَّ ٱللَّهَ ٱصۡطَفَىٰكِ وَطَهَّرَكِ وَٱصۡطَفَىٰكِ عَلَىٰ نِسَآءِ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٤٢ يَٰمَرۡيَمُ ٱقۡنُتِي لِرَبِّكِ وَٱسۡجُدِي وَٱرۡكَعِي مَعَ ٱلرَّٰكِعِينَ ٤٣}[آل عمران: ٤٢- ٤٣]،

‹‹መላእክትም ያሉትን (አስታውስ)፦ መርየም ሆይ! አላህ በእርግጥ መረጠሽ፣አነጻሽም፣በዓለማት ሴቶችም ላይ መረጠሽ:: መርየም ሆይ! ለጌታሽ ታዘዢ፤ስገጂም፤ከአጎንባሾቹም ጋር አጎንብሺ::››[ኣሊ. ዒምራን:42-43]

ከዚያም ዒሳ عليه السلام እንዲወለዱ የአላህ (ሱ.ወ.) ፈቃድ ሲሆንም መርየም عليها السلام ከቤተሰቦቿ ገለል ብላ ሄደች፦

{وَٱذۡكُرۡ فِي ٱلۡكِتَٰبِ مَرۡيَمَ إِذِ ٱنتَبَذَتۡ مِنۡ أَهۡلِهَا مَكَانٗا شَرۡقِيّٗا ١٦ فَٱتَّخَذَتۡ مِن دُونِهِمۡ حِجَابٗا فَأَرۡسَلۡنَآ إِلَيۡهَا رُوحَنَا فَتَمَثَّلَ لَهَا بَشَرٗا سَوِيّٗا ١٧}[مريم: ١٦- ١٧]،

‹‹በመጽሐፉ ውስጥ መርየምንም ከቤተሰቧ ወደ ምሥራቃዊ ስፍራ በተለየች ጊዜ (የኾነውን ታሪኳን) አውሳ:: ከነሱም መጋረጃን አደረገች፣መንፈሳችንንም (ጂብሪልን) ወደርሷ ላክን፤ለርሷም ትክክለኛ ሰው ኾኖ ተመሰለላት::››[መርየም: 16-17]

ክፉ የሚሠራባት አድርጋ ስለጠረጠረችው መርየም መልአኩን ፈራች፦

{قَالَتۡ إِنِّيٓ أَعُوذُ بِٱلرَّحۡمَٰنِ مِنكَ إِن كُنتَ تَقِيّٗا ١٨ قَالَ إِنَّمَآ أَنَا۠ رَسُولُ رَبِّكِ لِأَهَبَ لَكِ غُلَٰمٗا زَكِيّٗا ١٩}[مريم: ١٨- ١٩]،

‹‹፦ እኔ ከአንተ በአልረሕማን እጠበቃለሁ፤ጌታህን ፈሪ እንደ ኾንክ፣(አትቅረበኝ) አለች:: ፦ እኔ ንጹሕን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ፣የጌታሽ መልክተኛ ነኝ አላት:: ››[መርየም:18-19]

ድንግሏ መርየም በነገሩ እጅግ ተገረመች፦



{قَالَتۡ أَنَّىٰ يَكُونُ لِي غُلَٰمٞ وَلَمۡ يَمۡسَسۡنِي بَشَرٞ وَلَمۡ أَكُ بَغِيّٗا ٢٠}[مريم: ٢٠]،

‹‹(በጋብቻ) ሰው ያልነካኝ ኾኜ፣አመንዝራም ሳልኾን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል! አለች::››[መርየም:20]

መልአኩም ይህ የአላህ (ሱ.ወ.) ፍርድና የርሱ ውሳኔ መሆኑን፣የሚወለደው ልጅም የርሱ ታምር መሆኑንና ይህን ማድረግም ለአላህ (ሱ.ወ.) በጣም ቀላል መሆኑን ነገራት::

{قَالَ كَذَٰلِكِ قَالَ رَبُّكِ هُوَ عَلَيَّ هَيِّنٞۖ وَلِنَجۡعَلَهُۥٓ ءَايَةٗ لِّلنَّاسِ وَرَحۡمَةٗ مِّنَّاۚ وَكَانَ أَمۡرٗا مَّقۡضِيّٗا ٢١}[مريم: ٢١]،

‹‹አላት፦ (ነገሩ) እንደዚህሽ ነው፤ጌታሽ ፦ እርሱ በእኔ ላይ ገር ነው፤ለሰዎችም ታምር፣ከኛም ችሮታ ልናደርገው (ይህንን ሠራን) የተፈረደም ነገር ነው፣አለ፤(ነፋባትም)::››[መርየም:21]

ንጹሕና የጠራች፣ከዝሙትም ሆነ ከማንኛውም ዝንፈት የጸዳች ከሆነች ድንግል እናት ዒሳ عليه السلام ያለ አባት እንዲወለድ የአላህ (ሱ.ወ.) ፈቃድ ነበር:: ይህም በችሮታውና ቃሉን ለመፈጸም ሲሆን የነቢዩ ዒሳ عليه السلام በዚህ ሁኔታ መወለድም ከአላህ (ሱ.ወ.) ተአምራት አንዱ ተአምር ነው:: ምሳሌውም ያለ አባትና ያለ እናት ከዐፈር እንደ ተፈጠረው አዳም ምሳሌ ነው:: ህን በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ مَثَلَ عِيسَىٰ عِندَ ٱللَّهِ كَمَثَلِ ءَادَمَۖ خَلَقَهُۥ مِن تُرَابٖ ثُمَّ قَالَ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ٥٩ ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّكَ فَلَا تَكُن مِّنَ ٱلۡمُمۡتَرِينَ ٦٠}[آل عمران: ٥٩- ٦٠].

‹‹አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ፣እንደ አዳም ብጤ ነው፤ከዐፈር ፈጠረው፤ከዚያም ለርሱ (ሰው) ኹን አለው፣ኾነም:: ይህ ከጌታህ ዘንድ የኾነ እውነት ነው፤ከተጠራጣሪዎቹም አትኹን::››[ኣሊ.

## ነቢዮች ከሰው ልጆች ምርጦችና ፈርጦች ናቸው

‹‹የአላህን ነቢያትና መልክተኞቹን በተመለከተ ከተላለፉት የተዛቡና ተአማኒነት ከጎደላቸው ዘገባዎች መካከል መስከራቸውን፣ወይም ዝሙት ላይ መውደቃቸውን፣ወይም ሰዎች እንዲገደሉ ትእዛዝ መስጠታቸውን . . የሚያወሩ ይገኛሉ:: ይህ ሁሉ በአላህ ለተመረጡ ምርጦችና የሰው ልጆች ፈርጦች ከሆኑ የአላህ ነቢያት ቀርቶ በመልካም ስነምግባር ለታነጸ ተራ ሰው እንኳ የማይገባ መሰረት የለሽ ተረት ነው:: ከመሰል ተረቶች መካከል ነቢዩ ዳውድን عليه السلام አስመልክቶ (ሳሙኤል ካልዕ 11፣2-26)፤ስለ ኢያሱ ወልደ ነወዌ عليه السلام የቀረበው (ኢያሱ 6፣24)፤ነቢዩ ሙሳን عليه السلام አስመልክቶ የሰፈረው (ዘኁልቁ 31፣14-18) እና ሌሎቹም መሰል ጥቅሶች ለአላህ ክቡራን ነቢያት ፈጽሞ የማይገቡ ናቸው::››

https://www.path-2-happiness.com/am

ዒምራን:59-60]

በጸነሰች ጊዜም ከማሕበረሰቡ ገለል አለች፦

{فَحَمَلَتۡهُ فَٱنتَبَذَتۡ بِهِۦ مَكَانٗا قَصِيّٗا ۝٢٢}[مريم: ٢٢]،

‹‹ወዲያውኑም አረገዘችው፤በርሱም (በሆድዋ ይዛው) ወደ ሩቅ ስፍራ ገለል አለች።›› [መርየም:22]

የመውለጃ ጊዜዋም ደረሰ፦

{فَأَجَآءَهَا ٱلۡمَخَاضُ إِلَىٰ جِذۡعِ ٱلنَّخۡلَةِ قَالَتۡ يَٰلَيۡتَنِي مِتُّ قَبۡلَ هَٰذَا وَكُنتُ نَسۡيٗا مَّنسِيّٗا ۝٢٣}[مريم: ٢٣]،

‹‹ምጡም፤ወደ ዘንባባይቱ ግንድ አስጠጋት፤ዋ ምኞቴ! ምነው ከዚህ በፊት በሞትኩ፤ተረስቼም የቀረሁ በኾንኩ፤አለች።›› [መርየም:23]

እዚህ ላይም ሌላ ተአምር ለነቢዩ ዒሳ ﷺ ተከሰተ፦

{فَنَادَىٰهَا مِن تَحۡتِهَآ أَلَّا تَحۡزَنِي قَدۡ جَعَلَ رَبُّكِ تَحۡتَكِ سَرِيّٗا ۝٢٤ وَهُزِّيٓ إِلَيۡكِ بِجِذۡعِ ٱلنَّخۡلَةِ تُسَٰقِطۡ عَلَيۡكِ رُطَبٗا جَنِيّٗا ۝٢٥ فَكُلِي وَٱشۡرَبِي وَقَرِّي عَيۡنٗاۖ فَإِمَّا تَرَيِنَّ مِنَ ٱلۡبَشَرِ أَحَدٗا فَقُولِيٓ إِنِّي نَذَرۡتُ لِلرَّحۡمَٰنِ صَوۡمٗا فَلَنۡ أُكَلِّمَ ٱلۡيَوۡمَ إِنسِيّٗا ۝٢٦}[مريم: ٢٤ـ ٢٦]،

‹‹ከበታቿም እንዲህ ሲል ጠራት፦ አትዘኝ፤ጌታሽ ከበታችሽ ትንሽን ወንዝ በእርግጥ አድርጓል።የዘምባባይቱንም ግንድ፤ወዳንቺ ወዝውዢት፤ባንቺ ላይ የበሰለን የተምር እሸት ታራግፍልሻለችና። ብይም፤ጠጭም፤ተደሰችም፤ከሰዎችም አንድን ብታይ፦ እኔ ለአልረሕማን ዝምታን ተስያለሁ፤ዛሬም ሰውን በፍጹም አላነጋግርም፤በይ።›› [መርየም:24-26]

ወልዳ ወደ ማሕበረሰቡ ስትመለስም ንጹይቱን ድንግል የጠበቃት አቀባባል በጣም አስጨናቂ ነበር፦

{فَأَتَتۡ بِهِۦ قَوۡمَهَا تَحۡمِلُهُۥۖ قَالُواْ يَٰمَرۡيَمُ لَقَدۡ جِئۡتِ شَيۡـٔٗا فَرِيّٗا ۝٢٧ يَٰٓأُخۡتَ هَٰرُونَ مَا كَانَ أَبُوكِ ٱمۡرَأَ سَوۡءٖ وَمَا كَانَتۡ أُمُّكِ بَغِيّٗا ۝٢٨}[مريم: ٢٧ـ ٢٨]،

‹‹በርሱም የተሸከመችው ኾና ወደ ዘመዶቿ መጣች፤- መርያም ሆይ! ከባድን ነገር በእርግጥ ሠራሽ አሉዋት። የሃሩን እኅት ሆይ! አባትሽ



መጥፎ ሰው አልነበረም፤እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም፤አሉዋት።›› [መርየም:27-28]

መልስ ሳትሰጥ፦

{فَأَشَارَتۡ إِلَيۡهِ}[مريم: ٢٩]،

‹‹ወደርሱም ጠቀሰች፤ ›› [መርየም:29]

እንዴት ይሆናል ብለው ተቃወሙና፦

{قَالُواْ كَيۡفَ نُكَلِّمُ مَن كَانَ فِي ٱلۡمَهۡدِ صَبِيّٗا ۝٢٩}[مريم: ٢٩]،
{قَالَ إِنِّي عَبۡدُ ٱللَّهِ ءَاتَىٰنِيَ ٱلۡكِتَٰبَ وَجَعَلَنِي نَبِيّٗا ۝٣٠ وَجَعَلَنِي مُبَارَكًا أَيۡنَ مَا كُنتُ وَأَوۡصَٰنِي بِٱلصَّلَوٰةِ وَٱلزَّكَوٰةِ مَا دُمۡتُ حَيّٗا ۝٣١ وَبَرَّۢا بِوَٰلِدَتِي وَلَمۡ يَجۡعَلۡنِي جَبَّارٗا شَقِيّٗا ۝٣٢ وَٱلسَّلَٰمُ عَلَيَّ يَوۡمَ وُلِدتُّ وَيَوۡمَ أَمُوتُ وَيَوۡمَ أُبۡعَثُ حَيّٗا ۝٣٣}[مريم: ٣٠ـ ٣٣]،

‹‹በአንቀልባ ያለን ሕጻን እንዴት እናናግራለን! አሉ።›› [መርየም:29] ‹‹(ሕጻኑም) አለ፦ እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፤መጽሐፍን ሰጥቶኛል፤ነቢይም አድርጎኛል። በየትም ስፍራ ብኾን ብሩክ አድርጎኛል፤በሕይወትም እስካለሁ ሶላትን በመስገድ፤ዘካንም በመስጠት አዞኛል። ለእናቴም ታዛዥ፤(አድርጎኛል)፤ትእቢተኛ እምቢተኛም አላደረገኝም።› ሰላምም በኔ ላይ ነው፤በተወለድሁ ቀን፤በምሞትበትም ቀን፤ሕያው ኾኘ በምቀሰቀስበትም ቀን፤ ›› [መርየም:30-33]

ከአይሁድ ከፊሉ እውነት አይደለም ብለው አስተባበሉ፤አላህ (ሱ.ወ.) የጠራትንና ያነጻትን ድንግል በከባድ ኀጢአት ወነጀሉ።

{وَبِكُفۡرِهِمۡ وَقَوۡلِهِمۡ عَلَىٰ مَرۡيَمَ بُهۡتَٰنًا عَظِيمٗا ۝١٥٦}[النساء: ١٥٦]،

‹‹በመካዳቸውም፤በመርየም ላይ ከባድ ቅጥፈትን በመናገራቸውም ምክንያት፤(ረገምናቸው)።›› [አል ኒሳእ: 156]

ድንግሏን በዝሙት ሲወነጅሉም አላህ (ሱ.ወ.) ንጽሕናዋንና ቅድስናዋን እንዲህ ሲል አረጋገጠ፦

{وَأُمُّهُۥ صِدِّيقَةٞ}[المائدة: ٧٥]؛

‹‹እናቱም በጣም እውነተኛ ናት፤ ›› [አል ማእዳህ:75]

አላህ (ሱ.ወ.) በዒሳ ﷺ ነቢይነትና በመልክታቸው ያመነች መሆኗን አረጋገጠ። ጸጋውንም ለአገልጋዩና ለመልክተኛው ዒሳና ለድንግል እናቱ ዘረጋ።

{إِذۡ قَالَ ٱللَّهُ يَٰعِيسَى ٱبۡنَ مَرۡيَمَ ٱذۡكُرۡ نِعۡمَتِي عَلَيۡكَ وَعَلَىٰ وَٰلِدَتِكَ

{إِذۡ أَيَّدتُّكَ بِرُوحِ ٱلۡقُدُسِ تُكَلِّمُ ٱلنَّاسَ فِي ٱلۡمَهۡدِ وَكَهۡلٗاۖ وَإِذۡ عَلَّمۡتُكَ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ وَٱلتَّوۡرَىٰةَ وَٱلۡإِنجِيلَ}[المائدة: ١١٠]،

‹‹አላህ በሚል ጊዜ (አስታውስ)፦ የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! በአንተና በእናትህ ላይ (የዋልኩላችሁን) ጸጋዬን አስታውስ፤በሕጻንነትና በከፊኒሳነት (የበሰለ ሰው ኾነህ) ሰዎችን የምታናግር ስትኾን፣በቅዱሱ መንፈስ (በገብርኤል) ባበረታሁህ ጊዜ፣ጽሕፈትንና ጥበብንም፣ተውራትንና እንጂልንም፣ባስተማርኩህ ጊዜ፣›[አል ማእዳህ፡110]

በታኣምራትና በተለያዩ ምልክቶችም አገዘው፦

{وَإِذۡ تَخۡلُقُ مِنَ ٱلطِّينِ كَهَيۡـَٔةِ ٱلطَّيۡرِ بِإِذۡنِي فَتَنفُخُ فِيهَا فَتَكُونُ طَيۡرَۢا بِإِذۡنِيۖ وَتُبۡرِئُ ٱلۡأَكۡمَهَ وَٱلۡأَبۡرَصَ بِإِذۡنِيۖ وَإِذۡ تُخۡرِجُ ٱلۡمَوۡتَىٰ بِإِذۡنِيۖ وَإِذۡ كَفَفۡتُ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ عَنكَ إِذۡ جِئۡتَهُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِ فَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنۡهُمۡ إِنۡ هَٰذَآ إِلَّا سِحۡرٞ مُّبِينٞ ۝١١٠ وَإِذۡ أَوۡحَيۡتُ إِلَى ٱلۡحَوَارِيِّـۧنَ أَنۡ ءَامِنُواْ بِي وَبِرَسُولِي قَالُوٓاْ ءَامَنَّا وَٱشۡهَدۡ بِأَنَّنَا مُسۡلِمُونَ ۝١١١}[المائدة: ١١٠- ١١١]،

‹‹ከጭቃም የወፍ ቅርጽ ብጤ በፈቃዴ በምትሠራና በውስጧ በምትነፋ፣በፈቃዴም ወፍ በምትኾን ጊዜ፣ዕውርም ኾኖ የተወለደንና ለምጻምንም በፈቃዴ በምታሽር ጊዜ፣ሙታንንም በፈቃዴ (ከመቃብራቸው) በምታወጣ ጊዜ፣የእስራኤልንም ልጆች በተአምራት በመጣህባቸውና ከነሱ እነዚያ የካዱት ይህ ግልጽ ድግምት እንጅ ሌላ አይደለም ባሉ ጊዜ፣(ሊገድሉህ ሲያስቡህ) ከአንተ ላይ በከለከልኩልህም ጊዜ፣(ያደረግሁልህን ውለታ አስታውስ)። ወደ ሐዋርያትም በኔና በመልክተኛዬ እመኑ፣በማለት ባዘዝኩ ጊዜ፣(አስታውስ)፤አመንን፤እኛም ሙስሊሞች መኾናችንን፣መስክር አሉ።››[አልማእዳህ፡110]

## ነቢዩ ዒሳ ﷷ ወንጌል ውስጥ ፈጣሪ አምላክ አንድ መሆኑን ያረጋግጣሉ

‹‹ከጻፎችም አንዱ ቀርቦ ሲከራከሩ ሰማና መልካም አድርጎ እንደመለሰላቸው አስተውሎ፦ ከሁሉ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ማናቸይቱ ናት? ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ፦ እስራኤል ሆይ፣ስማ፤ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፣አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።››
ማርቆስ 12፤28-35



በኋላ ላይም ሐዋርያት ማእድ ከሰማይ ያወርድላቸው ዘንድ ለጌታቸው ለአላህ እንዲጸልዩ ነቢዩ ዒሳን ﷷ ጠየቁ። ይህን በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِذۡ قَالَ ٱلۡحَوَارِيُّونَ يَٰعِيسَى ٱبۡنَ مَرۡيَمَ هَلۡ يَسۡتَطِيعُ رَبُّكَ أَن يُنَزِّلَ عَلَيۡنَا مَآئِدَةٗ مِّنَ ٱلسَّمَآءِ}[المائدة: ١١٢]،

‹‹ሐዋርያት፦ የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! ጌታህ በኛ ላይ ከሰማይ ማእድን ሊያወርድልን ይችላልን? ባሉ ጊዜ (አስታውስ)፤››[አል ማእዳህ፡112]

ነቢዩ ዒሳ ﷷ ግን ሐዋርያቱ ለጸጋው ተገቢውን ተግባራዊ ምስገና አያደርሱ ይሆናል ብለው ሰጉ፦

{قَالَ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ۝١١٢ قَالُواْ نُرِيدُ أَن نَّأۡكُلَ مِنۡهَا وَتَطۡمَئِنَّ قُلُوبُنَا وَنَعۡلَمَ أَن قَدۡ صَدَقۡتَنَا وَنَكُونَ عَلَيۡهَا مِنَ ٱلشَّٰهِدِينَ ۝١١٣}[المائدة: ١١٢- ١١٣]،

‹‹ምእመናን እንደ ኾናችሁ አላህን ፍሩ አላቸው።››[አል ማእዳህ፡112-113]

ነቢዩም ﷷ ጌታቸውን ለመኑም፦

{قَالَ عِيسَى ٱبۡنُ مَرۡيَمَ ٱللَّهُمَّ رَبَّنَآ أَنزِلۡ عَلَيۡنَا مَآئِدَةٗ مِّنَ ٱلسَّمَآءِ تَكُونُ لَنَا عِيدٗا لِّأَوَّلِنَا وَءَاخِرِنَا وَءَايَةٗ مِّنكَۖ وَٱرۡزُقۡنَا وَأَنتَ خَيۡرُ ٱلرَّٰزِقِينَ ۝١١٤ قَالَ ٱللَّهُ إِنِّي مُنَزِّلُهَا عَلَيۡكُمۡۖ فَمَن يَكۡفُرۡ بَعۡدُ مِنكُمۡ فَإِنِّيٓ أُعَذِّبُهُۥ عَذَابٗا لَّآ أُعَذِّبُهُۥٓ أَحَدٗا مِّنَ ٱلۡعَٰلَمِينَ ۝١١٥}[المائدة: ١١٤- ١١٥]،

‹‹የመርም ልጅ ዒሳ አለ፦ ጌታችን አላህ ሆይ! ለኛ ለመጀመሪያዎቻችንና ለመጨረሻዎቻችን ባዕል (መደሰቻ) የምትኾንን፣ከአንተም ተአምር የኾነችን ማእድ፣ከሰማይ በኛ ላይ አውርድ፤ስጠንም፤አንተ ከሰጪዎች ሁሉ በላጭ ነህና። አላህ፦ እኔ (ማእድዋን) በናንተ ላይ አውራጅዋ ነኝ፤በኋላም ከናንተ የሚክድ ሰው፣እኔ ከዓለማት አንድንም የማልቀጣውን ቅጣት እቀጣዋለሁ አለ።››[አል ማእዳህ፡114-115]

ማእዱ ከወረደላቸውና ከተቋደሱት መካከል ከፊሉ ከሓዲ ሆነ።

የአላህን ነቢይ ዒሳን ﷷ ያስተባበሉት አይሁዶች ክደታቸውና በዒሳ ﷷ ላይ የሚሸርቡት ሴራቸው እንደቀጠለ ዘለቀ፦

{وَمَكَرُواْ وَمَكَرَ ٱللَّهُۖ وَٱللَّهُ خَيۡرُ ٱلۡمَٰكِرِينَ ۝٥٤}[آل عمران: ٥٤]،

‹‹(አይሁዶችም) አደሙ፤አላህም አድማቸውን መለሰባቸው፤አላህም ከአድመኞች ሁሉ በላጭ ነው።››[ኣሊ ዒምራን፡54]

አላህ (ሱ.ወ.) ግን አድማቸውን ለነቢዩ ዒሳ ﷷ አጋልጦ እንዴት ከተንኮላቸው እንደሚያድናቸውም ነገራቸው፦

{إِذۡ قَالَ ٱللَّهُ يَٰعِيسَىٰٓ إِنِّي مُتَوَفِّيكَ وَرَافِعُكَ إِلَيَّ وَمُطَهِّرُكَ مِنَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَجَاعِلُ ٱلَّذِينَ ٱتَّبَعُوكَ فَوۡقَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِۖ ثُمَّ إِلَيَّ مَرۡجِعُكُمۡ فَأَحۡكُمُ بَيۡنَكُمۡ فِيمَا كُنتُمۡ فِيهِ تَخۡتَلِفُونَ ۝٥٥}

https://www.path-2-happiness.com/am



[آل عمران: ٥٥]،

‹‹አላህም ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤ዒሳ ሆይ! እኔ ወሳጅህ፣ወደ እኔም አንሺህ ነኝ፤ከነዚያም ከካዱት ሰዎች አጥሪህም (ከጉርብትናቸው አራቂህ) ነኝ፤እነዚያንም የተከተሉህን እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ፣ከነዚያ ከካዱት በላይ አድራጊ ነኝ፤ከዚያም መመለሻችሁ ወደኔ ነው፤በርሱ ትለያዩበት በነበራችሁት ነገር በመካከላችሁ እፈርዳለሁ::››[ኣሊ. ዒምራን:55]

ቃል ኪዳን ማፍረሳቸውን፣ሴራ መጎንጎናቸውን፣ክህደታቸውን፣የአላህን ነቢያት ለመግደል መሞከራቸውን፣ክብርቷን ቅድስት ድንግል መርየምን በሐሰት መወንጀላቸውን ሲገፉበት አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ አለ፦

{فَبِمَا نَقْضِهِم مِّيثَٰقَهُمْ وَكُفْرِهِم بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ وَقَتْلِهِمُ ٱلْأَنۢبِيَآءَ بِغَيْرِ حَقٍّ وَقَوْلِهِمْ قُلُوبُنَا غُلْفٌۢ ۚ بَلْ طَبَعَ ٱللَّهُ عَلَيْهَا بِكُفْرِهِمْ فَلَا يُؤْمِنُونَ إِلَّا قَلِيلًا ﴿١٥٥﴾ وَبِكُفْرِهِمْ وَقَوْلِهِمْ عَلَىٰ مَرْيَمَ بُهْتَٰنًا عَظِيمًا ﴿١٥٦﴾ وَقَوْلِهِمْ إِنَّا قَتَلْنَا ٱلْمَسِيحَ عِيسَى ٱبْنَ مَرْيَمَ رَسُولَ ٱللَّهِ}[النساء: ١٥٥-١٥٧]،

‹‹ቃል ኪዳናቸውንም በማፍረሳቸው፣በአላህም አንቀጾች በመካዳቸው፣ነቢያትንም ያለ አግባብ በመግደላቸውና ልቦቻችን ሽፍኖች ናቸው በማለታቸው ምክንያት፣(ረገምናቸው)፤በውነቱ በክህደታቸው ምክንያት አላህ በርሷ ላይ አተመ፤ስለዚህ ጥቂትን እንጅ አያምኑም:: በመካዳቸውም፣በመርየም ላይ ከባድ ቅጥፈትን በመናገራቸውም ምክንያት፣(ረገምናቸው):: ፦እኛ የአላህን መልክተኛ፣የመርምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸውም፣(ረገምናቸው)፤››[አል ኒሳእ:155-157]

አላህ (ሱ.ወ.) ግን ከመግደል ሙከራቸው ነቢዩ ዒሳን عليه السلام አዳነ፦

{وَمَا قَتَلُوهُ وَمَا صَلَبُوهُ}[النساء: ١٥٧]

‹‹አልገደሉትም፤አልሰቀሉትምም፤›[አል ኒሳእ:157]

የገደሉት ግን በዒሳ የተመሰለላቸውን ሰው ነበር፦

{وَلَٰكِن شُبِّهَ لَهُمْ ۚ وَإِنَّ ٱلَّذِينَ ٱخْتَلَفُوا۟ فِيهِ لَفِى شَكٍّ مِّنْهُ ۚ مَا لَهُم بِهِۦ مِنْ عِلْمٍ إِلَّا ٱتِّبَاعَ ٱلظَّنِّ ۚ وَمَا قَتَلُوهُ يَقِينًۢا ﴿١٥٧﴾ بَل رَّفَعَهُ ٱللَّهُ إِلَيْهِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَزِيزًا حَكِيمًا ﴿١٥٨﴾}[النساء: ١٥٧-١٥٨]،





‹‹ግን ለነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ፤እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት፣ከርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፤ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፤በእርግጥም አልገደሉትም:: ይልቁንስ አላህ ወደርሱ አነሳው፤ አላህም አሸናፊ፣ጥበበኛ ነው::››[አል ኒሳእ:157-158]

አላህ (ሱ.ወ.) አገልጋዩንና መልክተኛውን ዒሳ عليه السلام ከተንኮላቸው አድኖ ወደራሱ ከፍ አደረጋቸው፦

{وَإِن مِّنْ أَهْلِ ٱلْكِتَٰبِ إِلَّا لَيُؤْمِنَنَّ بِهِۦ قَبْلَ مَوْتِهِۦ ۖ وَيَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ يَكُونُ عَلَيْهِمْ شَهِيدًا ﴿١٥٩﴾}[النساء: ١٥٩].

‹‹ከመጽሐፉም ሰዎች ከመሞቱ በፊት፣በርሱ (በዒሳ) በእርግጥ የሚያምን እንጅ (አንድም) የለም፤ በትንሣኤም ቀን በነሱ ላይ መስካሪ ይኾናል::››[አል ኒሳእ:159]

እናም ይህ የመርየም ልጅ የዒሳ [የአላህ ሰላም በሁለቱም ላይ ይሁን] ታሪክ እውነታ ነው፦

{ذَٰلِكَ عِيسَى ٱبْنُ مَرْيَمَ ۚ قَوْلَ ٱلْحَقِّ ٱلَّذِى فِيهِ يَمْتَرُونَ ﴿٣٤﴾ مَا كَانَ لِلَّهِ أَن يَتَّخِذَ مِن وَلَدٍ ۖ



https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am



## ዒሳ . . እስላም ዘንድ

‹‹እስላምን ባጠናሁ ጊዜ ጥልቅ የሆነ ስሜት አውስጤ የፈጠረ የተለየ ሌላ የአልመሲሕ ዒሳን ﷵ ገጽታ ነበር ያየሁት።

ፍሬድሪክ ዶላማርክ
የጆሃንስበርግ ሊቀ ጳጳስ

{سُبۡحَٰنَهُۥٓۚ إِذَا قَضَىٰٓ أَمۡرٗا فَإِنَّمَا يَقُولُ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ٣٥} [مريم: ٣٤ـ ٣٥]،

‹‹ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው፤ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው። ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም፤(ከጉድለት ሁሉ) ጠራ፤ነገርን በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው ኹን ነው፣ወዲያውም ይኾናል።››[መርየም:35]

አላህ (ሱ.ወ.) የሁሉም ነገር ፈጣሪና ገዥ ጌታ በመሆኑ ልጅ መውለድ ለርሱ ተገቢው አለመሆኑን፣እርሱ ከምንምና ከማንም የተብቃቃ ሲሆን ሁሉም ሁሉንም ነገር ከርሱ ፈላጊዎችና ከጃዮች፣ለርሱም ታዛዦችና ተገዥዎች መሆናቸውን፣በሰማያትና በምድር የሚገኙ ሁሉ አገልጋይ ባሮቹ ሲሆኑ እርሱ ግን ብቸኛው አንድ አምላካቸውና ጌታቸው መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) አብራርቷል።

## ወንጌል ስቅለትን ያስተባብላል ዕርገትን ያረጋግጣል

- ‹‹ስለዚህ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ኢየሱስ ግን ተሰወራቸው ከመቅደስም ወጥቶ በመካከላቸው አልፎ ሄደ።›› ዮሐ 8፣59
- ‹‹እንግዲህ ደግመው ሊይዙት ፈለጉ፤ከእጃቸውም ወጣ።›› ዮሐ 10፣39
- ‹‹ይህ የሆነ ከእርሱ አጥንት አይሰበርም የሚል የመጽሐፉ ቃል እንዲፈጸም ነው።›› ዮሐ 19፣36
- ‹‹ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ . . ›› የሐዋ ሥራ 1፣11





## 5- ሙሐመድ ﷺ

ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ የነቢያትና የመልክተኞች መደምደሚያ ሲሆኑ፣የእስራኤል ቤት ነቢያት መደምደሚያ የሆኑት ነቢዩ ዒሳ ﷵ በነቢዩ ሙሐመድ ﷺ መምጣት ሕዝባቸውን አብስረዋል። ይህን በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذۡ قَالَ عِيسَى ٱبۡنُ مَرۡيَمَ يَٰبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ إِنِّي رَسُولُ ٱللَّهِ إِلَيۡكُم مُّصَدِّقٗا لِّمَا بَيۡنَ يَدَيَّ مِنَ ٱلتَّوۡرَىٰةِ وَمُبَشِّرَۢا بِرَسُولٖ يَأۡتِي مِنۢ بَعۡدِي ٱسۡمُهُۥٓ أَحۡمَدُۖ فَلَمَّا جَآءَهُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِ قَالُواْ هَٰذَا سِحۡرٞ مُّبِينٞ ٦}[الصف: ٦]،

‹‹የመርየም ልጅ ዒሳም፦ የእስራኤል ልጆች ሆይ! ፦እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ፣ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን፣ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ፣ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤በግልጽ ታምራቶች በመጣቸውም ጊዜ፣ይህ ግልጽ ድግምት ነው፣አሉ።››[አል ሶፍ:6]

ይህ የብስራት ትንቢትም በተውራትና በኢንጂልም ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ يَتَّبِعُونَ ٱلرَّسُولَ ٱلنَّبِيَّ ٱلۡأُمِّيَّ ٱلَّذِي يَجِدُونَهُۥ مَكۡتُوبًا عِندَهُمۡ فِي ٱلتَّوۡرَىٰةِ وَٱلۡإِنجِيلِ يَأۡمُرُهُم بِٱلۡمَعۡرُوفِ وَيَنۡهَىٰهُمۡ عَنِ ٱلۡمُنكَرِ وَيُحِلُّ لَهُمُ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَيُحَرِّمُ عَلَيۡهِمُ ٱلۡخَبَٰٓئِثَ وَيَضَعُ عَنۡهُمۡ إِصۡرَهُمۡ وَٱلۡأَغۡلَٰلَ ٱلَّتِي كَانَتۡ عَلَيۡهِمۡۚ فَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِهِۦ وَعَزَّرُوهُ وَنَصَرُوهُ وَٱتَّبَعُواْ ٱلنُّورَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ مَعَهُۥٓ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ١٥٧}[الأعراف: ١٥٧]،

‹‹ለነዚያ፣ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን፣የማይጽፍና የማያነብ ነቢይ የኾነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለኾኑት፣(በእርግጥ እጽፋታለሁ)፤በበጎ ሥራ ያዛቸዋል፤ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል፤መልካም ነገሮችንም ለነርሱ ይፈቅድላቸዋል፤መጥፎ ነገሮችንም በነሱ ላይ እርም ያደርግባቸዋል። ከነሱም ላይ ሸክማቸውንና እነዚያንም በነሱ

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ላይ የነበሩትን እንዛዝላዎች (ከባድ ሕግጋቶች) ያነሳላቸዋል፤እነዚያም በርሱ ያመኑ፣ያከበሩትም፣የረዱትም፣ያንንም ከርሱ ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ፣እነዚያ እነሱ የሚድኑ ናቸው::››[አል አዕራፍ:157]

ይልቅዬም በሕይወት እያሉ ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ቢላኩ እንዲያምኑባቸውና እንዲደግፉአቸው፣ይህንኑም ለሕዝቦቻቸው እንዲያሳውቁ አላህ (ሱ.ወ.) ሁሉንም ነቢያት ቃል ኪዳን አስገብቷል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذۡ أَخَذَ ٱللَّهُ مِيثَٰقَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ لَمَآ ءَاتَيۡتُكُم مِّن كِتَٰبٖ وَحِكۡمَةٖ ثُمَّ جَآءَكُمۡ رَسُولٞ مُّصَدِّقٞ لِّمَا مَعَكُمۡ لَتُؤۡمِنُنَّ بِهِۦ وَلَتَنصُرُنَّهُۥۚ قَالَ ءَأَقۡرَرۡتُمۡ وَأَخَذۡتُمۡ عَلَىٰ ذَٰلِكُمۡ إِصۡرِيۖ قَالُوٓاْ أَقۡرَرۡنَاۚ قَالَ فَٱشۡهَدُواْ وَأَنَا۠ مَعَكُم مِّنَ ٱلشَّٰهِدِينَ ٨١} [آل عمران: ٨١].

‹‹አላህ የነቢያትን ቃል ኪዳን፣ከመጽሐፍና ከጥበብ ሰጥቻችሁ ከዚያም ከእናንተ ጋር ላለው (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ መልክተኛ ቢመጣላችሁ በርሱ በእርግጥ እንደምታምኑበት በእርግጥም እንድትረዱት ሲል በያዘ ጊዜ (አስታውስ)፤አረጋገጣችሁን? በየሃችሁ ላይ ኪዳኔን ያዛችሁምን? አላቸው፤አረጋገጥን አሉ፤እንግዲያስ መስክሩ፤እኔም ከእናንተ ጋር ከመስካሪዎቹ ነኝ አላቸው::››[ኣሊ. ዒምራን:81]

ቅዱስ ቁርኣንም እነዚያን ብሥራቶች አውስቶ ለሙሐመድ ﷺ እውነተኛነት ማስረጃ አድርጓል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَيَقُولُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَسۡتَ مُرۡسَلٗاۚ قُلۡ كَفَىٰ بِٱللَّهِ شَهِيدَۢا بَيۡنِي وَبَيۡنَكُمۡ وَمَنۡ عِندَهُۥ عِلۡمُ ٱلۡكِتَٰبِ ٤٣} [الرعد: ٤٣]،

‹‹እነዚያም የካዱት ሰዎች፣መልክተኛ አይደለህም ይላሉ፤በኔና በናንተ መካከል መስካሪ በአላህና እርሱ ዘንድ የመጽሐፉ ዕውቀት ባለው ሰው በቃ፣በላቸው::››[አል ረዕድ:43]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِنَّهُۥ لَفِي زُبُرِ ٱلۡأَوَّلِينَ ١٩٦ أَوَ لَمۡ يَكُن لَّهُمۡ ءَايَةً أَن يَعۡلَمَهُۥ عُلَمَٰٓؤُاْ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ١٩٧} [الشعراء: ١٩٦-١٩٧]،

‹‹እርሱም (ቁርኣን) በቀድሞዎቹ መጻሕፍት ውስጥ (የተወሳ) ነው:: የእስራኤል





ልጆች ሊቃውንት፣የሚያውቁት መኾኑ፣ለነርሱ (ለመካ ከሓዲዎች) ምልክት አይኾናቸውምን?››[አል ሹዐራ:196-197]

በብሉይና አዲስ ኪዳኖች ውስጥ ወደፊት እንደሚላኩ የተበሰረ ከመሆኑ አንጻር፣ልጆቻቸውን የሚያውቁትን ያህል ሙሐመድን ﷺ በማወቃቸው የመጀመሪያዎቹ አማኞች መሆን ይገባቸው ስለነበረው የመጽሐፉ ሰዎችም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ ءَاتَيۡنَٰهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ يَعۡرِفُونَهُۥ كَمَا يَعۡرِفُونَ أَبۡنَآءَهُمۡۖ وَإِنَّ فَرِيقٗا مِّنۡهُمۡ لَيَكۡتُمُونَ ٱلۡحَقَّ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ ١٤٦} [البقرة: ١٤٦]،

‹‹እነዚያ መጽሐፍን የሰጠናቸው፣ወንዶች ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (በመጽሐፋቸው ምልክቱ ተነግሯልና ሙሐመድን) ያውቁታል፤ከነሱም የተለዩ ክፍሎች፣እነርሱ የሚያውቁ ሲኾኑ ውነቱን በእርግጥ ይደብቃሉ::››[አል በቀራህ:146]

በተጨማሪም እንዲህ ብሏል፦

{وَلَمَّا جَآءَهُمۡ رَسُولٞ مِّنۡ عِندِ ٱللَّهِ مُصَدِّقٞ لِّمَا مَعَهُمۡ نَبَذَ فَرِيقٞ مِّنَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ كِتَٰبَ ٱللَّهِ وَرَآءَ ظُهُورِهِمۡ كَأَنَّهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ ١٠١} [البقرة: ١٠١]،

‹‹እነርሱ ጋርም ላለው (መጽሐፍ)፣አረጋጋጭ የኾነ መልክተኛ ከአላህ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ፣ከነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ከፊሉ እነርሱ እንደማያውቁ ኾነው የአላህን መጽሐፍ ከጀርባዎቻቸው ኋላ ጣሉ::››[አል በቀራህ:101]

አላህ (ሱ.ወ.) በመጨረሻው ዘመን እንደሚላክ የተናገረው ነቢይ



https://www.path-2-happiness.com/am

ሙሐመድ ﷺ መሆናቸውን ሁሉም ትንቢታዊ ብስራቶች በግልጽ ያመለክቱ ቢሆንም፣ከመጽሐፉ ባለቤቶች ከፊሎቹ ግን እያወቁ በቅዱሳን መጽሐፎቻቸው ውስጥ የሰፈረውን እውነታ በመደበቅ የማያውቁ ለመምሰል ይሞክራሉ።

ከርሳቸው በፊት የነበሩት ነቢያትና መልክተኞች ይዘው እንደመጡ ሁሉ፣ነቢዩ ሙሐመድም ﷺ አንድ አላህን ብቻ ያለ ምንም ማጋራት የማምለክን የተውሒድ ጥሪ ይዘው ነው የመጡት። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِيٓ إِلَيۡهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعۡبُدُونِ ﴿٢٥﴾} [الأنبياء: ٢٥].

«ከአንተ በፊትም፣እነሆ ከኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ፣በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም።»[አል አንቢያ፡25]

የተላኩትም ከርሳቸው በፊት የነበሩትን ነቢያትና መልክተኞች ተልእኮ በማረጋገጥና ያለ ምንም ልዩነት በሁሉም በማመን ነው።

{لَا نُفَرِّقُ بَيۡنَ أَحَدٖ مِّنۡهُمۡ}[البقرة: ١٣٦].

«ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤»[አል በቀራህ፡136]

ይህ ብቻም ሳይሆን በሙሐመድ ﷺ አምኖ ከተቀሩት የአላህ ነቢያትና መልክተኞች ውስጥ በአንዱም እንኳ ሳያምን የቀረ ሰው፣በሙሐመድም ያላመነ ስለመሆኑ ቁርአን ውስጥ ሰፍሯል፦

{شَرَعَ لَكُم مِّنَ ٱلدِّينِ مَا وَصَّىٰ بِهِۦ نُوحٗا وَٱلَّذِيٓ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ وَمَا وَصَّيۡنَا بِهِۦٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ وَعِيسَىٰٓۖ أَنۡ أَقِيمُواْ ٱلدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُواْ فِيهِۚ} [الشورى: ١٣].

«ለናንተ ከሃይማኖት ያንን ኑሕ ያዘዘበትን ደነገገላችሁ፤ያንንም ወደ አንተ ያወረድነውን፣ያንንም በርሱ ኢብራሂምን፣ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን፣ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ፣በርሱም አትለያዩ፣ማለትን (ደነገግን)፤»[አል ሹራ፡13]

ነቢዩ ﷺ የአላህ መልክተኛና አገልጋይ ባሪው መሆናቸውንም አረጋግጧል፦

{قُلۡ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٞ مِّثۡلُكُمۡ يُوحَىٰٓ إِلَيَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۖ فَمَن كَانَ يَرۡجُواْ لِقَآءَ رَبِّهِۦ فَلۡيَعۡمَلۡ عَمَلٗا صَٰلِحٗا وَلَا يُشۡرِكۡ بِعِبَادَةِ رَبِّهِۦٓ أَحَدَۢا ﴿١١٠﴾} [الكهف: ١١٠].

«፦ እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ወደኔ የሚወረድልኝ ብጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ፤የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤መልካም ሥራ ይሥራ፤በጌታውም መግገዛት አንድንም አያጋራ፣በላቸው።»[አል ከህፍ፡110]

እርሳቸውን አስመልክቶ የመጽሐፎቹ ባለቤቶች ምልክታቸውን በግልጽ ያውቁ ዘንድ በቀደሙት ቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ እንደ ሰፈረው ሁሉ፣ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ የማያነቡና የማይጽፉ ነቢይ ነበሩ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ يَتَّبِعُونَ ٱلرَّسُولَ ٱلنَّبِيَّ ٱلۡأُمِّيَّ ٱلَّذِي يَجِدُونَهُۥ مَكۡتُوبًا عِندَهُمۡ فِي ٱلتَّوۡرَىٰةِ وَٱلۡإِنجِيلِ يَأۡمُرُهُم بِٱلۡمَعۡرُوفِ وَيَنۡهَىٰهُمۡ عَنِ ٱلۡمُنكَرِ وَيُحِلُّ لَهُمُ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَيُحَرِّمُ عَلَيۡهِمُ ٱلۡخَبَٰٓئِثَ وَيَضَعُ عَنۡهُمۡ إِصۡرَهُمۡ وَٱلۡأَغۡلَٰلَ ٱلَّتِي كَانَتۡ عَلَيۡهِمۡۚ فَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِهِۦ وَعَزَّرُوهُ وَنَصَرُوهُ وَٱتَّبَعُواْ ٱلنُّورَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ مَعَهُۥٓ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ﴿١٥٧﴾} [الأعراف: ١٥٧].

«ለነዚያ፣ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን፣የማይጽፍና የማያነብ ነቢይ የኾነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለኾኑት፣(በእርግጥ እጽፋታለሁ)፤በበጎ ሥራ ያዛቸዋል፤ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል፤መልካም ነገሮችንም ለነርሱ ይፈቅድላቸዋል፤መጥፎ ነገሮችንም በነሱ ላይ እርም ያደርግባቸዋል። ከነሱም ላይ ሸክማቸውንና እነዚያንም በነሱ ላይ የነበሩትን እንዛዝላዎች (ከባድ ሕግጋቶች) ያነሳላቸዋል፤እነዚያም በርሱ ያመኑ፣ያከበሩትም፣የረዱትም፣ያንንም ከርሱ ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ፣እነዚያ እነሱ የሚድኑ ናቸው።»[አል አዕራፍ፡157]

በቀደሙት ነቢያት እጅ አላህ (ሱ.ወ.) ተአምራትን እንዳሳየ ሁሉ፣በነቢዩ ሙሐመድ ﷺ እጅም ብዙ ቁሳዊ ተአምራቶችን አሳይቷል። ከተሰጧቸው ተአምራቶች ሁሉ ትልቁና ዋነኛው ሕያው ተአምር ግን፣የቀድሞዎቹና የመጪዎቹ






**ሙሐመድ . . የመጨረሻውና የመደምደሚያው መልክተኛ**

‹‹ምክንያቱም በዚያን ወቅት እግዚአብሔር እኔን ከምድር ላይ ይወስደኛና እኔን አሳልፎ የሸጠውን ከሐዲ መልኩን በመቀየር እኔን እንዲመስል ያደርገዋል፣ሰዎችም እኔ የተገደልኩ ይመስላቸዋል። እርሱ ይህን የውርደት ሞት ከሞተ በኋላም ክብሬን ተነፍጌ ለረዥም ዘመን በዓለም እኖራለሁ። ነገር ግን ቅዱሱ የእግዚአብሔር መልክተኛ ሙሐመድ በሚመጣ ጊዜ ይህ ውርደት ከኔ ይወገዳል።›› (በርናባስ ወንጌል ምዕ 112 ቁጥር 13-16)

**የበርናባስ ወንጌል**

https://www.path-2-happiness.com/am

ዜና ያለበት፣ማብራሪያ፣መመሪያ፣እዝነትና ብስራት የተካተተበት ታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ ቁርኣን ነው።

{وَنَزَّلۡنَا عَلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَ تِبۡيَٰنٗا لِّكُلِّ شَيۡءٖ وَهُدٗى وَرَحۡمَةٗ وَبُشۡرَىٰ لِلۡمُسۡلِمِينَ ٨٩}[النحل: ٨٩]،

‹‹መጽሐፉንም፣ለሁሉ ነገር አብራሪ፣መሪም እዝነትም፣ለሙስሊሞችም አብሳሪ ኾኖ ባንተ ላይ አወረድነው።››[አል ነሕል:89]

ቁርኣን ለምእመናን የልብ ብርሃን ነው፦

{هَٰذَا بَصَٰٓئِرُ لِلنَّاسِ وَهُدٗى وَرَحۡمَةٞ لِّقَوۡمٖ يُوقِنُونَ ٢٠}[الجاثية: ٢٠]،

‹‹ይህ (ቁርኣን) ለሰዎች የልብ ብርሃኖች ነው። ለሚያረጋግጡም ሕዝቦች መሪና እዝነት ነው።››[አል ጃሢያ:20]

የማያነበውና የማይጽፈው ነቢይ ﷺ ሰዎች የተወዛገቡባቸውን ጉዳዮች በቁርኣን አብራርቶላቸዋል፦

{وَمَآ أَنزَلۡنَا عَلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَ إِلَّا لِتُبَيِّنَ لَهُمُ ٱلَّذِي ٱخۡتَلَفُواْ فِيهِ}[النحل: ٦٤].

‹‹ባንተም ላይ መጽሐፉን አላወረድንም፣በርሱ የተለያዩበትን ለነርሱ ልታብራራላቸውና ለሚያምኑትም ሕዝቦች መሪና እዝነት ሊኾን እንጂ።››[አል ነሕል:64]

እውነተኛው ሙሐመድ እያሉ ሲጠሯቸው የኖሩት የቁረይሽ ከሃዲዎች የነቢዩን ﷺ ታማኝነትና ሐቀኝነት ቢያውቁም አስተባበሉዋቸው። አላህም (ሱ.ወ.) ከመላው የሰው ዘር ጋር ብቻ ሳይሆን ከአጋኔንትም ጋር ጭምር ተሳባስበውና ተረዳድተው ቁርኣንን የመሰለ መጽሐፍ እንዲያመጡ ተፈታታኝ ጥያቄ አቀረበላቸው፦

{قُل لَّئِنِ ٱجۡتَمَعَتِ ٱلۡإِنسُ وَٱلۡجِنُّ عَلَىٰٓ أَن يَأۡتُواْ بِمِثۡلِ هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانِ لَا يَأۡتُونَ بِمِثۡلِهِۦ}[الإسراء: ٨٨]۞

‹‹፦ ሰዎችም ጋኔኖችም የዚህን ቁርኣን ብጤ በማምጣት ላይ ቢሰባሰቡ፣ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢኾንም እንኳ ብጤውን አያመጡም፤በላቸው።››[አል እስራእ:88]

በዘመኑ የላቀ የስነጽሑፍና የቋንቋ አጠቃቀም አቅም የነበራቸው ቢሆንም ማምጣት አቅቷቸው ዋሹ። ጥያቄውን በማቅለል ከፈለጉት ኃይል ጋር ተባብረው መሰሉን አስር ምዕራፎች ብቻ እንዲያመጡ ጋበዛቸው፦፦




> **ወንጌል የሙሐመድን መምጣት ያበስራል**
>
> ‹‹ይህ የሚቆየው የእግዚአብሔር መልክተኛ የሆነው ሙሐመድ እስኪመጣ ድረስ ብቻ ነው፤እርሱ ሲመጣም በእግዚአብሔር ሕግ ለሚያምኑ ሁሉ ይህን ሽንገላ ይገልጣል።›› (በርናባስ ወንጌል ምዕ 220 ቁጥር 16)
> ‹‹እግዚአብሔር ከቴማን፣ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ይመጣል። ክብሩ ሰማያትን ከድኖአል፣ምስጋናውም ምድርን ሞልቶአል። ፀዳሉም እንደ ብርሃን ነው፤›› ትንቢተ ዕንባቆም 3፣3-4
>
> **የበርናባስ ወንጌል**

{أَمۡ يَقُولُونَ ٱفۡتَرَىٰهُۖ قُلۡ فَأۡتُواْ بِعَشۡرِ سُوَرٖ مِّثۡلِهِۦ مُفۡتَرَيَٰتٖ وَٱدۡعُواْ مَنِ ٱسۡتَطَعۡتُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ١٣}[هود: ١٣]،

‹‹ይልቁንም (ቁርኣንን) ቀጣጠፈው ይላሉን? እውነተኞች እንደ ኾናችሁ፣ብጤው የኾኑን ዐሥር የተቀጣጠፉ ሱራዎች አምጡ፤ከአላህም ሌላ የቻላችሁትን (ረዳት) ጥሩ፣በላቸው።››[ሁድ:13]

አሁንም ማምጣት ተሳናቸው። አሁንም ጥያቄውን በማቅለል መሰሉን አንድ ምዕራፍ ብቻ እንዲያመጡ ተጠየቁ፦

{وَإِن كُنتُمۡ فِي رَيۡبٖ مِّمَّا نَزَّلۡنَا عَلَىٰ عَبۡدِنَا فَأۡتُواْ بِسُورَةٖ مِّن مِّثۡلِهِۦ}[البقرة: ٢٣]؛

‹‹በባሪያችን ላይ ካወረድነው፣በመጠራጠር ውስጥ ብትኾኑ፣ከብጤው አንዲትን ምዕራፍ አምጡ፤››[አል በቀራህ:23]

ታላላቅ ባለቅኔ ገጣሚዎችና የተባ አንደበት ያላቸው ተናጋሪዎች እያሏቸው የተባሉትን ማምጣት አሁንም ሳይችሉ ቀሩ። የቁረይሽ ከሓዲዎችም ነቢዩን ማስተባበል ገፉበት። አላህ (ሱ.ወ.) ግን እንደ ኢብራሂም፣ኑሕ፣ሙሳና ዒሳ ያሉ [የአላህ ሰላም በሁሉም ላይ ይሁን] ቁርጠኞቹ የትዕግስትና የጽናት ባለቤቶች (ኡሉል ዐዝም) ነቢያትና መልክተኞች እንዳደረጉ ሁሉ እንዲታገሱ ነቢዩን ﷺ አዘዛቸው፦

{فَٱصۡبِرۡ كَمَا صَبَرَ أُوْلُواْ ٱلۡعَزۡمِ مِنَ ٱلرُّسُلِ}[الأحقاف: ٣٥]،

‹‹ከመልክተኞችም የቆራጥነት ባለቤቶች የኾኑት እንደ ታገሡ ሁሉ ታገሥ፤።››[አል አሕቃፍ:35]

ነቢዩም ﷺ በአንደበታቸውና በምጡቅ ስነምግባራቸው በትዕግስትና በጥበብ እያስተማሯቸውና እየመከሯቸው



> **አርአያና ታላቅ አብነት**
>
> ‹‹በታሪክ ውስጥ ታላቅ አብነትና አርአያን ለማወቅ ተመራምሬ ዐረባዊውን ነቢይ ሙሐመድን አገኘሁ።››
>
> **ጎቴህ ጎቴህ**
> **ጀርመናዊ ባለቅኔ**



> **ጠይቅ . . ቁርኣን መልስ ይሰጠሃል**
>
> ‹‹ቁርኣን አጠናሁና ለሁሉም የሕይወት ጥያቄዎች መልሶችን አገኘሁበት።››
>
> **ማይክል ሃርት**
> **አሜሪካዊ ጸሐፊ**



ለሰዎችም አሕመድ

‹‹ክርስቲያኖች ዘንድ በስፋት የሚታወቀውና፡- ‹ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፣ሰላምም በምድር፣ለሰውም በጎ ፈቃድ . . › የሚለው አባባል እንደዚያ ሳይሆን፡- ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፣እስላምም በምድር፣ለሰዎችም አሕመድ፤ የሚል መሆን ነበረበት::››

ዴቪድ ቤንጃሚን ከልዳኒ
የቀድሞው የሞሲል ጳጳስ

ደዕዋቸውን ቀጠሉ:: ከከሓዲዎቹ ተንኮልም አላህ ጠበቃቸው፦

{يَـٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ حَسۡبُكَ ٱللَّهُ وَمَنِ ٱتَّبَعَكَ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ٦٤}[الأنفال: ٦٤]، {أَلَيۡسَ ٱللَّهُ بِكَافٍ عَبۡدَهُۥ}[الزمر: ٣٦]،

‹‹አንተ ነቢዩ ሆይ! በቂህ አላህ ነው፤ለተከተሉህም ምእመናን፣(በቂያቸው አላህ ነው)::››[አል አንፋል:64] ‹‹አላህ ባሪያውን በቂ አይደለምን?››[አል ዙመር:36]

ነቢያቱንና መልክተኞቹን ድል እንዳጎናጸፈ ሁሉ አላህ (ሱ.ወ.) በከሓዲዎቹ ላይ ድል አቀዳጃቸው፦

{كَتَبَ ٱللَّهُ لَأَغۡلِبَنَّ أَنَا۠ وَرُسُلِيٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ قَوِيٌّ عَزِيزٞ ٢١}[المجادلة: ٢١]،

‹‹አላህ፦ እኔ በእርግጥ አሸንፋለሁ፤መልክተኞቼም (ያሸንፋሉ ሲል) ጽፏል:: አላህ ብርቱ፣አሸናፊ ነውና::››[አል ሙጃደላህ:21]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدۡ سَبَقَتۡ كَلِمَتُنَا لِعِبَادِنَا ٱلۡمُرۡسَلِينَ ١٧١ إِنَّهُمۡ لَهُمُ ٱلۡمَنصُورُونَ ١٧٢ وَإِنَّ جُندَنَا لَهُمُ ٱلۡغَٰلِبُونَ ١٧٣}[الصافات: ١٧١-١٧٣]، {إِنَّا لَنَنصُرُ رُسُلَنَا وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَيَوۡمَ يَقُومُ ٱلۡأَشۡهَٰدُ ٥١} [غافر: ٥١].

‹‹(የርዳታ) ቃላችንም፣መልክተኞች ለኾኑት ባሮቻችን በውነት አልፋለች:: እነርሱ ተረጂዎቹ እነርሱ ናቸው:: ሰራዊቶቻችንም፣በእርግጥ አሸናፊዎቹ እነርሱ ናቸው::››[አል ሶፍፋት፡ 171-173] ‹‹እኛ መልክተኞቻችንን እነዚያንም ያመኑትን፣በቅርቢቱ ሕይወት፣ምስክሮችም በሚቆሙበት ቀን በእርግጥ እንረዳለን::››[አል ሙእሚን:51]

ከሓዲዎቹ ተልእኮአቸውን ለመገደብና የደዕዋውን ብርሃን ለማጥፋት የቻሉትን ሁሉ አደረጉ፤አላህ (ሱ.ወ.) ግን ደዕዋቸውን ድል አድራጊ በማድረግ ጸጋውን አሟላ፦

{يُرِيدُونَ لِيُطۡفِـُٔواْ نُورَ ٱللَّهِ بِأَفۡوَٰهِهِمۡ وَٱللَّهُ مُتِمُّ نُورِهِۦ وَلَوۡ كَرِهَ ٱلۡكَٰفِرُونَ ٨ هُوَ ٱلَّذِيٓ أَرۡسَلَ رَسُولَهُۥ بِٱلۡهُدَىٰ وَدِينِ ٱلۡحَقِّ لِيُظۡهِرَهُۥ عَلَى ٱلدِّينِ كُلِّهِۦ وَلَوۡ كَرِهَ ٱلۡمُشۡرِكُونَ ٩}[الصف: ٨-٩]؛

‹‹የአላህን ብርሃን በአፎቻቸው ሊያጠፉ ይሻሉ፤አላህም ከሓዲዎቹ ቢጠሉም እንኳ ብርሃኑን ገላጭ ነው:: እርሱ ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልክተኛውን በመምሪያ (መጽሐፍ)፣በውነተኛው ሃይማኖትም (በእስላም)፣ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ሊያደርገው የላከ ነው::›[አል ሰፍ:8-9]

አላህ (ሱ.ወ.) ጸጋውን ምሉእ በማድረግም እስላምን አሸናፊ አደረገ::በሁሉም መለኮታዊ ሃይማኖቶች ውስጥም የተውሒድን ወሳኝነት በአጽንኦት አሳወቀ:: ለሰው ልጆች የዋለውን ታላቅ ጸጋም በዚህ መልክትና በዚህ ሃይማኖት አሟልቶ ደመደመ ፦

{ٱلۡيَوۡمَ أَكۡمَلۡتُ لَكُمۡ دِينَكُمۡ وَأَتۡمَمۡتُ عَلَيۡكُمۡ نِعۡمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ ٱلۡإِسۡلَٰمَ دِينٗا}[المائدة: ٣]،

‹‹ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ:: ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ:: ለናንተም እስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፤››[አል ማእዳህ:3]

በተጨማሪም የሃይማኖቱን ጥበቃ ለራሱ ወስዶ ደዕዋው እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ ቋሚና ቀጣይ እንዲሆን አደርጓል፦

{إِنَّا نَحۡنُ نَزَّلۡنَا ٱلذِّكۡرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ٩}[الحجر: ٩]؛

‹‹እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፤እኛም ለርሱ ጠባቂዎቹ ነን::››[አል ሒጅር፡ 9]

እስላምንም የቀደሙት መለኮታዊ ሃይማኖቶች ሁሉ የመጨረሻው ማጠቃለያና መደምደሚያ መልክት አደረገው፦

{مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَآ أَحَدٖ مِّن رِّجَالِكُمۡ وَلَٰكِن رَّسُولَ ٱللَّهِ وَخَاتَمَ ٱلنَّبِيِّـۧنَۗ وَكَانَ ٱللَّهُ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٗا ٤٠}[الأحزاب: ٤٠]،

‹‹ሙሐመድ፣ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፤ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፤አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው+::››[አል አሕዛብ:40]

እስላምን አላህ (ሱ.ወ.) ምድርንና በላይዋ ያሉትን እስኪወርስ ድረስ ቀሪና ቀጣይ መልክት አደረገው::

ለመሆኑ ይህ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በአላህ (ሱ.ወ.) ጥበቃ እየተደረገለት ቋሚና ቀጣይ የሆነው መልክት ምንድነው . . ?

ተአምራዊው ቁርኣን

‹‹ቁርኣን ሀሳብን ተቆጣጥሮ ይይዛል፤ልቦናን ሙሉ በሙሉ ይማርካል:: ወደ ሙሐመድ የተላለፈው ስለ እውነተኛነቱ አረጋጋጭ አስረጅ ሆኖ ነው::››

ሄንሪ ዴ ካስትሬ
የፈረንሳይ ጦር ኃይል የቀድሞ ሻምበል







https://www.path-2-happiness.com